
አትፍረድ



በአቡነ ሺናዳ ሣልሳዊ
የግብፅ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ

ትርጉም፡- ዲ/ን ማዘዘ ሞሰይሁን

አሳታሚና አከፋፋይ፡-
በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
በሰንበት ትምህርቶች ማደራጃ መምሪያ
ማኅበረ ቅዱሳን
፳፻፲፪ ዓ.ም

አትፍረድ

በአቡነ ሺናዳ ሣልሳዊ
የግብፅ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
ፓትርያርክ

ትርጉም፡- ዲ/ን ማዘዘ ሞሰይሁን

አሳታሚና አከፋፋይ፡-
በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
በሰንበት ትምህርቶች ማደራጃ መምሪያ
ማኅበረ ቅዱሳን
፳፻፲፪ ዓ.ም.

© ማኅበረ ቅዱሳን ፳፻፪ ዓ.ም.
መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
ALL RIGHTS RESERVED

ሁለተኛ ዕትም ፳፻፲፪ ዓ.ም.
ሦስተኛ ዕትም ፳፻፯ ዓ.ም.
የመጀመሪያ ዕትም ፳፻፪ ዓ.ም.

ይህ መጽሐፍ
በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ/በሰ/ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ
ማኅበረ ቅዱሳን
ኢዲቶሪያል ቦርድ ታይቶ የተፈቀደ ነው።

አድራሻ፡-
በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ/በሰ/ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ
ማኅበረ ቅዱሳን
ፖ.ሳ.ቁ 80078
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

ስልክ ፡- +251 11 124 61 84/83/82

E-Mail:- distribution.procurement@eotcmk.org
or mkpublisher@yahoo.com
Website:- www.eotc-mkidusan.org

የተርጓሚው አድራሻ፡-
+251 911 30 51 66

ማውጫ

አርእስት ገጽ

መግቢያ I
መቅድም 1

ምዕራፍ አንድ
- የሚገባ ፍርድ 2
  ሀ- ሓላፊነትና የክህነት ሥራ /ግብረ ኖሎት/ 2
  ለ- የተፈጥሮ እውቀት 8
  ሐ- የአንዳንድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትዕዛዛት ትርጉም 13
  መ- በኑፋቄና በተለያዩ የስህተት መንገዶች ላይ መፍረድ 15
  ሠ- ምክር መምራትና እና ተግሣጽ 16
  ረ- ሂስ 25
  ሰ- በራስ ላይ መፍረድ 28
  ሸ- ኃጢአተኛውን የሚያጸድቅ ማነው? 28
  ቀ- ፍርድን ኃጢአት የሚያደርጉ ሁኔታዎች 33
  በ- ያለጊዜው አትፍረድ 34
  ተ- ትክክለኛ ፍርድ 35

ምዕራፍ ሁለት
- ሌሎች የመፍረድ ዓይነቶች 38
  ሀ- በሕሊና መፍረድ 38
  ለ- በንግግር መፍረድ 40
  ፈ- ሀሜት 40
  ፈ- ስም ማጥፋት 41
  ፈ- ማውገዝ 42
  ፈ- ዝናና ክብርን ማጉደፍ 45

ምዕራፍ ሦስት
- በሌሎች መፍረድ ድርብርብ በደል ስለመሆኑ 56
  ሀ- በእግዚአብሔር ላይ የሚፈጸም ጥፋት ነው 56
  ለ- በሌሎች በሚፈርድ በእርሱ በራሱ ላይ
  የሚፈጸም ጥፋት ነው 57
  ሐ- በሚፈረድበት ሰው ላይ የሚፈጸም ጥፋት ነው 61
  መ- በሰማእኑ ላይ የሚፈጸም ጥፋት ነው 62
  ሠ- አንተ በማታውቃቸው እነርሱም በማያውቁህ
  ሰዎች ላይ የሚፈጸም ጥፋት ነው። 63
  ሠ- በሌሎች መፍረድ የሚያስከትላቸው ሌሎች
  የኃጢአት ሥራዎች 64
  - ፍቅርን ማጣት 65
  - የልብ መደንደን 67
  - ጭቅና /ሜና/ 68
  - ውሸት 69
  - ትሕትና ማጣት 70
  - ሌሎችን ማሰናከል 72
  - ስድብና ንቀት 73
  - ሥነ ሥርዓት ማጣት 73
  - በሌሎች ምኞት /ሐሳብ/ ላይ መፍረድ 74
  - ግብዝነት 75
  ቀ- በኀጥሞት ውጤቶች በክሴት ቅጂዎች አማካኝነት
  በሌሎች መፍረድ 47
  በ- በመስማት መፍረድ 49
  ተ- ሌሎች የመፍረድ ኃጢአት ዓይነቶች 53

ምዕራፍ አራት
- በሌሎች ስለመፍረድ የአባቶች ትምህርት 77

ምዕራፍ አምስት
- መፍትሔዎች 93
  ሀ- ሰዎችን ማክበር ልመድ 93
  ለ- የጊዜ ማሳለፊያ የሚሆን መልካም ስምሪት ፈልግ 95
  ሐ- መፍረድን ከመስማት ተለይ 99
  መ- የእንክርዳድና የስንዴው ምሳሌ 102
  ሠ- ትሕትናና ራስን መገሠጽ 105
  ሠ- በሌሎች ላይ መፍረድን ለማስወገድ የሚረዱ
  የመፍትሔ ልምምዶች 108
  ፩ሀ- ከንግግር ኃጢአት ራስህን ለመፈወስ
  ራስህን አሠልጥን 108
  ፩ለ- «እንግዲህ ከወዲት እንደወደቅህ አስብ፤
  ንስሐም ግባ» 108
  ፩ሐ- በሌሎች ላይ መፍረድን በፍቅር አሸንፍ 108
  ፩መ- በሌሎች ላይ መፍረድን በእንተም ላይ ደግሞ
  ጉዳት እንደሚያስከትል አስብ 109
  ፩ሠ- የሰዎችን ክፉ ሥራ አለማሰብን ወይም በችኮላ
  አለመፍረድን ለራስህ አስለምድ 110
  ፩ሠ- በሰዎች ላይ በርህራሄ መፍረድን ለራስህ
  አስለምድ 110
  ፩ረ- በሚታዩ ነገሮች ሁሉ አትፍረድ 111
  ፩ሰ- የሚፈትኑህ /የሚያስቆጣህን/ መታገስን
  ራስህን አስለምድ 111
  ፩ሸ- ሰውን እጁ በሌለበት ሁኔታ አትፍረድበት 112
  ፩ቀ- በወቀሳ መልክ ስትፈርድም ጥንቁቅ ሁን 112

መግቢያ

በዘመናችን ሕይወትን የሚያድሱ፣ ነፍስን የሚቀድሱ ታላላቅ የሃይማኖትና የሥነ ምግባር መጻሕፍትን በማዘጋጀት ዓለምን በማስተማር ላይ ያሉት የግብጽ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ ከጻፏቸው መጻሕፍት «Judge Not others» የሚለው አንዱ ነው:: ይህ መጽሐፍ በሌሎች ሰዎች ላይ የመፍረድ ግንዛቤ /ፅንስ ሐሳብ/ ውስጥ ያሉ አንዳንድ ግልጽ ያልሆኑ ነጥቦችን ለማብራራትና የሚገቡና የማይገቡ በሌሎች የመፍረድ አካሔዶችን ዘርዝሮና ተንትኖ ለማሳየት የተዘጋጀ ነው::

ቅዱስነታቸው ሰዎች ሁሉ የነፍስ ንጽሕናን ገንዘብ እንዲያደርጉ ካላቸው የዘወትር ትጋት በመነጨ ያዘጋጁትን ለክርስቲያናዊ ሕይወት የሚበጅ መጽሐፍ፣ ራስን በመግዛትና በፍቅር እየተመላለሱ እግዚአብሔርን ደስ በማሰኘት ለመኖር ለፈቀዱ ኢትዮጵያውያን ሁሉ እንደሚጠቅም በማጤን መጽሐፉ ከእንግሊዝኛው ቅጂ ወደ አማርኛ «አትፍረድ» የሚል ርእስ ይዞ በቀጥታ ተተርጉሟል::

መጽሐፉ አምስት ምዕራፎች አሉት:: የመጀመሪያው ምዕራፍ፡ የምንፈረደው ፍርድ ሁሉ ኃጢአት ሆኖ የሚወሰድ ባለመሆኑ በምን ላይ፣ በምን ሁኔታና ስለምን ስንፈርድ የሚገባ ፍርድ እንደሆን የሚተነትን ነው:: በተጨማሪም በዚሁ ነጥብ ላይ ለሰዎች ግራ የሚያጋቡና ለስሕተት መነሻ የሚሆኑ አረዳዶችን ግልጽ ያደርጋል::

በሁለተኛው ምዕራፍ የኃጢአት መንገድ በሆነው በሌሎች የመፍረድ አካሔድ ውስጥ ዓይነቶቹንና መንገዶቹን በመዘርዘር ያስተምረናል:: በሦስተኛው ምዕራፍ ደግሞ በሌሎች የመፍረድ ኃጢአት ውስጥ ስንገባ መፍረድ በራሱ ካለው ኃጢአትነት ባለፈ ድርብ ድርብርብ በደሎችን እንደሚያስከትል ይገልጻል::

የመጽሐፉ አራተኛ ምዕራፍ በትምህርትና ቅድስናቸው የተመሰከረላቸው አባቶች /ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን/ በሌሎች ላይ ስለመፍረድ ነገር ያስተማሩትን ትምህርት ይጠቀመናል:: የመጽሐፉ የመጨረሻው ምዕራፍ ኃጢአት ከሆነው/ከማይገባው/ በሌሎች የመፍረድ አካሔድ ተቆጥበን በንጽሕናና በቅድስና እንድንኖር የሚያደርጉ የመፍትሔ ትምህርቶችን ይሰጣል::

በአጠቃላይ ተገቢ በሚባለው በሌሎች የመፍረድ አካሔድ ያለብንን ሓላፊነት እንድንወጣ፣ ኃጢአት ከሆነው በሌሎች የመፍረድ ኑሮ ደግሞ ተቆጥበን ጽድቅን እንድንኖር የሚያመለክት መጽሐፍ መሆኑን በመገንዘብ፣ አንብባችሁ በምታገኙት ጭብጥ እንደምትደሰቱ በማመን ነው::

ተርጓሚው

መቅድም

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «እንዳይፈረድባችሁ አትፍረዱ፤ በምትፈርዱበት ፍርድ ይፈረድባችኋልና፤ በምትሰፍሩበትም መሥፈሪያ ይሠፈርባችኋል::» በማለት ያዘናል:: ማቴ. ፯+፩ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም «አንተ በሌላው ሎሌ የምትፈርድ ማን ነህ? እሱ ቢቆም ወይም ቢወድቅ ለገዛ ጌታው ነው፤ ... » በማለት ይናገራል:: ሮሜ. ፲፬+፬ ሌላው ቅዱስ ጳውሎስ ያነሣውን ጥያቄ የደገመው እና መልስም የሰጠው ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ ነው:: «በሌላው ላይ ግን የምትፈርድ አንተ ማን ነህ» ያዕ. ፬+፲ ደግሞም እንዲህ ይለናል «ወንድሞች ሆይ እርስ በእርሳችሁ አትተማሙ:: ወንድሙን የሚያማ በወንድሙም የሚፈርድ ሕግን ያማል»

እነዚህ ትዕዛዛት ካሉ በምን ደረጃ እና በምንስ መንገድ ነው «በሌሎች አትፍረዱ» የሚለውን ትእዛዝ የምንረዳው? ይህ ትዕዛዝ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ሌላው ቀርቶ አንድን በስህተት ውስጥ ያለን ሰው ምንም የማይስማማውን ቃል ፍፁም እንዳንናገረው የቀረበ ትዕዛዝ ነው? በሌሎች መፍረድ በማንኛውም ጉዳይ እና ሁኔታ ውስጥ ስህተት ነው? ወይስ በአንዳንድ ጉዳዮች የሚፈቀድ ወይስ የግድ አስፈላጊ ይሆን? እንዲህስ ከሆነ በሌሎች ላይ መፍረድ የሚቻለው መቼ ነው? በማንስ ላይ ነው? በሌሎች ላይ መፍረድ የግድ የሚያስፈልገውስ መቼ ነው? በሌሎች ላይ ስንፈርድ ስህተት ላይ የምንወድቀውስ መቼ ነው? እነዚህን ሁሉ ጥያቄዎች በመጽሐፉ በተለያዩ ክፍሎች እንመልሳለን::

ምዕራፍ አንድ

የሚገባ ፍርድ

- ሓላፊነትና የክህነት ሥራ /ግብረ ናሎት/
- የተፈጥሮ እውቀት
- የአንዳንድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትዕዛዛት ትርጓሜ
- በኑፋቄና በተለያዩ የስህተት መንገዶች ላይ መፍረድ
- ምክር፣ መመሪያ እና ተግሣጽ
- ሂስ
- በራስ ላይ መፍረድ
- ኃጥኡን የሚያጸድቅ ማነው?
- ፍርድን ኃጢአት የማያደርጉ ሁኔታዎች
- ከሚገባው ጊዜ በፊት ስለ መፍረድ
- ትክክለኛ ፍርድ

በብዙ አጋጣሚዎች መፍረድ ስህተት አይደለም:: ከእነዚህ የሚከተሉትን እንይ፦

፩/ ሓላፊነትና የክህነት ሥራ /ግብረ ናሎት/

በአንድ ሓላፊነት ካለበትና ሥልጣን ከተሰጠው አካል ከተላለፈ መፍረድ የተፈቀደ ነው:: የተወሰኑ ሰዎች በሌሎች ላይ ሥልጣን እንዲኖራቸው በእግዚአብሔር የተሾሙ ሊሆኑ ይችላሉ:: በመሆኑም እግዚአብሔር እንዲሠለጥኑ በፈቀደላቸው ወገን ላይ ፍርድን ማሳለፍ ይችላሉ:: በዚህ መሠረት «እንዳይፈረድብህ አትፍረድ» የሚለው ቃል በእነርሱ ላይ ተፈጻሚ አይሆንም:: ለእነዚህ ሰዎች መፍረድ መብት ብቻ ሳይሆን ግዴታም ነው:: በተሾሙበት ሕዝብ ላይ ካልፈረዱ ጉድለት/ጥፋት/ እንዳለባቸው ይታሰባል::

በሌሎች ላይ እንዲፈርዱ እግዚአብሔር ካሠለጠናቸው መካከል አባቶች እና እናቶች /ወላጆች/ ተጠቃሽ ናቸው:: እነርሱም ልጆቻቸውን በሥርዓት እንዲያሳድጉ ከእግዚአብሔር አደራ ተቀብለዋል፡ ሥልጣንም ተሰጥቷቸዋልና:: በጥፋቶቻቸው ላይ እንዲፈረዱ እንዲገሥጹም በእግዚአብሔር ተሾመዋል:: ልጆቻቸውን «አንተ ስህተትን እየሠራህ ነው፤ አቁም!» ማለት አለባቸው:: ልጆቻቸው ጥፋቶቻቸውን የማያቆሙ ከሆነም ሊቀጧቸው የተገባ ነው:: በእርግጠኝነት ይህ መፍረድ ቢሆንም ኃጢአት ያልሆነና ተገቢ ፍርድ ነው:: ምክንያቱም ይህ የመነጨው ሥልጣን ካለው አካል እንደውም እግዚአብሔር እንዲያደርገው በትዕዛዝ የተቀበለውና ልጁን እንዲያርቅ /እንዲያርም/ የተፈጥሮም ሓላፊነትን ከያዘ ወላጅ ነው:: በተጨማሪም ልጁን ወደ መልካም ከማምጣት የቦዘነ፣ በሥርዓት እንዲያድግ ክትትል ያላደረገ፣ ያልመራ፣ በሥራዎቹ ሁሉ ላይ ያልፈረደ እና በክፉ ተግባሮቹም ያልወቀሰ አባት እግዚአብሔር ይቀጣዋል:: ለዚህም በምሳሌነት የሚጠቀሰው እግዚአብሔር ስለልጆቹ ሥርዓት አልበኝነት የቀጣው ካህኑ ኤሊ ነው::

ካህኑ ኤሊ ልጆቹ በእስራኤል ሁሉ ፊት ምን ይሠሩ እንደነበር ሰምቷል:: ሊፈርድባቸው ቢሞክርም ከልብ /በጥብቅ/ አልነበረም:: እንዲህም ብሏቸዋል:: «... ስለ ክፉ ሥራችሁ ከዚህ ሕዝብ ሁሉ ሰምቻለሁ ስለምን እንዲህ ያለነገር ታደርጋላችሁ? ልጆቼ ሆይ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ኃጢአተኛ በማድረጋችሁ ስለናተ የደረሰኝ ወሬ መልካም አይደለምና ይህ አይሆንም...እነርሱ ግን እግዚአብሔር ሊገድላቸው ወድዶአልና የአባታቸውን ቃል አልሰሙም» ፩ ሳሙ. ፪+፳፪-፳፭

ጌታም በኤሊ ተቆጣ በልጆቹ በጽናት ከመፍረድ ችላ ብሏልና:: እግዚአብሔርም እንዲህ አለ «እነሆ የሰማውን ሁሉ ሁለቱን ጆሮዎቹን ጭው የሚያደርግ ነገርን በእስራኤል አደርጋለሁ:: በዚያም ቀን በቤቱ ላይ የተናገርኩትን ሁሉ በኤሊ ላይ አወርዳለሁ...:: ልጆቹ የእርግማን ነገር እንዳደረጉ አውቆ አልከለከላቸውምና ስለኃጢአቱ በቤቱ ለዘላለም እንድፈርድ አስታውቄዋለሁ» ፩ ሳሙ. ፫+፲፩-፲፬ ስለዚህ በዚህ መሰል ጉዳይ በሌሎች መፍረድ ግዴታ ነው:: በመሆኑም ለመፍረድ ሥልጣን ኖሮት በዚህ መሰል ጉዳይ ሁሉ ፍርድን ያላሳለፈ ወገን እርሱ ለፍርድ እና ለቅጣት የተሰጠ ነው::

አንድ አባት በስሕተት ውስጥ በወደቀ ልጁ ላይ መፍረድ ብቻ ሳይሆን ባለው ኃይል ሁሉ ሊቆጥበው ወይም ሊከለክለው ግዴታ አለበት፤ ወይም ሊጠብቀው ይገባል:: ወላጆች ልጆቻቸውን በሥርዓት እንዲያሳድጉ፤ ልጆችም ለወላጆቻቸው በጌታ ፈቃድ እንዲታዘዙ እግዚአብሔር ብዙ ትዕዛዛትን ሰጥቶአል:: «ይህ የሚገባ ነውና::» ኤፌ. ፮+፩ ከላይ በሥጋ ለወለዱን አባቶቻችን የተሰጠው ትዕዛዝ በመንፈሳዊ አባትነትና መንጋውን ለመጠበቅ ለተሾሙ አገልጋዮች ሁሉ ይሠራል:: እግዚአብሔር አባቶች ካህናትን፣ የመንጋውን መጋቢዎች እና ነቢያትን ኃጢአተኞችን እንዲያስጠነቅቁና እንዲያወግዙ ግዴታን የጣለባቸው እርሱ እንዲህ ብሏል፦

«የሰው ልጅ ሆይ በእስራኤል ቤት ጠባቂ አድርጌሃለሁ፤ የአፌን ቃል ስማ ከእኔም ዘንድ አስጠንቅቃቸው:: እኔ ኃጢአተኛውን በእርግጥ ትሞታለህ ባልኩት ጊዜ አንተም ባታስጠነቅቀው ነፍሱም እንድትድን ከክፉ መንገድ ይመለስ ዘንድ ለኃጢአተኛው አስጠንቅቀህ ባትነግረው ያ ኃጢአተኛ በኃጢአት ይሞታል፤ ደሙን ግን ከእጅህ እፈልጋለሁ» ሕዝ. ፫+፲፯-፲፰

በመሆኑም ለአባቶች ካህናትና መምህራን የኃጢአተኞችና ዐመፀኞች የክፉት መንገድ የሚያጠፋቸው መሆኑን በመንገር እንዲያስጠነቅቁ፣ እንዲገሥጹ እንዲገቱ እንዲያወግዙ ሥልጣን የተሰጣቸው ብቻ ሳይሆኑ ግዴታም ያለባቸው ናቸው:: ባያደርጉት የክፋታቸው ውጤት ጥፋት መሆኑን በማሳየት ሓላፊነታቸውን ከተወጡ እነርሱ ከሚመጣባቸው ፍርድ ይድናሉ:: በዚህም በሕዝቅኤል አድሮ የተናገረው የጌታ ቃል ተፈጻሚ ይሆናል «ነገር ግን አንተ ኃጢአተኛው ብታስጠነቅቀው እርሱም ከኃጢአቱና ከክፉ መንገዱ ባይመለስ በኃጢአቱ ይሞታል፤ አንተ ግን ነፍስህን አድነሃል» ሕዝ. ፲+፲፱

ስለ መምህርና ተማሪ፣ ስለአሠሪና ሠራተኛ፣ ስለዳኛና ተከሳሽ ስናወሳም በወላጅ እና በልጅ እንዳልነው ሊሆን ይችላል:: እነዚህ ሁሉ ባላቸው የሥልጣን ወሰን ውስጥ፣ ለተግባሮቻቸው በተሰጣቸው ገደብ ውስጥ፣ በግልጽ በተቀመጡ የፍትሕና ርትዕ መርሖዎች ላይ ተመሥርቶ በተሰጣቸው የሥራ ደረጃና ሓላፊነት ውስጥ ሆነው እንዲፈርዱ መብት አላቸው:: አንድ መምህር ሥራውን በሚሠራበት ጊዜ በተማሪነት ስነ-ምግባር ውስጥ የማይኖር ጻተኛ ተማሪውን ስለማድፈቱ ቢነግረው፣ ቢገሥጸውም ሮይም አንድ አሠሪ የቢታቹን /ሬዳቱን/ በሥራው ታማኝ ስለአለመሆኑ ቢነግረው ወይም አንድ ዳኛ በወንጀለኛ ላይ ቢወስን በዚህ መንፈስ ውስጥ ሆነው በሚሰጡት ፍርድ ሁሉ «እንዳይፈረድብህ አትፍረድ» የሚለውን የጌታ ቃል እንደጣሱ ሊታሰብ አይችልም::

ከእነዚህ ወገኖች አንዱ «በሌላው ግን የምትፈርድ አንተ ማን ነህ?» የሚለው የሐዋርያው ቃል ቢጉጥመው «እኔ ለዚህ ሰውና ለሥራው ሓላፊነት አለብኝ» ብሎ ሊመልስ ይችላል:: ያዕ. ፬+፲፪ እነዚህ ወገኖች የሚፈርዱት በሥልጣን ነውና በሥራቸው ሁሉ በሌላው የመፍረድን ኃጢአት ሠሯት አይባልም:: ለእነርሱ መፍረዳቸው መብትም ግዴታም ነውና:: እነዚህ ወገኖች የመፍረድ መብትና ግዴታ ባይኖርባቸው ሥራቸው ይወሳሰባል፤ ጥፋት ይሠለጥናል፤ ግዴለሽነት ያይላል::

ሐኪሞች በተሰማሩበት ሙያ ስለበሽተኞቻቸው በሚሰጡት ምክር ውስጥ ታማሚውን ስለሚያሰቃይ በሽታው እርሱ ከሚያስበው /ከሚገምተው/ የተለየ የምርመራ አስተያየት ሊሰጡ ይችላሉ:: ፍላጐታቸው ግን ቁስልና ስቃዩን የበለጠ ማምጣት ወይም ስሙን ማጥፋት ሳይሆን ታማሚውን ለማዳን መሆኑ ለማንም ግልጽ ነው:: ይህም ቅዱስ ባስልዮስ ስለገዳማዊ ሕይወት በገለጸ ጊዜ ከተናገረው ጋር የሚመሳሰል ነው:: ታላቁ ቅዱስ ባስልዮስ በሌሎች ላይ

ስለመፍረድ ነገር በተጠየቀ ጊዜ እንዲህ ሲል ተናግሮ ነበር:: «ለመነኩሳት ሕይወት ሓላፊነት ያለባቸው ሁሉ የአንድ መነኩሴ ጉዳይን /ነገር/ በሚመረምሩ ጊዜ የሚታረምበትን መንገድ ለመ ፈለግና ሌሎችን ከተመሳሳይ የውድቀት ጠንቆች ለመጠበቅ በመነኩሴው ግድፈት ላይ ቢነጋገሩ ይህን በፈሪሀ እግዚአብሔር መንፈስ ውስጥ ሆነው እስከፈጸሙት ድረስ ሌሎች ላይ በመፍ ረድ የኃጢአት ቀንበር ሥር ወደቁ ሊባል አይችልም::»

ጌታ ለቤተ-ክርስቲያን የመፍረድ ሥልጣንን ሰጥቷል

ጌታ ለቤተ ክርስቲያን የማሰርና የመፍታት ሥልጣንን ሰጥ ቷታል:: በሙግት /ክርክር/ ውሳኔ እንድታሳልፍ፣ ፍርዷን የማ ይሰማ ግንም ደግሞ እንደ ሕዝባዊ እና አረመኔ እንዲቆጠር መብትን ሰጥቷታል:: ማቴ. ፲፰፥፲፰-፲፱ ቤተ ክርስቲያን አንድን ሰው እንደ ኃጢአተኛ ቀጥራ በምታወግዝበት ጊዜ፣ ርኩሰት እን ደገጠማት ሊታሰብ አይገባም:: ምክንያቱም ከላይ በቀረበው አግ ባብ መብትና ሥልጣኗን የእውነት አምላክ ሠርቶላታልና::

መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ኃጥአንን ገሥጿል:: ማቴ.፫፥፯ ቅዱስ ጳዉሎስ ደግሞ ከብዙዎች ለይቶ በሞኝነት የተጠመዱ የገላትያን ሰዎች ገሥጿል:: ገላ. ፫፥፩ እንዲሁም ደግሞ ደቀመዝ ሙሩን ቅዱስ ጢሞቴዎስን በሥሩ ያሉትን እንዲያሳምን፣ እንዲ ገሥጽ፣ እንዲያበረታታ አዞታል:: /፪ ጢሞ. ፬፥፪/ እንዲህም ሲል ይመክረዋል:: «ሌሎች ደግሞ እንዲፈሩ ኃጢአት የሚሠሩትን በሁሉ ፊት ገሥጻቸው» ሰዎች መካከል የነበሩ ዐመፀኞችንም

በግልጽ አውግዟል:: ፩ ቆሮ. ፭፥፭ ከፉዎችንም ከመካከላቸው ለይተው ባለማውገዛቸው ምእመናኑንም ገሥጿል:: ፩ ቆሮ. ፭፥፲፭ ቅዱስ ጴጥሮስም ሐናንያንና ሚስቱን ሰጲራን እንዳወገዘ እናያ ለን:: ሐሰተኞች ስለነበሩ፣ በአድማም የእግዚአብሔርን መንፈስ ስለተፈታተኑ በአደባባይ ፈርዶባቸዋል:: እግዚአብሔርም ቀጥቶ አቸዋል:: የሐዋ. ፭፥፫-፱

ምናልባት እንዳንዶቻችን ተነሥተን «እኔ ሐዋርያ፣ ነቢይም አይደለሁም» ልንል እንችላለን:: ይህ ትክክል ነው:: ነገር ግን እግዚአብሔር በሰጠን ማንኛውም ሥልጣን እና ደረጃ ውስጥ ሆነን ልንፈርድ እንችላለን::

ስለዚህ ምንም እንኳን እጅግ ውስን ነው ብለህ ብታስብም በተሰጠህ የሓላፊነት ወሰን ውስጥ ሆነህ አድርግ:: ከምንም በላይ ግን በቀጣይ የመጽሐፉ ክፍሎች ከምንገልጸው መንፈሳዊና እውነተኛ መሠረት ላይ እየፈረድክ መሆኑን እርግጠኛ ሁን::

፪. ተፈጥሮአዊ ዕውቀት /ሕገ ልቡና/

አንዳንዴ በፍርድ ክፉና ደግን ለይቶ የመሄድ ነገር ተፈጥሮ አዊ ሊሆን ይችላል:: ለምሳሌ አንድ ሰው የስድብን ቃል ሲናገር ብትሰማ፣ ይህን ቃል ስድብ /የከፋት ሥራ/ እንደሆነ ቢያንስ በሐሳ ብህ ለይተህ እንዳትሄድ ራስህን ልትከለክል አትችልም:: እንዲ ሁም አንድ ሰው ራሱን መቆጣጠር እስኪያቅተው በንዴት እና በእልህ ማዕበል ውስጥ ሆኖ ቢታይ ወይም አንዲት ሴት ገደብ በሌለው ልብስ ዘማ ታጅላ ዕዩኝ ዕዩኝ ስትል ብትታይ እየሆነ ስላለው የማይገባ ነገር ራስህን ቢያንስ ምንም እንዳታስብ መከላከል እንዴት ይቻላል?

አንድን ሰው ሲምል ሲገዝት፣ ስለዓለም ሲዘፍን፣ ሲዘምር፣ ነገረ ዘርቅም ሠልጥናበት ባይ ስለምሰማው ነገር እንዳልፈርድ እንዴት ራሴን ልከለክል እችላለሁ? አንድ ሰው ከሕሊናው ግፊት የተነሣ ሳያቅድ /ሆን ብሎ ለመፍረድ ሳይንደረደር/ ፍርድን ግን ሊሰጥ ይችላል::

መንፈሳዊ ጉዳዮችን ከጥርጣሬ ርቀን በአግባቡ ልንረዳቸው ይገባል:: በሌሎች አለመፍረድም በተፈጥሮ የተሰጠንን ነገሮችን የመለየት ባህርይ ማጣት ማለት አይደለም:: እግዚአብሔር ራሱ ለሰው ክፉና ደግን የሚለይ ሕሊናን በማደሉ ለእኛ ያለንን ለይቶ /መዝኖ/ የመሄድ አቅም ከውስጣችን የማጥፋት ችሎታና ፍላጎት የለንም::

ሰው በራሱና በሰው ሥራ ላይ ያሉ ልዩነቶችን በመመዘን ሊፈ ርድ የሚችለው በተፈጥሮው በተሰጠው ብርሃን ዕውቀት ነው:: ሰው ይህን የሚመዝንበትን አቅም ዕሴትና መርኅ ካጣ መሆን ያለበትና የሌለበትን ነገር እንዴት ሊያውቅ ይችላል? ጌታም በተራራው ላይ ሰብከቱ «ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ» ያለበት ምክንያት ይህ ነው:: ይህንንም ሲያብራራ እንዲህ ይለናል «ከእሾህ ወይም ከኩርንችትስ በለስ ይለቀማልን? እንዲሁ መልካም ዛፍ መልካም ፍሬን ያደርጋል፤ ክፉም ዛፍ ክፉን ፍሬ ያደርጋል:: መልካም ዛፍ ክፉን ፍሬ ማፍራት ወይም ክፉ ዛፍ መልካም ፍሬን ማፍራት አይቻለውም፤ ስለዚህ ከፍሬአቸው ታውቃቸዋላችሁ::» ማቴ. ፯፥፲፮

እንግዲህ እሾህን አይተን እንደሆነ እሾህ መሆኑን ልናውቅ እንችላለን ወይም መልካም ፍሬ ያልሆነን አይተን እንደሆነ መልካም አለመሆኑን ለይተን ልናስብ እንችላለን:: ይህንን ታዲያ በማለታችን እኛ ላይ ይፈረድብናል ልንል እንችላለን? በእርግጠ ኝነት አይደለም:: ቅዱስ አውግስጢኖስ ከላይ ስለ ተጠቀሰው የወን ጌል ቃል ሲናገር እንዲህ ይላል «ውስን ዛፎች መልካም ያልሆ ነውን ፍሬ ያፈራሉ፤ ውስኑ ደግሞ መልካም ፍሬን ያፈራሉ:: ማንም ቢሆን መጥፎውን ጥሩ፤ ጥሩውንም መጥፎ በማለት ራሱን ሉና፤ በነዚህ ነገሮች ራሳችንን ልናታልል አንችልም::» ያለምርምር ነገሮች ሁሉ ግልጽ ሆነው ይታያ አያታልልም::

ሐዋርያው ቅዱስ ጳዉሎስም ከዚሁ ጋር በተያያዘ «የአንዳንድ ሰዎች ኋጢአት የተገለጠ ነው፤ ፍርድንም ያመለክታል» በማለት ይገልጸዋል:: ፩ጢሞ. ፭፥፳፬

እነዚህን ግልጽ የኃጢአት ሥራዎች በሰዎች ላይ ብታይ በአንተ ምክንያት የሆኑ አይደሉም:: ስለዚህም በተፈጥሮ ምክንያት የምት ፈርድባቸው ግልጽ የኃጢአት ሥራዎች እንዳሉ ይሰማሀል:: ይህም በአንተ እንደጉድለት/ጥፋት/ አይታሰብም:: ይሁንእንጂ ጉዳዮች ላይ መፍረድና በሰዎች ላይ በመፍረድ መካከል ልዩነት ግን እንዳለ ከግምት ማስገባት ይኖርብሃል::

አንድን ሰው ጠጥቶ ከዚያ ወደዚያ ሲወላገድ ባየህ ጊዜ በእር ግጥም ይህ ተግባሩ ተገቢ አለመሆኑን ለይተህ እንዳትፈርድ ራስ ህን መከላከል አትችልም:: ነገር ግን ስለሰውየው በጥቅልና በጥል ቀት ሳትረዳ ልታወግዘው ግን አይገባም:: ምናልባትም በሌሎች

ተታሉ፣ ወይም ባለማወቅ እና በመሳሰሉት ምክንያቶች ጠጥቶ ይሆናል፤ ማን ያውቃል? ከዚህም መፍረድና ማውገዝ ሁለት የተለያዩ ነገሮች እንደሆኑ መረዳት ይቻላል::

የስድብን ቃል በሰማሁ ጊዜ፤ ስድብም መሆኑን ተረድቼ በፈረድሁ ጊዜ ይህ የሕሊና ሚዛን /ፍርድ/ ጉዳይ ነው:: ነገር ግን የስድብን ቃል ሰምቼ ከሆነ፣ የተናገረውንም ሰው ሌላው ቀርቶ በሐሳቡም እንኳን እንዲህ ነው ወይም እንዲያ ነው በማለት የምፈርድበት፤ ይህ ይገባዋል በማለት ዋጋን እስከመደልደል ከደረ ስኩ ይህ በእውነት ውግዘት ነው:: በዚህ ጊዜም በሥራው ላይ ካነጣጠረ ከመጀመሪያ ይሕሊና ፍርድና ሚዛን በዘለለ ሰውየውን ወደ ማውገዝ ተሸጋግሬአለሁ ማለት ነው:: ምናልባትም በባሰ ሁኔታ ስለዚህ ሰው ታሪክ ለሌሎች እናገርም ይሆናል:: በዚህ ዓይነት ሥራ ውስጥ ከተገኘሁ በተፈጥሮ ከተሰጠኝ የሕሊና ፍርድ የተነሣ ተግባርን ከፉ ደግ ከማለት ያለፈ ውግዘት እና ከዚያም በላይ ሐሜት እየፈጸምኩ ነው:: እነዚህ ሁለቱም ፍርድን በራሳችን ላይ የሚያመጡብን የኃጢአት ሥራዎች ናቸው:: አንዳንድ ነገሮች የተገለጡ የኃጢአት ሥራዎች ቢመስሉም ያንን ለማለት ግን በማያ ስችሉን እውነታዎች ውስጥ የተከሰቱ ሊሆኑ ይችላሉ::

በጾም ወራት አንድን ሰው ወተት ሲጠጣ ብታየው፤ ስግብ ግብና ጾምንም ያፈረሰ እንደሆነ ብታስብ በግልጽ ኃጢአትን ሲሠራ እንዳገኘኸው፤ እንደ ኃጢአተኛም በማሰብ ብትኮንነው /ብታወግ ዘው/ በዚህ ፍርድህ ከስህተት ልትወድቅ ትችላለህ:: ይህ ሰው ምናልባትም ታማሚ፣ በሆድ ሕመም /Ulcer/ የሚሰቃይ፣

ወተትም ለበሽታው እንደመድኃኒት የሚያስፈልገው ሊሆን ይችላልና:: ለጤንነቱ ሲል ያስፈቃዱ የሐኪሙን ትዕዛዝ አክ ብሮ ሊሆን ይችላልና:: ይህ ሰው እንደስሰታም፣ ጾምንም እንዳ ፈረሰ ሊፈረድበት አይችልም::

እንዲሁም ቅዱሳን ሰዎች እንደተናገሩት ሁሉንም መብል በበጐ ሕሊና ከጽኑ ፍትወት እና ልዩነት ተቆጥበን ልንወስድ እንች ላለን:: በዚህም የሐዋርያው የቅዱስ ጳዉሎስን ቃል ማስታወስ እንችላለን:: «የሚበላው የማይበላውን አይናቀው፤ የማይበላውም በሚበላው አይፍረድ፤ እግዚአብሔር ተቀብሎታልና» ሮሜ. ፲፬፥፫ «አንተ በሌላው የምትፈርድ ማን ነህ? እርሱ ቢወድቅ ወይም ቢቆም ለገዛ ጌታው ነው፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ሊያቆመው ይችላ ልና ይቆማል» ሮሜ. ፲፬፥፬

በእነዚህ ነገሮች ማንም የመፍረድ መብት የለውም:: ወደ ፍርድም የሚመሩ ግልጽ የኃጢአት ሥራዎች አይደሉም:: ግልጽ ኃጢ አቶችስ ማመንዘርን፣ ስርቆትን፣ ቁጣ ጸብጫሪነት እና ርኩሰት የመሳሰሉት ናቸው:: በፈቃድና በዓላማ ላይ ተመሥርተን በምን ሠራቸው ነገሮች ላይ እኛ አንፈርድም:: የልባችን ሐሳብ የሚያውቀው ግን እግዚአብሔር ብቻ ነውና:: በእርግጥም የሰውን ልብ የሚ መረምረው፣ የሰውን የሥራውን መነሻና ዓላማውን የሚያውቀው እግዚአብሔር ነው:: እኛ በማናውቀው ነገር ውስጥ ሁሉ ያለ ውን የሰውን የሥራውን ክፋትና ደግነት አይቶ ይፈርዳል::

፫. የአንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትዕዛዛት ትርጉም

በመጽሐፈ ምሳሌ የተጠቀሰ «ከቁጡ ሰው ጋር ባልንጀራ አትሁን፤ ከወፈፍም ጋር አትሂድ» የሚል የትዕዛዝ ቃል አለ:: ምሳ. ፳፪፥፳፬ ታዲያ ይህን ለንዴት የተሰጠ ሰው ካላወቅነው በስ ተቀር ከእርሱ ለመራቅ እና ይህንንም ትዕዛዝ ለመፈጸም እንዴት እንችላለን? ይህስ በሌሎች ላይ የመፍረድ ኃጢአት ሊሆን ይችላል? አይደለም:: ይህ አስቀድመን ያነሣነው ተግባሩን አይቶ የማወቅ፣ ወይም ጉድጓድን እንዳንወድቅበት መርጠን እንደ መጓዝ ያለ ርምጃ ነው::

በሌላም ቦታ «ክፉ ባልንጀርነት መልካሙን አመል ያጠፋል» ተብሎ ተጽፏል:: ፩ቆሮ. ፲፭፥፴፫ መጥፎ መሆኑን በጥቅል ሳትረዳ ከዚህ ዓይነት ክፉ ባልንጀርነት መቆጠብ እንዴት ትችላለህ? ይህን መረዳት ታዲያ በሌሎች ላይ የመፍረድ ኃጢአት ሊሆን ይችላል? አይደለም:: በዚሁ አግባብ በመዝሙረ ዳዊት «ምስጉን ነው በክፉዎች ምክር ያልሄደ በኃጢአተኞች መንገድ ያልቆመ በዋዘኞችም ወንበር ያልተቀመጠ» በማለት ስለቀረበው ትዕዛዝም መናገር እንችላለን:: አንድ ሰው ግብራቸውን አስ ቀድሞ ሳያውቅ ከዐመፀኞች፣ ከኃጢአተኞችና ከዋዘኞች ራሱን ለይቶ ሊጓዝ ይችላል? ይህ ዕውቀት ታዲያ በሌሎች የመፍረድ ኃጢአት ሊሆን ይችላል? ይህ በእውነት በማወቅና በመቆጠብ ደረጃ ብቻ የሚወሰን ከሆነ ኃጢአት ሊሆን ይችላል:: ሌላው ቀርቶ የእነዚህን ወገኖች እርምጃ በእርግጠኝነት የማይገባ መሆኑን ተረድቶ ጓደኛን፣ የምናውቀውን፣ ዘመድን ወይም

ተማሪን ከእነርሱ እንዳያብር መምከር ኋጢአት ሊሆን አይች ልም:: ወይስ የምታስብላቸውን ሰዎች ወደ ጉድጓድ እንዲወድቁ «በጉድጓድ መፍረድ አልፈልግም» በማለት ትተዋቸዋለህ? ሐዋር ያው እንዲህ ይላል «ወንድሞች ሆይ ከኛ እንደተቀበለው ወግ ሳይሆን ያለሥርዓት ከሚሄዱ ወንድሞች ትለዩ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናዛችኋለን::» ፪ ተሰ. ፫፥፮

እንዲህ ያለውን «ወንድም» ያለሥርዓት መሄዱን በእጅጉ ካላ ወቅህ እንዴት ልትለየው ትችላለህ? ይህስ ታዲያ በሌሎች ላይ የመፍረድን ኃጢአት ገንቦን ሊያስብል ይችላል? ሊሆን አይችልም:: ምክንያቱም የአንዳንዶች ኃጢአት የለየለት ነውና::

ስለ ማሰናከያ ድንጋይ ተነግሮ የተሰጠን ትዕዛዝም በተመሳሳይ የሚታይ ነው:: መንፈሳዊ ሰው ከማሰናከያ ድንጋይ ራሱን ሊያድን ይገባል:: ይህ ደግሞ እንዲህ /ማሰናከያ ድንጋይ/ የሆነውን ሁሉ መረዳት ይጠይቃል:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም «ቀኝ ዓይንህ ብታሰናክልህ አውጥተህ ካንተ ጣላት...» በማለት ተናግሯል:: ማቴ. ፭፥፳፱ ጻድቁ ዮሴፍም እንዲህ ዐይነት የመሰናከያ ድንጋይ ገጥሞታል:: «... እንዴት ይህን ትልቅ ክፉ ነገር አደርጋለሁ? በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ኃጢአት እሠራለሁ» በማለት ግን አልፎታል:: ዘፍ. ፴፱፥፱ በዚህም ዮሴፍ ኃጢአት /ታላቅ ዐመፅ/ በማለት የገለጸውን ሥራ አወገዘ እንጂ ሴቲቱን አልኮነነም፤ በሚወጋ ቃልም አልገለጻትም:: በሥራና በነገር ላይ የመፍረድ መብት አለን:: ይህም በተፈጥሮ የተሰጠን ኃጢአት ያልሆነ ክፉና ደግን የመለየት ባህርይ ነው:: ሰዎችን ግን አንኮንንም::

ሁሉም ትዕዛዛት ግን በሰዎች ምግባር ላይ ብቻ ተመሥርተን የማሰናከያ ድንጋይን እንድናስወግድ የተሰጡ አይደሉም:: የማሰ ናከያ ድንጋዮች በሰው ምግባር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በሃይማ ኖቱ፣ በሃይማኖት ትምህርቱ፣ በሥርዓት ጉዳዮች ሁሉ ውስጥ ሊታዩ ይችላሉ:: ለዚህም የሚቀጥለውን ክፍል እንመልከት::

፬. በኑፋቄና በተለዩ መንገዶች ላይ መፍረድ

በፍቅር ሥራና ትምህርቱ የሚታወቀው ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ «ማንም ወደ እናንተ ቢመጣ ይህንንም ትምህርት ባያመጣ በቤታችሁ አትቀበሉት፣ ሰላምም አትበሉት፣ ሰላም የሚለው ሰው በክፉ ሥራው ይካፈላል» ይላል:: ፪ ዮሐ. ፩+፲

ታዲያ መናፍቃንን የማንቀበል፣ ያልተቀበለም፣ ሰላምም ያላለን ሰው በሌሎች ላይ የመፍረድ ኃጢአትን ሠራ ልንለው እንችላለን? በእርግጠኝነት አይደለም:: ይልቅስ እነርሱን ሰላም በማለቱ ኃጢአትን ሠራ ልንለው እንችል ይሆናል እንጂ:: መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ «በእግራቸው እንዳይረ ግጡት፣ ተመልሰውም እንዳይነክሱአችሁ፣ የተቀደሰውን ለውሾች አትስጡ፣ ዕንቁዎቻችሁንም በእርያዎች ፊት አትጣሉ ይላል::» ማቴ. ፯+፮

እንዲህ መሆናቸውን ቀድመን የማንረዳ ከሆነ ይህን ትዕዛዝ ልንፈጽም እንዴት እንችላለን? ያለዚህ ዕውቀት ትዕዛዙን ልናከብር አንችልም:: ጌታ አሁንም ደግሞ እንዲህ ይላል «የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችሁ በውስጣቸው ግን ነጣቂዎች ተኩላዎች ተጠንቀቁ» ማቴ. ፯+፲፭ ሐሰተኞችን ማወቅ፣ በእነ ርሱ ላይ እንደመፍረድ ተደርጐ ሊተረጐም ቢችልም እንኳን በውሸተኛነት ላይ መፍረድ ኃጢአት አይደለም:: ምክንያቱም መንፈሳዊ ሰው ራሱን መጠበቅ፣ በሐዋርያት ትዕዛዝ መሠረትም መናፍስትን መለየት ይኖርበታል:: ፩ ዮሐ. ፬+፩ ሀመፀኞችን ማወቅ፣ ነጣቂ ተኩላ ሆነው ነገር ግን የበግ ለምድ ለብሰው እንደመጡ ማወቅና ማሳወቅ ስሕተት ሳይሆን ጥበብ ነው::

መንፈሳዊ መሆን ማለት የነጣቂ ተኩላዎችን የሐሰት ሥራ እንዳያይ፣ እንዳያውቅም ሆኖ ዓይኑን ከልሎ የሚራመድ ሰው መሆን ማለት አይደለም:: መጻሕፍት እንዲህ ይላሉ:: «የጠቢቡ ዓይኖች በራሱ ላይ ናቸው ሰነፍ ግን በጨለማ ይሄዳል» መክ. ፪+፲፬ በጨለማ መጓዝ ትሩፋት ሊሆን ይችላልን? አይሆንም:: ካንተ የሚፈለገው ጨለማን እንድትረግም አይደለም፣ ለይተህ ካንተም አስወግደህ በብርሃን እንድትራመድ ነው እንጂ:: ጌታም «ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ» በማለት እንደተናገረው ብርሃንን ከጨለማ መለየት በእውነት ለሚያምን ቀላል ነው::

፭. መምከር፣ መምራት እና ተግሣጽ

ሐዋርያው እንዲህ ይላል «ወንድሞች ሆይ ማንም ከእውነት ቢስት፣ አንዱም ቢመልሰው ኃጢአተኛን ከተሳሳተበት መንገድ የሚመልሰው ነፍሱን ከሞት እንዲያድን የኃጢአትንም ብዛት እንደሸፈነ ይወቅ» ያዕ. ፭+፲፱-፳

አንድ ሰው ከእውነት መሳቱን ግልጽ ማድረግ መኮነን /ማውገዝ/ ሊሆን ይችላል? የአንተ ዓላማ ስሙን ማጥፋት ሳይሆን መመለስ

እስከሆነ ድረስ በፍፁም ሊሆን አይችልም:: ኃጢአተኞችን እን ደዚያ እንደሆኑ ቀድመን ሳናውቅ ልንመራቸው አንችልም:: ባለ መድኃኒት የታማሚውን በሽታ ለይቶ መድኃኒት እንደሚሰጠው ሁሉ ዓላማው ማስተካከል እስከሆነ ድረስ እኛም የአንድን ሰው ወይም የአንድን ቡድን፣ ሌላው ቀርቶ በጥቅል የአንዲት ቤተ - ክርስቲያን የኃጢአት ሥራን እንመረምራለን::

የመምራትና የመምከርን አገልግሎት የሚያጸኑ ብዙ ቃላት እናገኛለን:: ምክርና መምራት ተግሣጽን ሊያሳዩ ይችላሉ:: ይህም ግን ኃጢአት አይደለም:: በመጽሐፍ ምን እንደተጻፈ ተመልከት «ፍሬም ከሌለው ከጨለማ ሥራ ጋር አትተባበሩ፣ ይልቁን ግለጡት እንጅ» ኤፌ. ፭+፲፩ ቃሉ እንደሚያሳየን የጨለማን ሥራ ማወቅ መግለጥም የመፍረድ ኃጢአት አይደለም፣ ትዕዛዛትን የመጠበቅና ደማጽናት በጐ ሥራ ነው እንጂ::

ይህ የተገባ ተግሣጽ መንጋውን ለመጠበቅ የሚደረጉ ማናቸ ውንም አስፈላጊ ነገሮች ያጠቃልላል:: ይህን በተመለከተም ቅዱስ ጳውሎስ ለደቀመዝሙሩ ጢሞቴዎስ «እየታገስህና እያስተማርህ ገሥጽ፣ ምከርም» ብሎታል::» ፪ጢሞ. ፬+፪

መፍረድ ምክርና ተግሣጽ የሚሰጥባቸው መንገዶች መፍረድን የሚያስከትሉ ከሆነም አንድ ሰው የሚፈጽምበትን ሥርዓት ማወቅ አለበት:: ለምሳሌ ንጉሥና ነብዩን ዳዊትን የመከረችው አቢጊያ ንጉሡን ደምን ከማፍሰስ ራሱን ከመበቀልም በጥበብ ጠብቃዋ ለች:: ይህቺ ሴት በተገዢነት መንፈስና ለንጉሡ ውዳሴ በማቅረብ

ጀምራ ስሜቱን በማይጐዳ ብልሀት ችግሩን አሳይታዋለች:: ምንም እንኳን በትሕትና መንገድ ብትቀርብም ግልጽ ግን ነበረች::

አቢጊያ በምክሯ ውስጥ ለዳዊት የሚገባውን ክብር «ጌታዬ» በማለት ስትሰጥ ራሷንም «የአንተ ባሪያ» በማለት ቀርባለች:: ምክሯንም ስለባሏ ድክመት ይቅርታ በመጠየቅ «ጌታዬ ሆይ ይህ ኃጢአት በእኔ ላይ ይሁን፣ እኔ ባሪያህ በጆሮህ ልናገር የባሪያህን ቃል አዳምጥ» እያለች ምግብ በማቅረብ ጀምራለች:: ስሜቱም እንዳይጐዳ ስላቀረበችለት ስጦታ ተናገረች «አሁንም ባሪያህ ወደ ጌታዬ ያመጣችው ይህ መተያያ ጌታዬን ለሚከተሉ ጐል ማሶች ይሰጥ» ፩ሳሙ. ፳፭+፳፯

ከዚህ በኋላ ግን አቢጊያ በምስጋና ጀምራ ለዳዊት ጥፋቱን ሲታሳየው እናያለን «የእግዚአብሔርን ጦርነት ስለምትዋጋ... በዘመንህም ሁሉ ክፋት አይገኝብህም» እንዲሁም ስትል ገሥጻችው «... የጌታዬ ነፍስ በሕያዋን ወገን በአምላክህ በእግዚአብሔር ዘንድ የታሰረች ትሆናለች» በዚህም ርሱን ለመበቀል አልአግ ባብ ደምንም ለማፍሰስ እየሄደ መሆኑን በመንገር አስጠነቀ ቀችው:: ከዚህ ተግባሩም እንዲቆጠብ መከረችው ከዚያም በኋላ አልተሰማውም::

ዳዊትም ተግሣጽ የሆነ የትሑት ሰው ምክርን ተቀበለ፣ ለዚ ህም አመሰገናት:: እንዲህም አላት «ወደ ደም እንዳልሄድ በእጄም በቀል እንዳላደርግ ዛሬ የከለከለኝ አእምሮሽ የተመሰገነ ይሁን፣ ፩ ሳሙ. ፳፭+፴፫ ስጦታዋንም ተቀበለ፣ በሰላምም አሰናበታት፣ ቃሏንም ጠበቀ፣ ተቀበላትም በባሏም ላይ እንዳች ጉዳት

ሳያደርስ አቤቱታዋን ተቀበለ:: ምክርን በትሑት ሰብእናና በጥበብ ማቅረብ እንዴት መልካም ነው!

በዚሁም ምክርና ተግሣጽ ለማቅረብ በምን ሥርዓት መሄድ እንዳለብን ጥቂት ነጥቦችን ማንሣት እንወዳለን::

ሀ/ ምክርን ለማቅረብ መብት ያለን፣ ግዴታም የተጣለብን ብንሆንም በትሑት ሰብእና፣ እና ፍቅር ይሁን

ከኩራት፣ ትዕቢት፣ ንቀት ወይም ቸልተኝነት ጋር የሆነ ተግሣጽ ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም:: አንድን ሰው ለመም ከር ወይም ለመገሥጽ ብትሻ እንዲህ በለው::

«እንዴት እንደምወድህ ታውቃለህ፣ ለአንተም እንዴት እንደ ምጨነቅ ትረዳለህ ነገር ግን በዚህ እና በዚህ ጠባይህ ግን ደስተኛ አይደለሁም:: ይህም እንደሚጐዳህ ይሰማኛል:: ጠባቶች ህም ይህን ዕድል ተጠቅመው ይህንና ያን ሆነ ሊሉህ ይችላሉ:: ስለዚህ ይህን አካሄድ በማስወገድ ይህንና ያንን በማድረግ ተስተካከል» እንዲህ ያለ ምክር ተቀባይነት አለው:: ነገር ግን አንድን ሰው «ያንን እንዴት ልታደርግ ትችላህ? ሕሊናህስ እንዴት ተቀበለው? ይህ ተገቢ ሥራ ነው? ከአንድ ከተከበረ ሰው ይጠበ ቃል? አንተ ይህንና ያንን ነህ::» በማለት በሚያቆስሉ ቃላት መገርሰጥ ተመካሪው በጠላቱ ፊት እንደቆመ እንዲሰማው ማድረግ ነው::

ስለዚህ አንድን ሰው ለማጻን ስትነግረው በቁጣ ከነደደ፣ ቃልህንም ካልተቀበለ ምክርህ ፍቅርና ትሕትና የጐደለው ሊሆን ይችላል:: ምናልባትም ያንተን ምክር ተቀባይነት ባለው መንገድ

ማቅረብ በሚችል በሌላ ሰው ቢስጥ ሊድንበት ከዚያም አልፎ የመከረውን ማመስገን ይጀምርም ይሆናል:: ለዚህም ነው መጽሐፍ «...ቃሉን የሚሰበስብ እሱ ጠቢብ ነው» የሚለው:: ምሳ. ፲፩+፴ ነፍሶችንም የሚሰበስብ ... የማይሰኙ ፍርዶች መሆናቸው መምከርና መምራት ኃጢአት የማይሰኙ ፍርዶች መሆናቸው ... ነው የምንል ከሆነ ደግሞ ሁሉንም ምክር ሳይሆን ፍቅርና ትሕትና የሞሉበትን የጥበብ ምክርን ማለታችን ነው:: ምክርን የምናቀርብበት መንገድ ምክሩን ስሕተት ወይም ... የኃጢአት ፍርድ ወይም ከኃጢአት የጸዳ ፍርድ ሊያደ ርገው ይችላል::

አንድ ሰው ተግሣጽ የሚያደርገውን ሰው ለእርሱ ርሕራሔ ወይም ንቀት እና ፌዝ እንደሆነ በበቂ ሊረዳ ይችላል:: ከተግሣ ጹ ዓላማ ይልቅ በአንድ ተመካሪ ላይ ስሜት የሚፈጥሩት የንግግሩ መንፈስ፣ የድምፅ አወጣጡ ቃላቱ ስሜቱ እና የመሳ ሰሉት ናቸው::

ለ/ ተግሣጻችን በእውነት ላይ ይመሥረት

በእውነታ ላይ ያልተመሠረተ ተግሣጽን በአንድ ምሳሌ እና ስታውስ፣ ይህም በሕልቃና ሚስት በሐና ፊት ሆኖ ኤሊ ያሳየው ነው:: ሐና መካን ነበረች የእርሷ ጣውንት ፍናና ግን ልጆች ነበሯት፣ እጅግም ትመካ ነበርና አስቆጣቻት በዚህም ምክንያት ሐና ወደ ቤተ መቅደስ ሄደች፣ በነፍሷ ምሬት በጽኑ አለቀሰች:: በእግዚ አብሔርም ፊት ሆና ልጅን ከሰጣት በሕይወት ዘመኑ ሁሉ እንዲያገለግል ለጌታ እንዲሰጥ ተሳለች:: በልቧም ትናገር ነበር፣ ድምጿም አይሰማም፣ ከንፈሮቿ ሲንቀሳቀሱ ግን ይታዩ ነበር::

ኤሊ ጠጥታ እንደሰከረች አሰበ፣ መገሠጽ ሥራው እንደሆነ አየ፣ እንዲህም አላት «ስካርሽ እስከ መቼ ነው? የወይን ጠጅሽን ካንቺ አርቂ» ፩ሳሙ.፱+፲፬ በእርግጥ ኤሊ ሓላፊነት እና ሥልጣን የነበረው ካህን ነው:: የመገሠጽና የመፍረድ ሥልጣን ነበረው:: በዚህ ጊዜ ግን ስሕተት ላይ ወድቋል:: ተግሣጹ በእውነት ላይ የተመሠረተ አልነበረም:: በፍርዱና በውግዘቱ ትክክል አልነ በረም:: በዚህ ጊዜ ጨካኝና ጉጂም ነበር:: እርሷ ግን ለካህናቱ እንደሚገባው በትሕትና መለሰችለት:: ለእርሷ መልካምን ቢመ ኝም ስሕተትን ሠርቷል፣ ቀድሞ ለተናገራቸው ቃሎቹም ይቅ ርታን አልጠየቀም::

ከተግሣጽ በፊት በጥንቃቄ የተሞላ ምርመራ ይጠበቅብናል:: ማንንም በሠራው ስሕተት ላየ እርግጠኛ ሳንሆን በሚጐዳ ሁኔታ መገሠጽ አይገባም:: አንድ ሰው ግን የሚገሥጽበት ጉዳይ ተጨ ባጭ እና «ብማያፈሩ የጨለማ ሥራዎች» ውስጥ የሚፈረጅ ጥፋት ከሆነ «ይልቁንም ግለጡት» ተብሎ እንደታዘዘ በዚሁ አግባብ የሚፈጸም ይሆናል::

ሐ/ ተግሣጽ በምሬት የምትሰቃይ ነፍስን አይመለከትም

ሦስቱ የኢዮብ ጓደኞች የምትሰቃይ የኢዮብን ነፍስ ደጋግመው በተግሣጽ በማቁሰላቸው በኃጢአት ውስጥ ወድቀዋል:: በፈጠ ሩት የከሰና የተግሣጽ ሜና እንዲህ እንዲል አነሣሡት «ነፍሴን የምትነዘንዙ በቃልስ የምታደርቁኝ እስከመቼ ነው? ይኸው ስትሰድቡኝ ዐሥር ጊዜ ነው፣ ስታሽከሩኝም አላፈራችሁም» «እናንተ ወዳጆቼ ሆይ ማሩኝ የእግዚአብሔር እጅ መታኛለችና ማሩኝ» ኢዮ. ፲፱+፪፣፫፣፳፩

በአስደናቂ ቃላቶቹም «እኔ ደግሞ እንደ እናንተ እናገር ዘንድ ይቻለኝ ነበር፣ ነፍሳችሁ በነፍሴ ቦታ ቢሆን ኖር እኔ በእናንተ ላይ ቃል ማሳካት ራሴንም በእናንተ ላይ መነቅነቅ በተ ቻለኝ ነበር» በማለት ይናገራቸዋል:: ኢዮ. ፲፮+፬

በምሬት የተዘፈቀች ነፍስ የምትሻው የሚያስደስትና የሚያ ጽናና ቃልን እንጂ የተግሣጽ የምክርም የውግዘትንም ጋጋታ አይደለም:: ተግሣጽህ በእርሱ መከራ መፈንደቅ መስሎ እንዳ ይታይ አንድ ነፍሱ በመራራ ስቃይ ውስጥ ያለችን ሰው ስሕ ተትን የፈጸመ እንኳን ቢሆን ልትገሥጸው አትሞክር፣ ይል ቁንስ የርሕራሔ እና የሚያስደስት ቃልን በመንገር አጽናናው:: በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ተግሣጽህን መሸከም አይችልምና፣ ለዚ ህም ጊዜው አይደለምና ያጋጠመው ስቃይ ለእርሱ ይበቃዋልና:: ወንድሜ ሆይ ጠቢቡ ሰሎሞን ያለውንስ ቃል ታስተውላለህ «ለሁሉም ጊዜ አለው፣ ከሰማይ በታችም ለሆነ ነገር ሁሉ ጊዜ አለው» መክ. ፫+፩

መ/ ምክርና ተግሣጽ የሚሰምሩት በተባለው ጊዜ ሲቀርቡ ብቻ ነው

ከዚህ ነጥብ ጋር የሚስማማ አንድ ታሪክ በአእምሮዬ መጣ:: በአንዱ ቀን አንድ ታዳጊ ልጅ አደገኛ ቢሆንና ጠንካራ የውሃ ግፊት ወዳለበት ቦታ ለመዋኘት ሄደ:: በዚህም ቦታ ሲዋኝ የው ሃው ግፊት ወደ ውስጥ ይስበዋል:: በዚህ ጊዜም ወደ መስጠም ሲቀርብ በጩኸት የእርዳታ ጥሪ ያቀርባል:: በዚያም ቦታ አንድ ሰው ሲያልፍ ስጥሞ እንዳይሞት ከውሃ ጋር የሚታገ ለውን ታዳጊ ልጅ ያየዋል:: ሰውየውም ታዳጊውን «አንተ ልጅ

በዋና ሥልጡን ሳትሆን እንዴት በዚህ አደገኛ ቦታ ለመዋኘት ደፈርክ? በዚህ አደገኛ ቦታ እንደማይዋኝ እንዴት አታውቅም? ይህ እንዴትስ ይቻላል?» ይለዋል:: ያን ጠንካራ የውሃ ግፊት እየታለገ ያለ ታዳጊም እንዲህ ይመልስለታል፦ «ጌታዬ ሆይ አሁን አድነኝ ኋላ ትገሥጸኛለህና»:: በእርግጥም ኋጥአን የሚገሥጻቸው ሳይሆን የሚያድናቸው ብቻ የሚፈልጉባቸው ብዙ ጊዜ ያት አሉ:: ተግሣጽ ጊዜ አለው፤ በደረጃም ቀዳሚ ሊሆን የማይገባበት ጊዜ ሊኖር ይችላል:: ወንድሜ ሆይ በፍቅር በማገዝና በሌሎች አስፈላጊ በሆኑ መንገዶች ሁሉ ጀምር፤ ተግሣጹንም ለሚገባው ጊዜ ቅጠር:: ያ ኃጢአተኛ ምናልባትም በከባድ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ በጽናት ራሱን እየወቀሰ ይሆናልና ተጨማሪ ተግሣጽ አያሻውም::

በጠፋው ልጅ ታሪክ ውስጥ ሩሕሩሑን አባት አላስተዋልከም? ልጁን እንዳችም የተግሣጽን ቃል አልተናገረውም፤ ይልቁንስ ልጁ በተመለሰ አባቱም ባየው ጊዜ፤ ራራለት፤ ተደሰተም፤ ሮጦም፤ በአንገቱም ላይ ተጠምጥሞ ሳመው:: በተጨማሪም አባቱ የመረጠውን /ያማረውን/ እንዲለብስ፤ ፍሪዳም እንዲጣል አዘዘ:: ሉቃ. ፲፭፥፲፮-፳፫ ይህ የተመረጠ የደስታ ጊዜ እንጂ የተግሣጽ አይደለምና:: ተግሣጽና ምክርም የኃጢአት ፍርድ የማይሆኑትም በሚገባው ጊዜ እና ሁኔታ ውስጥ ሲቀርቡ ብቻ ነው:: ካልሆነ ግን ተግሣጽ ማቁሰል፤ ማስደብ፤ ማውገዝ ወደ መሆን ይለወጣል:: ይህ ደግሞ የከፋ ውጤትን ያስከትላል::

ሠ/ አንዳንዴ ተግሣጽህ የሚሰምረው አንተና ታራሚው ብቻችሁን ስትከውኑት ብቻ ነው::

በዚህ ሁኔታ ኃጢአትን ያደረገው ታራሚ በሰዎች ፊት ኃፍረት አይሰማውምና፤ ኃጢአቱንም በአደባባይ አትገልጥምና ተግሣጽህን ይቀበል ይሆናል:: በዚህ አጋጣሚ ኃጢአቱን ሊያ ምን ስለ እርሱም ይቅርታን ሊጠይቅ ይችላል:: ያየው አንድስ እንኳ የለምና፤ የራሱም ክብር በሰዎች ፊት ተጠብቋልና ተግሣጽህን ሊቀበል ይችላል:: ይህ በምስጢር የሚፈጸም ምክርና ተቀባይነት ያለው ተግሣጽ ነው:: ያ ተግሣፅ በሰዎች ፊት ከሆነ፣ የሠራውን ክፋት ሊክድ፣ ራሱንም ሊከለክል፣ ሊከራከርም ይገደድ ይሆናል::

በሌሎች ፊት ሆነህ ምንም እንኳ በፍቅርና በየዋህነት ተሞልተህ ብትገሥጸው ሥራውን በሌሎች ፊት ስለ መግለጥህ በሐሰት ራሱን ለመከላከል ይቆማልና:: በዚህ ጊዜም ያን እንዳያደርግ የሚያስገድድ ማስናከያን አምጥተሃል፤ በአደባባይ ገልጠኸዋልና፤ አዋርደኸዋል፤ አቁስለኸዋልና:: ምናልባትም በሰው ፊት ስላልከው ነገር ላያፍር ይችላል:: እንደውም አጉልቶ «አዎን አድርጌዋለሁ» ሊል ይችላል:: በልቡ ጸጸት ውስጥ ከማለፍ ይልቅ በጽናት ሊቃወምህ፤ ሊከላከልም ይነሣል:: በሌሎች ፊት ደካማ ሆኖ ላለመታየት ይቃወማል::

ነገር ግን ሐዋርያው ኃጢአታቸው ለሁሉ የተገለጠ በሥራቸውም የቤተ ክርስቲያንን ደኅንነት ዋጋና እና መንፈሳዊነት ስለሚያዛቡ «ሌሎች ደግሞ እንዲፈሩ ኃጢአት የሚሠሩትን በሁሉ ፊት ገሥጻቸው::» ይላል ፩ጢሞ. ፭፥፳:: ለምሳሌ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቢጮኹ ወይም የማይገባና የተለየን ነገር ቢናገሩ ሌሎችም እንዲፈሩ በአደባባይ ለሠሩት ክፋት በአደባባይ ሊገሠጹ ይገባቸዋል:: እንዲህ ለሚያደርጉት በአንተና በእነርሱ መካከል ብቻ ብትገሥጽ ተገቢ አይደለም::

፮ ሂስ

አንድ ሰው በአንድ መጽሔት፣ ትረካ፣ ጽሑፍ፣ ቴአትር ወይም ስፖርት ውስጥ እንደ ሀያሲ ሆኖ ሊሠራ ይችላል:: ታዲያ ይህ ሰው በሌሎች በመፍረድ ኃጢአት ውስጥ ይጥለኛል በማለት የሀያሲነት ሥራውን መተው ይኖርበታል?

ይህ ሰው ሥራውን በአግባቡና በመንፈሳዊ መንገድ ካሉት የሥሯው ሳይንሳዊ መሠረቶች በመነሣት ሊያከናውን እንጂ ሊለቅ አይገባውም:: ሌሎችን ግን ማጥፋትም መጉዳትም የለበትም:: ስለዚህም በሂስና በፍርድ መካከል ልዩነት እንዳለ እንረዳለን:: ዋናውም ልዩነት ሂስ ጉዳይ ሥራ ተኮር ሲሆን ፍርድ ግን ሰው ተኮር መሆኑ ላይ ነው:: ሂሱ ጉዳዩን /ሥራውን/ ያብጠለጥላል ይተነትናል፤ ብሎም በትክክለኛ /ተመጣጣኝ/ መንገድ ጠንካራና ደካማ የሥራውን ጐኖች በማንሣት ይመዝናል:: ከዚያም የስኬትና የውድቀቱን ምክንያቶች ከየማዕዘኑ ያንፀባርቃል:: ሂስ ለሥራው መልካምነት የሚያስፈልጉ ተገቢ መንገዶችንም በአስ ተያየት ያቀርባል::

በመሆኑም ሂስ በማኅበራዊ እና የቤተ ክርስቲያን ኑሮአችን በተግባሮቻችንም ሁሉ ውስጥ የሚያስፈልግ የምዘና ሂደት ነው:: ሂስ ጉድለቶቻችንን ነቅሶ በማውጣት መልካም ጐኖቻችንን በማጎልፀግ የተሻለ የስኬት ደረጃ እንድንጨብጥ ዓላማ አድርገን የምንሠራበት መንገድ ነው:: ስለዚህም አንድ ሰው አዘውትሮ ሥራውን ይገመግማል:: ይህም ግለ-ሂስ በመባል ይታወቃል:: በመንፈሳውያን ዘንድ በራስ መፍረድ /ራስን መውቀስ/ የምንለው ነው::

ሂስ የራሱ ሕግ፣ ቀመር እና ብልሃት ያለው ሳይንስ ነው:: የማይደርስበት የራሱም ወሰን አለው፤ ይህ ካልሆነ ደግሞ ሂስ ሳይሆን ተገቢ ያልሆነ ትችት ነው:: በተለይ ደካማ ጐኖችን ደጋግሞ በማንሣት የምንገመግም ከሆነ ሂስ ሳይሆን ማጥቃት ነው:: እንዲህም የሚያደርግ ትክክለኛ ሀያሲ አይደለም::

ሂስ የተለያየ ዓይነትና ደረጃ አለው:: ልዝብ፣ ጠንካራ እና ተአማኒነት ያለው ሲሆን የትኛው ተገቢነትና ተቀባይነት ሊኖረው ይችላል? እንዲሁም ደግሞ የሰላ እና ጐጂ የሆነ ሂስም አለ:: እያንዳንዱ ሀያሲ የራሱ እና የተለየ የሂስ መንገድና መጠቀሚያ ቃላት አሉት:: ትክክለኛ ሀያሲ ግን በጣም ትክክለኛ በሆኑ መሥፈርቶች ላይ ተመሥርቶ ቃላትን የሚመርጥ ነው:: ምናልባትም አንተ ሀያሲ ከሆንህ የቱን ዓይነት እንደሆንክ ራስህን እይ በሂስ አቀራረብህ ትክክለኛና ተጨባጭ ሆነህ ተገኝ እንጂ ጐጂ አትሁን::

አንዳንድ ሀያሲያን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ አንድን መጽሐፍ ሊገመግሙ ይችላሉ:: ይህ ሂስ አስፈላጊና ለሥራው የተሟላ መሆን የሚገባ ይሆናል:: ሌላው ደግሞ አንድን መጽሐፍ

የሚገባው ከሆነ ሂሱን በአድናቆት ጀምሮ በአድናቆት ሊፈጽመ ይችላል::

ሂስ ጥንቃቄ የተሞላበት ጥናት ይፈልጋል:: ሂስ በሚተቹት ጉዳይ ዙሪያ ሰፊ ዕውቀት መያዝን ይፈልጋል:: በተጨማሪም የሀያሲያን ጥበብና ሕግ ዕውቀትንም ይሻል:: ማንም የሀያሲነት ደረጃን፣ ስም፣ ክብርና ተአማኒነትን ከኅብረተሰቡ እንዲሁ ማግኘት አይችልም::

የትክክለኛ ሀያሲ ትችት ለአንባቢና ሥራውን ለሚያስገመግመው አካል እጅግ ጠቃሚ ነው:: እንዲህ ዓይነቱ ሂስ ሳይንስ ሥነ-ጽሑፍና ጥበብን ገንብቷል፤ አምጥቷል::

ጌታ እግዚአብሔር በነቢዩ ኢሳይያስ መጽሐፍ ውስጥ እንዲህ ይላል «ክፉውን መልካም መልካሙን ክፉ ለሚሉ፣ ጨለማውን ብርሃን ብርሃኑንም ጨለማ ለሚያደርጉ፣ ጣፋጩን መራራ መራራውንም ጣፋጭ ለሚያደርጉ ወዮላቸው» ኢሳ. ፭፥፳ ወንድሜ ሆይ ለምስክርነት ፍርድ ቤት ውስጥ በመጥሪያ ብትጠራ በደለኛውን ንጹህ ለማለት የሐሰትን ቃል በመናገር ትመሰክራለህን? እውነትንስ ብትናገር በሌሎች የመፍረድ ኃጢአት ውስጥ ወድቀሃልን? እግዚአብሔር ይህን አላለም:: ኃጢአትስ በደለኛውን ንጹህ በማድረግ ተናግሮ ሐሰተኛ ምስክር ሆኖ መገኘት ነው::

በተመሳሳይ በግል ምክንያቶችህ እውነትን መመስከር ካልቻልክ ደግሞ ቢያንስ ዝም በል:: ይህ በደለኛውን ንጹህ ከማድረግ ሌሎችንም ከመዋሸት ይሻላልና::

፯ በራስ ላይ መፍረድ

በራስ መፍረድ ወደ ትሕትና እና ንጽህና የሚያደርስ የትሩፋት /የጽድቅ/ ሥራ ነው:: ቅዱስ መቃርዮስ «ወንድሜ ሆይ ሳይፈረድብህ በፊት በራስህ ፍረድ» እንዳለ ተገቢ ፍርድን የመቀበል ሁኔታ ነው::

ቅዱስ እንጦንስም «እኛ በራሳችን ላይ ብንፈርድ ፈራጃችን /ዳኛው/ በእኛ ይደሰታል» በማለት ተናግሯል:: እንዲሁም ራሱን ለማስተካከል ራሱን የሚገሥጽና በራሱም ላይ የሚፈርድ ያ ሰው በሌሎች ላይ ለመፍረድ የሚያነሣሣ ውስጣዊ ማንነት አይኖረውም፤ ምክንያቱም እንደሌሎች ምናልባትም ከእነርሱ በባሰ የኃጢአተኛነት ስሜት አድሮበታልና:: በራስ መፍረድ ሰውን በሌሎች ከመፍረድ ይጠብቀዋል:: ቅዱስ ሙሴ ጸሊም ደግሞ ስለራሱ ኃጢአት የሚጨነቅ ማንም ስለሌሎች ኃጢአት የሚናገርበት ጊዜ እስከሚያጣ ወደ ራሱ ልብ እንደሚገባ ሲናገር «የራሱን የሞተ ዘመድ ትቶ ስለ ባልንጀራው /ጐረቤቱ/ የሞተ ዘመድ ሊያለቅስ የሚሄድ እሱ ማነው?» ይለናል::

፰ ኃጢአተኛውን የሚያጸድቅ ማነው?

አንዳንዴ ሰዎች በሌሎች በመፍረድ ኃጢአት እንዳይነካኩ በመስጋት ዐመፀኛ ሆኖ ያገኙትን እንኳን ሳይቀር ሁሉን ያጸድቃሉ:: እነዚህ ወገኖች የቅዱሳት መጻሕፍትን ቃል ሊሰሙ ይገባል::

«ኃጥኡን የሚያጸድቅና በጻድቁ ላይ የሚፈርድ ሁለቱ በእግዚአብሔር ዘንድ አጸያፊዎች ናቸው» ምሳ. ፲፯፥፲፭ እንዲሁም

የተባለበት ምክንያት ሁለቱም ከእውነት ርቀዋል፤ ሐሰት ንም ተናግረዋልና ነው:: ወንድሜ ሆይ «ኃጥኡን የሚያጸድቅና» የሚለው ቃል ቀድሞ መቅረቡን አስተዋልክ:: ኃጥኡን ባጸደቅህ ጊዜ ጻድቅና እና ሩህሩህ ልብ የያዝክ አይምሰልህ፤ የበደል በደል ነው፤ ኃጢአትም ኃጢአት ነው:: ኃጢአትን ያደረጋት ሰው ባህርይዋን በማወቅም፣ ባለማወቅም፣ በድክመት፣ በፍርሃት ወይ በግፊት ከክስ አያመልጥም:: አንተ ልታጸድቀው ወይም እንዳል ሠራ ልትሟገትለት አትችልም::

አንዳንዴ ኃጥኡን ጻድቅ የሚያደርግ ሰው፣ያየና የሰማ ለባሰ ለፍርድ ኃጢአት ሊነቃቃ ይችላል:: ይህ ሰው ኃጥኡን ጻድቅ ሲል የሰሙትን ሁሉ ኃጢአት ፈጻሚውን ስለ ሠራው ክፋት በሐሰት በመከላከሉ ሊያወግዙት፣ ክፉ ሥራውን ደግ ለማለት ያቀረበውን ማስተባበያ ሁሉ ለማፍረስ የሚመጥን ምላሽ በመስጠት በጽኑ ሊኮንኑት ይገደዳሉ:: በዚሁ ሁኔታ ኃጥኡን ጻድቅ ለማድረግ ለተነሣው ሰው ሌሎች ደግሞ ምላሽ ለመስጠት ሲጥሩ በአንጻሩ ወደ ሌላ ኃጢአት እንዲገቡ ምክንያት ሆኗል::

በተጨማሪም ኃጥኡን ጻድቅ ማለትን ያበረታታል:: እንዲህ ያለ ክፋትን ሠርተው ንጹህ ከተባሉ በኋላ ጸጸት የማይሰማቸው፣ በክፋታቸውም የሚቀጥሉ፣ የእነርሱንም አርአያ የሚከተሉ ሌሎችም የሠሩትን ክፋት ንጹህ ተደርጉ እንደሚቆጠርላቸው ማሰብ ከጀመሩ ራሳቸው በዳዮች ይሆናሉ::

ታላቁ ቅዱስ ባስልዮስም «በደለኛውን ንጹህ አድርገው ለሚከራከሩ ለእነርሱ ቅጣታቸው ምን ይሆን?» ቅዱስ ባስልዮስ በወንጌል

ሌሎችን የሚያስናክሉ ሰዎች ከሚቀበሉት ከባድ ፍርድ በባሰ እነዚህ ወገኖች እንደሚያገኛቸው አስቧል:: ማቴ. ፲፰፥፮-፱ ምክንያቱም ስለኃጢአተኛው የክፋት ሥራ የሚከላከሉለት ከንስሐም ይከለክሉታልና:: ኃጢአተኛውም በኃጢአት ሥራው ይጸናል:: ዐመፃውንም ለሌሎች ያጋባል:: እንዲህ ያለውን አካሄድ ካላወገዘን ስለክፋት ሥራቸው ከተከላከልን፣ ጻድቅም ካደረግናቸው ሌሎች እንዲህ እንዲያደርጉ ስለሚነሣሡ የተባለው በእርግጥም እውነት ነው::

በዚህ አጋጣሚ ግን አንድ መልስን የሚሻ ጥያቄ እንደ ሚኖር አስባለሁ:: ታዲያ ለምንድነው ቅዱሳን የኃጥአንን ሥራ እንድንሰውር የሚመክሩን? ለዚህ መልስ ለመስጠት ግን ቀድመን «መሰወር» የሚለውን ቃል ምንነት መረዳት ይኖርብናል:: በዚህ ጊዜ «መሰወር» ማለት መንፈሳዊ ሚዛናችንን የሚያሳጣ፣ ክፉውን መልካም አድርጉ የሚያስጠራ አይደለም:: ምክንያቱም መጻሕፍት «ጥሩውን መልካም መል ካሙን ክፉ የሚሉ.., ጣፋጩንም መራራ፣ መራራውንም ጣፋጭ ለሚያደርጉ ወዮላቸው» ይሉናልና:: ኢሳ. ፭፥፳ በዚህ ጊዜ ኃጢአትን መሰወር በሥራው ላይ የተመሠረተ ንግግር ሳይሆን ኃጢአት በተሠራበት አካባቢያዊ ሁኔታ ላይ ተንተርሰን የምንናገረው ነው:: ኃጢአትንስ ስለመሰወር በሞት የተለዩንን በጸሎተ ፍትሀት ስናስብ /በዓለም ኗሪ ሥጋ ለባሽም ነበሩና... ለአንዲት ቀን ብቻ እንኳን በዚህ ዓለም በሕይወት ቢኖሩ ማንም ከበደል ንጹህ አይደለምና../ በማለት የሰውን የባህርይ ድካም በዓለም ያለውን የያሩን ጽናት በማሰብ

የባልንጀራን ኃጢአት እንሰውራለን:: ይህም በዲያብሎስ ተንኮል የሐሰት ሥራ እና የማታለያ ጥበብ ስለመታለላቸው የሚቀርብ የይቅርታ ጥያቄ ነው:: ሳያውቁ በድለ ዋልና ይቅርታን ልንጠይቅላቸው እንችላለን:: መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም «የሚሠሩትን አያውቁምና ይቅር በላቸው» በማለት የሰቃዮቹን ኃጢአት ሰውሯልና:: ሉቃ.፳፫፥፴፬ ቅዱስ ጳውሎስም «አውቀውትስ ቢሆን የክብርን ጌታ ባልሰቀሉት ነበር» እያለ ጌታውን ሲመስል እናያለን:: ፩ቆሮ. ፪፥፰

በእርግጥ በፈተና ውስጥ ነበርና፣ ዕንቅፋት ይመታልና፣ በአጋንንት ተገፋፍቷልና፣ ራሱን መግዛት አልቻለምና፣ ኃጢአትን ሊያደርጋት ተነሣሣ ብለን በደልን ልንሰውር እንችላለን:: ነገር ግን የሠራውን በደል መካድ፣ ወይም በደልን እንዳልሆነ አድርጎ ማወጅ አንችልም:: መናገር የምንችለው በደልን የሠራበትን ሁኔታ ነው:: ብልህ ጠበቃ ተከሳሹ ድርጊቱን የፈጸመበት ስነልቦናዊ ሁኔታ፣ አእምሯዊ እና ስነ-ምግባራዊ ሁኔታዎች እንዲታይለት ይጠይቃል እንጂ ተከሳሹ የቀረበበትን ተጨባጭ ክሶች አይክድም::

በዚህ ጊዜ ጠበቃው በሠራው በደል ከምሕረት ሌላ የሚያስፈልገውን የበደል ማቃለያን የመጠየቅ እንጂ የሠራውን በደል ፍፁም የመካድ ዓላማ የለውም:: እኛም ሁላችን ስለኃጥአን «ሁላችን ለውድቀት የተሰጠን ነንና ለኃጢአትም የተሰጠን ነንና» በማለት ከባቴ አበሳ ልንሆን እንችላለን:: ኃጢአትን ግን ጽድቅ ልናደርጋት አንችልም::

አንዳንድ ሰዎች ደግሞ የታላላቅ ሰዎችን በደል ለመከላከል «ይህ የሰው ባህርይ ነው ሰው ሆኖ የማይበድል የለም» ይላሉ:: ወንድሜ ሆይ መጽሐፍ ቅዱስ ነቢዩ ኤልያስን ስለሚመስሉ ታላላቅ ሰዎች የሚለውን ታስተውላለህ:: «ኤልያስ እንደ እኛ ሰው ነበር...»ያዕ. ፭፥፲፯

ይህ ነቢይ ዝናብ እንዳይጥል /እንዳይምር/ አጥብቆ ጸለየ፤ በምድርም ላይ ሦስት ዓመት ከስድስት ወር ዝናብ አልነበረም:: እንዲሁም ደግሞ ጸለየ ሰማይም ዝናብን ሰጠ:: ይሁን እንጂ ኤልያስ እንደ እኛ ሰው ነበር:: የሰው የራሱ ዝንባሌ እንጂ የተፈጥሮው ባህርይ ለኃጢአት የተዘጋጀ አይደለም::

በዚህ መንገድ ታላላቅ /የተከበሩ/ ሰዎችን የሚያወድሱ ኃጢአተኛውን ጻድቅ በማድረግ ኃጢአት ውስጥ ይወድቃሉ:: እንዲህ ያሉት ምን በደላቸው የከፋ ቢሆን ከእውነት አፈንግጠው ክፋታቸውን ደግ ለማስመሰል ይጥራሉ:: በእንዲህ ዓይነት በደልን ሸፍኖ በሚቀርብላቸው መወድስ ብዙ ታላላቅ ሰዎች በስህተት ወድቀዋል፤ ያለፀፀትም በበደላቸው ጸንተዋል:: በሚገርም ሁኔታ ደግሞ በውድቀታቸው ሊኮሩም ይችላሉ:: እነዚህ ኃጢአተኛውን ጻድቅ የሚያስመስሉ አወዳሽና አጉንባሾች ለእነዚህ ታላላቅ ሰዎች በኃጢአት እንዲፀኑ፣ኃጢአትን ሲሳተፏት እንዲኖሩ የስሕተት መመሪያም እንዲያነግቡ ጉልበት ሰጥተዋቸዋል::

በመሆኑም በተገለጠ የኃጢአት ሥራ ፊት ዝምታን የሚመርጡ፣ በበደል የጸናውንም ከእነርሱ የሚያርቁ ቅዱስ ጳውሎስ የቆሮንቶስ ሰዎችን እንዳወገዘ የተወገዙ ከሆነ የኃጢአት ሥራን

ስለሚከለከሉ፣ ጽድቅ አድርገውም ስለሚያስቡና ስለሚያሳስቡ ወገኖች ምን ልንል እንችላለን? ያለጥርጥር ፍርዳቸው የከፋ ነው::

፱ ፍርድን ኃጢአት የማያደርጉ ሁኔታዎች

ሀ. ሓላፊነት ካለበት አካል ከመጣ /ከመነጨ/

ይህ ቀደም ብለን የገለጽነው ሲሆን በየትኛውም ፍርድን በምትሰጥበት ጊዜ ሁሉ ራስክን እንዲህ ብለህ ጠይቅ /«እኔን ፈራጅ ያደረገኝ ማነው»/ ሉቃ. ፲፪፥፲፬ ወይም እኔን መምህር አድርጎ ያስቀመጠኝ ማነው? በእርግጥም ሓላፊነት እንዳለብህ ለራስህ መልስ ካገኘህ ልትፈርድ ትችላለህ::

ለ. ፍርድህ በዕውቀት ላይ የተመሠረተ ሲሆን

እግዚአብሔር «የምድር ሁሉ ፈራጅ» ነው:: ዘፍ. ፲፰፥፳፭ ምክንያቱም ከመለኮታዊ ሥልጣኑ ባሻገር በባህርይ ዕውቀቱ የተመሠረተ የእውነት ፍርድ ባለቤት /ፈታሒ በጽድቅ/ ነውና:: ሁሉን ያውቃል:: ልባችንን ይመረምራል:: ሐሳባችንን ያነባል፤ በአንድ ሰው ስሜት እና ፍላጎት ውስጥ የሆነውን ይረዳል:: የተሠራና የተገለጠውን ያውቃል::

የምድር ፈራጆች ግን ፖሊስ፣ አቃቤ ሕግ፣ ፍርድ ቤት መረጃን በመመርመር፣ ምስክሮችን በመጠየቅ በመስማት፣ የተከሳሹን መከላከያ ለመስማት ሙሉ ዕድል በመስጠት የተደረገን ምርመራ ተንተርሰው ይፈርዳሉ::

ወንድሜ ሆይ አንተስ? እንድትፈርድ ምን ዕውቀት ይዘሃል? አንድ ሰው የሌሎችን ሐሜት እና ጥርጣሬ መሠረት

አድርጎ፣ ሳያጣራ፣ ድርጊቱ ስለተፈጸመበት ሁኔታ፣ መነሻ እና ምክንያት ሳያውቅ በሌሎች ፈርዶ ይሆናል:: ምናልባት ይህ ሰው እውነታውን ሁሉ የሚረዳበት ዕድል ቢኖረው ስለፍርዱ ሊፀፀት፣ ይቅርታም ሊጠይቅ ይችላል::

ስለዚህ በአንድ ሰው ድርጊት ላይ ሳትመረምር፣ ሳታረጋግጥ ለእርሱም ስለ ሥራው የሚናገርበት ዕድል ሳትሰጠው ልትፈርድበት አይገባም:: እግዚአብሔር ሳይፈርድበት /ሳይገልጠው/ ፈጥኖ በሌላው መፍረድ ተገቢ አይደለም:: «ጊዜው ሳይደርስ እንዲት አትፍረዱ» ያለው የሐዋርያው ቃልም እውነት ነው:: ፩ ቆሮ. ፬፥፭ ይሄው ሐዋርያ አስከትሎም እንዲህ በማለት ይመክረናል «ስለ ዚህም በጨለማ የተሰወረውን ደግሞ ወደ ብርሃን የሚያወጣ የልብን ምክር የሚገልጥ ጊዜው ሳይደርስ አንዳች አትፍረዱ፤ በዚያን ጊዜ ለእየንዳንዱ ምስጋናው ከእግዚአብሔር ዘንድ ይሆናል» ፩ ቆሮ. ፬፥፭

፲ ያለጊዜው አትፍረድ

ቅዱስ አውግስጢኖስ ይህን ቃል ሲተረጉም ሐዋርያው «የአንዳንድ ሰዎች ኃጢአት የተገለጠ ነው:: ፍርድንም ያስከትላል» ያለውን ጠቅሶ የተገለጡ /የሚመሰከርባቸው ኃጢአቶች አሉ ይለናል:: ፩ጢሞ. ፭፥፳፬ በእነዚህ በደሎች የሚሰጥ ፍርድ ሁሉ አይታለፍም:: በአንፃሩ ግን ግልጽ ለሆኑ ነገሮች እግዚአብሔር የልብን ምክር ሲያወጣ በጨለማም የተሠወረውን ነገር ወደ

ብርሃን ሲያመጣ ይገለጣሉ:: «ያለጊዜው አትፍረድ» የሚለውም ስለእነዚህ ጉዳዮች የተጻፈ ነው::

አንዳንድ ጠባይ ስሕተት መስሉ ሊታዩን ይችላል:: ነገር ግን እግዚአብሔር የልብን ምክር በገለጠ ጊዜ ሆኖ እናገኘዋለን:: በተቃራኒው ደግሞ አንዳንድ ባህርይ ትክክል መስሉ ሊታየን ይችላል:: ነገር ግን እግዚአብሔር የልብን ምክር በገለጠ ጊዜ የማይገባ ሆኖ እናገኘዋለን::

ለዚህም ነው በአንዳንድ ጉዳዮች ጌታ እግዚአብሔር የተሰወረውን እስኪገልጥ ያለ ጊዜው መፍረድ የሌለብህ:: አንተ ግን በተገለጡና በተመሰከረባቸው ጉዳዮች ፍረድ:: ያልተገለጠውን ግን እንዲገልጠው ለብርሃን አምላክ ስጥ::

፲፩ ትክክለኛ ፍርድ

ታላቁ ቅዱስ ባስልዮስ «እንዳይፈረድብህ አትፍረድ» ስለሚለው የጌታ ቃል ተጠይቆ ሲመልስ እንዲህ ብሎ ነበር «ጌታ በሌላ ክፍል፣ «ፍርድን አታጣምም ፊት አይተህ አታድላ... በሕይወት ትኖር ዘንድ... እውነተኛውን ፍርድ ተከተል» ብሎናል» በማለት ነበር:: ዘዳ. ፲፮፥፲፱-፳ ማቴ. ፯፥፩

በፍርዳችን አድልዎ ማሳየት የለብንም:: በፍርዳችንም ትክክለኛ ጻድቅ ልንሆን ይገባል:: ይህ ቅዱስ ሰው እንዳስተማረን እግዚአብሔር እንዳንፈርድ አልከለከለንም፤ ትክክለኛነትን እንድንከተል፣ በጊዜው እንድንፈጽም፣ በሁሉ ሳይሆን በተገለጡት እንድንፈርድ አዘዘን እንጂ::

ነገር ግን ሰው በፈቃዱ የሚያደርጋቸው መብላትና መጠጣትን የመሰለ ያልተከለከሉ ነገሮች አሉ::* ቅዱስ ጳውሎስ ስለ እነዚህ ነገሮች ለይቶ እንዲህ ይለናል «አንተም ወንድምህ ላይ ስለምን ትፈርዳለህ?... እንግዲህ ከዛሬ ጀምሮ እርስ በእርሳችን አንፈራረድ» ሮሜ. ፲፬፥፲-፲፫ እግዚአብሔርን በማያስደስቱ ነገሮች ላይ የማይፈርዱ ግን እራሳቸው የተፈረደባቸው ናቸው:: ክፉትን የሚያወግዝ በኃጢአተኛም የማይፈርድ ሕዝብ የተፈረደበት ይሆናል:: ሐዋርያው «ክፉውን ከመካከላችሁ አውጡት» ይለናል:: በአንድ ሰው ኃጢአት ምክንያት የእግዚአብሔር ቁጣ በሕዝቡ ላይ ያርፋልና:: በአንድ ሰው ኃጢአት የመጣው የእግዚአብሔር ቁጣ ከሕዝቡ እንዲርቅ በኃጢአቱ የጸናውን ዐመፀኛ የማራቅ፣ ራሱንም የማንጻት ሓላፊነት አለበት::

ወንድሜ ሆይ በአንድ በነቢዩ ዮናስ ዐመፅ በመርከቡ የሞሉ ያልበደሉ ተጓዦች ሁሉ ሊሰጥሙ እንደነበር አስተውለሃል:: በኢያሱ ወልደነዌ ዘመንስ የከርሚ ልጅ አካን በሠራው ኃጢአት ምክንያት የእግዚአብሔር ቁጣ በሁሉ ላይ እንደነደደ አስታወስህ:: ኢያ. ፯

ስለዚህ ሕዝብ በበደለኛው ምክንያት እንዳይጠፉ ርኩሰትን ለማስወገድ በኃጢአቱ የፀናውንም ለመለየት መብት አለው:: ይሁን እንጂ ይህ አካሄድ ጥበብን ይጠይቃል:: በእርግጥ ቅዱስ

* [illegible]

ባስልዮስ በተለይ ለእግዚአብሔር መቅናት እንደሚገባን የሚናገሩና የመሳሰሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት የሚፈጸሙበት /የሚደረጉበት/ ጉዳይ ውስን ሊሆን እንደሚችል ይናገራል:: ለምሳሌ ነቢዩ «ጠላቶቼ ቃልህን ረስተዋልና የቤትህ ቅናት አቃጠለኝ» በማለት የተናገረው ለመንፈሳዊ ቅናት ነው:: መዝ. ፻፲፰፥፻፴፱ አንድ ሰው ይህን ሲያደርግ ግን የጌታን ቃል ያላከበሩትን ያወገዘበት መነሻ መንፈሳዊ ቅናት ወይስ የራስ ተንኮል፣ ጥላቻ ወይስ ክፋት ይህ ግን በመንፈሳዊ ቅናት ላይ የተመሠረተ ከሆነ ፍርዱ ተቀባይነት አለው:: እንዲህ ያለው መንፈሳዊ ቅናትም በእውቀት /መረጃ/ ላይ የተመሠረተ ሊሆን ይገባል:: /ሮሜ. ፲፥፪/

ምዕራፍ ሁለት

ሌሎች የመፍረድ ዓይነቶች

በሌሎች ላይ መፍረድ በአንድ በተወሰነ መንገድ ብቻ የሚገለጽ አይደለም:: በንግግር ብቻ አይደለም:: በሐሰት ወይም በመስማት፣ ወይም በልቦናችን ባሳደርነው ስሜት ወይም በፊት ገጽታ ወይም ደግሞ በአንድ ሰው አጠቃ ላይ እንቅስቃሴ ውስጥ ሊገለጽ ይችላልና::

በሌሎች ላይ መፍረድ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚፈጸም እና የተለየ መልክ ሊኖረው ይችላል:: ከሌሎች ስሜቶች ጋር ከተያያዘ ደግሞ የከፋ ሊሆን ይችላል:: እስቲ የሚቻለውን ያክል እያንዳንዱን በዝርዝር ለማየት እንሞክር::

፩. በሕሊና መፍረድ

በሕሊና መፍረድ ከሚፈርደው ሰው ጋር ብቻ የተያያዘ እና ወደ ውጪ ወጥቶ የማይገለጽ በመሆኑ ቀላል ወይም አነስተኛ ፍርድ ይመስላል:: ይሁን እንጂ ለሌሎች የፍርድ ዓይነቶች ሁሉ መነሻና ምንጭ በመሆኑ አደገኛ ነው:: ስለዚህ ሳያድግ፣ ሌላም ጉዳት ሳያስከትል ወደ ሌሎችም ደረጃዎች ሳይሰፋ በጊዜው መገታት ይኖርበታል::

ምናልባትም በሕሊና መፍረድ ለአንድ ሰው መንፈሳዊ ውጊያም ሆኖ ሊቀርብ ይችላል:: አንድ ሰው ይህን መንፈሳዊ ውጊያ ወደ ኃጢአት ከማደጉ በፊት ሊያጠፋው እና ሊያሸንፈው

ይችላል። ነገር ግን በውስጡ የመጣውን የመፍረድ ሐሳብ እንዲሠለጥንበት ከፈቀደ በእርሱም ካመነበት፣ ከስሜቱም ጋር ከተዋሐደ በውስጡ ተቀብሎታልና የመፍረድ ወይም የማውገዝ ሐሳቡ መንፈሳዊ ጦርነት መሆኑ ይቀራል። አንድ ሰው በሐሳቡ ብቻ ላይረካ ይችላል። ከውስጡ በሌላ መንገድ የሚገለጽ ፍርድን ለመጨመር ይሻ ይሆናል። በተለይ የሚፈርድበት ሰው ቀድሞ የሚጠላውና የዘለፈው ሰው ከሆነ ይሄ ስሜት ይጫነዋል። በዚህ ጊዜ በውስጡ በነበረው፣ አሁንም በቀጠለበት የሌላውን ኃጢአት የማሰብ ሥራ ካልጠገበ በዚህ ሰው ላይ በሐሳቡ ሌሎች የበደል ሥራዎችን ሊፈጽም ሕሊናው ፈጥሮ ያስቃኘዋል። ምናልባትም ያወገዘው ሰው በሌላ ኃጢአትም ሲወድቅ፣ በሰዎች ፊትም ሲጋለጥ፣ እነዚያም ሰዎች አሳፋሪ ኃጢአቱን ለይተው ሲያወጡበት ሲያፍር ወይም ፍርድ ቤት ሲቀርብ ሊታየው ይችላል።

በዚህም ሐሳቦቹ በልብ ውስጥ ያለን የትኛውንም የሰው ክፉ ስሜት እና የሚያስጠላ ሐሳብ የሚያይበቸው ስክሪን ብቻ ሆነዋል።

ሰው ይህ በሌላ የመፍረድ ሐሳብ በሕሊናው እንደመጣ ሊያቆመው ይገባል። የክፉ ደረጃ ከደረሰ ግን መስተካከል ብቻ ሳይሆን ለመንሥኤዎቹ መፍትሄ መስጠት እና በልብ ውስጥ የሚኖረውን ክፉ ስሜት ሁሉ ማስወገድ ያስፈልጋል። ቀይቶ በሕሊና መፍረድ ቦታውን በልቦና ወደ መፍረድ ይለውጣልና። ሕሊና በሰው ላይ በፈረደ ጊዜ ከዚህ ፍርድ ጋር የተያያዘ ውስን ሐሳብን ወደ ልቦና ያደርሳል። ይህ ስሜት በልቦና ውስጥ ከተንሰራፋ ደግሞ ልቦና መልሶ ወደ ሕሊና ያሠራጫል። በዚህም መንገድ እየተመጋገቡ ይህን የማይገባ መንፈስ ያጸኑበታል ማለት ነው።

፪. በንግግር መፍረድ

ይህ ደግሞ ከሕሊና በመነጨ መፍረድ ላይ ተመሥርቶ ወደ ሌሎችም ሕሊናና ስሜት የሚቀዳ ሌሎችን የማውገዝ አደጋ ነው።

አንድ ሰው በሐሳቡ ብቻ የፈረደ ከሆነ ሲፀፀት ጥፋቱ በዚያው ይቆማል። ነገር ግን ይህ ሰው በንግግሩ ፈርዶ ከሆነ ሌሎችም ቃሉን ከሰሙ በቃሉም ተጽዕኖ ካሳደረባቸው ቢፀፀትም እንኳ የተናገረው የፍርድ ቃል ማቆሚያ አይኖረውም። ከዚያ ምክንያቱም በሌሎች ሕሊናና ግንዛቤ ውስጥ ይቀጥላልና። ከዚያ በኋላ ምን ያህል ሰዎች ይህን የፍርድ ቃል ሰምተው እንደተጠመዱበት ማን ሊያውቅ ይችላል?

የተለያየ ዓይነት የንግግር ፍርድ አለ። ከእነዚህ መካከል የሚከተሉትን እንይ።

፪.፩ ሀሜት

ይሄ ዓይነቱ የሚፈረድበት ሰው በሌለበት ስለእርሱ ማውራት ሲሆን ምናልባትም እርሱ ባለበት ሁኔታ ምንም ለማለት አለመድፈር ነው። ሀሜተኛ ሰው የሚያወራው ምስጢር ሆኖ እንዲቀር ወይም ከሚታማው ሰው እንዳይደረስ ይጠነቀቃል። ለዚህ ምሳሌ የሚሆነው «በከብቱ ያለ ንጉሥ በሌለበት ይሰደባል» እንደሚባለው በእልቅና /በሹመት/ ለሚሠሩ ሰዎችም ሊሆን ይችላል።

ሀሜት በስውር ለሚሰደበው ራሱንም የመከላከል ዕድል ላልተሰጠው ለዚያ ሰው አደገኛ ነው፤ ስለነገሩ አያውቅምና። ሀሜቱን የሚሰሙት ሰዎች ደግሞ የተነገረውን ሁሉ የሚያምኑ ከሆነ ተጠቂው ሰው ሳያውቅ፤ ስለተከሰሰበት ነገር ግልጽ ለማድረግና ለማሳመን ዕድል ሳያገኝ ስሙ ሊጠፋ ይችላል።

ሀሜት በራሱ፤ የሚያማ ሰው ድፍረትና ወኔ እንደሌለው ያሳያል። ምናልባትም በሌለበት ሲያማው የነበረው ሰው በተገኘበት በስውር የተናገረውን ነገር በሚቃረን ሁኔታ በግብዝነትና በማስመሰል ሊናገር ይችላል።

፪.፪ ስም ማጥፋት

ስም ማጥፋት የሌሎችን ስም ማጉደፍ፣ ያለባቸውን ጉድለት /የሠሩትን ጥፋት/ ለሰዎች መንገር፤ መግለጥ በእነርሱም ላይ ጥፋተኝነትን መለጠፍ ነው። ይህ በብዙ ሰዎች ውስጥ የተዛመተ በሽታ ነው። የሚወራ ጠቃሚ ነገር ባጡ ጊዜ ሁሉ የሌሎች ዜና ዋና አጀንዳቸው ይሆናል። በተለይ እነዚህ ዜናዎች ጉድለትና ጥፋትን መተቸት፤ መግለጽና ስለ ሁኔታዎቹ መተንተን ላይ ያተኮረ ወሬ ከሆኑ ይስማማቸዋል።

ስለዚህም ስንፍና /ሥራ መፍታት/ የሰውን ስም ለማጥፋት ካሉት መንሥኤዎች መካከል የሚጠቀስ ነው። ሁልጊዜ በሥራ የተጠመደ ሰው ስለሌሎች ሰዎች እና ስለፈጸሙት ጥፋት የሚያወራበት ጊዜ የለውም። ሥራ ሳይኖራት ተቀምጣ ከጐረቤቶቿ ጋር አዘውትር ከምታወራ የቤት እመቤት ይልቅ በሥራ የተጠመደች

አንዲት ሴት በዚህ ኃጢአት የመውደቅ ዕድሏ አነስተኛ ነው። በትምህርቱና በጥናቱ ያተኮረ ፈተና ያለበት ተማሪም ስለሌሎች ጥፋት የሚያወራበት ጊዜ አይኖረውም። ለማውራት ዕድሉ ቢኖረው እንኳን ያን ለማድረግ የውስጥ ተነሣሽነት አይኖረውም። ስለዚህ በመፍረድ ኃጢአት እንዳትጠመድ አስቀድመህ ራስክን በሥራ ጥመድ።

ለስም አጥፊነት ሌላው መንሥኤ የስም አጥፊዎች ባልንጀራ መሆን ነው። እንደእነዚህ ያሉት እንዲህ ያለ ወሬ ይጀምሩና አንተም እንድታከልበት ያበረታቱሃል። ከእነርሱ ጋር ስትውል የሰዎችን ስም ክብር ማጉደፍ ለአንተ እንግዳ መሆኑ ይቀርና እንደተለመደና ተራ እንደሆነ ማሰብ ትጀምራለህ። ከሣቅ ሥላቅ ጋር ከተዋሐደ ደግሞ አንድ አንድ የመዝናኛና የደስታ ምንጭ ሆኖ ሊሰማህ ይችላል። ከዚያም ሕሊናቢስ እና ኃፍረት የለሽ ሆነህ ትቀጥላለህ።

፪.፫ ማውገዝ

ማውገዝ ማለት አንድ ሰው በደለኛ እንደሆነ አምኖ መፍረድ ነው። በእርግጥ በከፊል በማውገዝና ፍፁም በማውገዝ መካከል ልዩነት አለ። ለምሳሌ አንድን ሰው በአንዳንድ ሁኔታዎች ውስጥ ይዋሻል ማለት እና ውሸታም ነው ማለት ልዩነት አላቸው። ውሸታም ነው ማለታችን ውሸት ከዚህ ሰው ባህርይ አንዱ ክፍል ነው ማለት ነው። እንዲሁም አንድ ሰው በአንዳንድ በተለዩ ሁኔታዎች ውስጥ ፈሪ ነው በማለት እና በጥቅል

ፈሪ ነው በማለት መካከል ልዩነት አለ። በጥቅል ፈሪ ነው ካልን የሰብእናው አንዱ ክፍል ነው ማለታችን ነው።

ግለሰብን በማውገዝ እና ቡድንን በማውገዝ መካከልም ልዩነት አለ። አንድ ሰው አንድ ሌላን ሰው በማውገዝ ኃጢአት ሊወድቅ ይችላል። ሌላው ደግሞ አንድ የተወሰነ ቡድንን፣ አንድን ከተማ፣ ሁሉንም ሕዝብ ወይም በጥቅል የሰው ልጆችን ሊያወግዝ ይችላል። ለምሳሌ አንዱ ይህቺ ከተማ በስስታምነት ትታወቃለች ሊል ይችላል። እንዲሁም ሕዝቡ ቀስስተኛ ወይም ችኩል ነው እያለ ለሁሉም ሕዝብ በጥቅል አንድ መግለጫ /ስም/ ሊሰጥ ይችላል።

ይሁን እንጂ በአንድ ቤተሰብ ውስጥ እንኳ ሁለት ልጆች ቢኖሩ አንዱ ከሌላው ወንድሙ የተለየ ፀባይ ሊኖረው ይችላል። ለምሳሌም አቤል እና ቃየን ወንድማማች ቢሆኑም በሐሳባቸው ግን የተለያዩ ነበሩ። ያዕቆብና ኤሳው መንትያ ቢሆኑም በሐሳባቸው ግን የተለያዩ ነበሩ። በተመሳሳይ ሰሎሞንም ከአቤሴሎም የተለየ ነበር። በየትኛውም ቤተሰብ ውስጥ የተለያየ ጠባይ ይኖራል። ስለዚህ አንድ ሰው በዘመድ /ወገኖቹ/ መገለጫ ሊፈረድበት አይችልም። ስለዚህ በአንድ ከተማ በታየ ጠባይ በዚያ ሁኔታ ውስጥ ያልተካከሉትን ጨምሮ በጥቅል በሕዝቡ ላይ መፍረድ እንዴት ይቻላል?

በተጨማሪም አንድ ሰው በአንድ አጋጣሚ በተፈጠረ ሁኔታ ተጽዕኖ ሊደርስበት ይችላል። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ባደረገው ወይም በሆነበት ነገር በሕይወት ዘመኑ ሁሉ እንደዚያ እንዳደረገ ወይም እንደሆነ አድርጉ መፍረድ ወይም መግለጫው አድርጉ መውሰድ ሊኖር ይችላል። ነገር ግን ማንኛውም ሰው ድክመት፣ ለብ የማለት ግፊት፣ ጊዜያዊ የስሜት መረበሽ ሊያጋጥመው ይችላል። እንዲህ ያለ ጊዜ የዚህን ሰው የተሟላ ሰብእና ሊወክል የሚችል አይሆንም። ይህን በመሰለ አንድ ሁኔታ ውስጥ እያለ ሰዎች ፈርደውበት ከሆነ፤ ነገር ግን ይህ ሰው ብዙውን ጊዜውን ለነፍሱ ቅድስና የሚጋደል ከሆነ ይህ ሰው በእውነት ዕድለኛ አይደለም።

ሰዎችን በጥቅል የማውገዝ አባዜ ምሳሌ የሚሆነው እሕዛብ በአይሁድ የደረሰባቸው ውግዘት ነው። በተመሳሳይም የሳምራውያን እና ከእነርሱ ጋር የሚተባበር /የሚገናኝ/ ሁሉ የሚደርስበት ውግዘት ይጠቀሳል። ለዚህም ነው ሳምራዊቷ ሴት ጌታችን ቀርቦ ባነጋገራት ጊዜ የተደነቀችው። መጽሐፍም «አንተ የይሁዳ ሰው ስትሆን ሳምራዊት ሴት ከምሆን ከእኔ መጠጥ እንዴት ትለምናለህ? አለችው። አይሁድም ከሳምራውያን ጋር አይተባበሩም ነበርና» ይላል። ዮሐ. ፬፥፱ ይሄ አገላለጽ ሁሉንም ሕዝብ የሚመለከት ነውና። ይህ እንግዲህ በሰዎች ላይ መፍረድ ምን ያህል ግንኙነትን እንደሚቆርጥ ከሚነገሩት ቃላት የዘለለ ተጽዕኖ እንዳለው ነው።

ሌላው ምሳሌ ደግሞ በፈሪሳውያን የሚወገዙት ቀራጮች ናቸው። ቀራጮች በጊዜው የሚገለጹት በጨቋኝነታቸው ነው። ነገርግን ሁሉም ቀራጭ የግድ ጨቋኝ አልነበረም። የሚፀፀቱ ቀራጮችም ይኖራሉና። ነገርግን በቀራጮች ላይ ያን ጊዜ

የነበረው የፈሪሳውያን ከባድ ውግዘት በወንጌል ላይ በተጠቀሰው ፈሪሳዊ ጸሎት ውስጥ ታይቷል። «እንደ ሌላ ሰው ሁሉ ቀማኞችና ዐመፀኞች አመንዝሮችም ወይም እንደዚህ ቀራጭ ስላልሆንኩ አመሰግንሃለሁ» ብሏልና። ሉቃ. ፲፰፥፲፩

፪.፬ ዝናና ክብርን ማጉደፍ

ይህም ሌላው በሌሎች የመፍረድ ዓይነት ነው። ይህ ማለትም አንድ ሰው የሌላውን ኃጢአት /በደል/ በአደባባይ ሌሎች እንዲያውቁት ሲያደርግ ነው።

የሌሎችን ስም በማጥፋት ኃጢአት የወደቀ ሰው ስሙን ስለሚያጠፋው ሰው ለሰዎች በመፍረድ ስለመናገር አያመነታም /አይጠራጠርም/። ያ ሰው ሠራቸው ስለሚላቸው በደሎች የሚችለውን ያህል የፍርድ ቃሉን ሲነዛ ስሙ በመጥፋቱ ስሜቱ ለሚነካው ለዚያ ሰው አንዳች ጥንቃቄ አይኖረውም። የሌላውን ስም የማጥፋት ኃጢአት ብዙ በተሠራጨና በታወቀ ቁጥር በጣም የተጠላ ይሆናል። ይህ ስም ማጥፋት መጀመሪያ ከሰሙት ሰዎች አልፎ እየተሠራጨ ተከትለውም የሰሙት እያስፋፉት ይሔዳሉ። ማን ያውቃል? ምናልባትም የሰሙት ሁሉ ደግሞ በራሳቸው መረዳትና ድምጻሜ ሌሎች አዳዲስ ነገሮችን ጨምረው ሊቆጠር ለማይችል ሰፊ ሕዝብ ሊያስተዋውቁ ይችላሉ።

ምናልባትም በደለየተባለው ሰው /ስሙ የጠፋው/ በኃጢአቱ ተፀፅቶ ንስሐ ሊገባ ይችላል፤ ነገር ግን የጉደፈ ስሙ ይከተለዋል፤ ችግርም ያመጣበታል። የንስሐ ሕይወቱንም ሊያደናቅፍ ይችላል። የስም ማጥፋት ሥራ ብዙ ጊዜ በተጨባጭ እውነቶች ወይም በሀቅ ወይም በትክክለኛ ነገሮች ላይ ሳይመሠረት ስለሚችል ያን ሰው እንደኃጢአተኛም በመቀበላችን ምክንያት የዚያን ሰው የንስሐ ሕይወት ሊያደናቅፍ ይችላል። አንዳንዴ ስም ማጥፋቶች በሀሜትና በአሉባልታ በግምትም ላይ ሊመሠረቱ ይችላሉ። ይህ በቀላሉ የተንኮለኞች የምቀኞች የጨቋኞች ሥራ አካል ሊሆን ይችላል።

ንጉሥ አክአብ የእዝራኤላዊውን የናቡቴን የወይን አፀድ /መሬት/ ያገኝ ዘንድ ሚስቱ ኤልዛቤል በምስኪኑ በናቡቴ ላይ ለመግደል ታሴር ዘንድ ፈቅዶላታል። እርሷም በባሏ በአክአብ ስም ለሽማግሌዎች ለአለቆች ደብዳቤ ጻፈች፤ ጾምን እንዲያውጁ ናቡቴንም ከፍ ባለመድረክ አስቀምጠው የሐሰት ምስክሮች አቅርበው በማስፈረድ በድንጋይ ይወግሩት ዘንድ። ሤራውም ተሳካ፤ እርሱ /ናቡቴ/ ግን ንጹሕ ነበር። ፩ነገ. ፳፩

ይህንንም የሚመስል በጻድቁ በዮሴፍ ላይ ሆኗል፤ ለእስራትም አድርሶታል። ጸሐፍትና ፈሪሳውያን በራሱ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ለስቅለት ያበቃውን የሐሰት ወሬን ባዛመቱ ሰዓት ተመሳሳይ ነገር ተፈጽሟል።

ለእነዚህ ቀድመን ባነሣናቸው ምሳሌዎች ውስጥ የጠቀስናቸው ሰዎች ለንጽሕናቸው ምስክር ነበራቸው፤ አግኝተዋልም። ነገር ግን ንጽሕናን ለመግለጥ ዕድል ሊገኝ በማይችልባቸው የስም ማጥፋትና የሐሰተኛነት ሥራዎች ሰለባ የሚሆኑ ሊኖሩ ይችላሉ።

ስም በማጥፋት የሚሠራው በሌሎች የመፍረድ ኃጢአት በሕግም ስም ማጥፋት ተብሎ ይጠራል። ይህ ግን በቃላት /በንግግር/ ብቻ የሚገለጥ አይደለም። አንድ ኃይለኛ ጋዜጠኛ፣ አንድ ሰው፣ ድርጅት ወይም ሀገር ለማጥቃት በጥሬስ ውጤቶች ተጠቅሞ ቢያጠቃ ወደ ሰፊ ስም ማጥፋት እና ዓለም አቀፍ ቅሌት ወደ መሆን ሊያመራ ይችላል። ከእነዚህ ጥቃቶች አንዳንዶቹ ለአንድ ፕሬዚዳንት ወይም ለሁሉም የካቢኔ አባላት ወይም ለአንድ ሚንስትር ከሥልጣን መነሣትን ሊያስከትል ይችላል። ራሱን ከዚህ የተቀነባበረ ዘመቻ መከላከል ለጊዜው ባልቻለ ማንም ሰው ይህ እንዴት ሊሆን አይችልም?

፫. በኅትመት ውጤቶችና በካሴት ቅጂዎች አማካኝነት በሌሎች መፍረድ

በእርግጥም መፍረድ በአንደበት /በምላስ/ ብቻ የሚፈጸም አይደለም። የሆኑ አካላትን ለመጉዳት በመጽሐፍ፣ በበራሪ ወረቀት፣ ወይም በፎቶ ወይም ሥዕሎችን በሆኑ መንገዶች በመውሰድና በማሳተም በሺዎች በሚቆጠሩ ኮፒዎች አባዝቶ በማሠራጨትም ሊፈጸም ይችላል።

ይህ አንዱ ለሌላው በሚጽፈው ደብዳቤ ውስጥ የአንድ ሌላን ሰው ስሙን ለማጥፋት ለመኮነንም በማሰብ መጥፎ ቃላትን አካቶ በመላክም ይገለጻል።

እንዲሁም ደግሞ በንግግር ከምንፈርድባቸው መንገዶች እንደ አንድ ሊወሰድ የሚችለው በካሴት ቀድቶና አባዝቶ በሌላው መፍረድና ማስፈረድ ነው። በካሴት የተቀረጹ የንግግር መፍረዶችን

በተከታታይና በፈለግንበት ጊዜ ሁሉ ልናደርጋቸው እንችላለን። ለተወሰነ ጊዜ ሳንደጋግም በቃላት ከሚነገረው ፍርድ በባሰ የመሠራጨት፣ የመታመን ዕድል ያለው ነው። ይህ በማንኛውም ጊዜ ልንጠቀምበት /በክፉ/ የምንችልበት፣ በብዙ ቅጂ መዳረስ የሚችል እና በሰፊውም የመሠራጨት ዕድል ያለው ነው።

በምላስ መፍረድ /በንግግር/ በካህናት አፍ የተፈጸመ ከሆነ ደግሞ የከፋ ነው። ምክንያቱም ሰዎች የካህናትን ቃል ያለጥርጥር ለማመን ዝንባሌ አላቸውና። ቃላቸውም እንደ ቤተ ክርስቲያን የጸና ፍርድ ይወሰዳልና። የተፈረደበትም ሰው ራሱን ንጹህ አድርጐ ለማቅረብ /ለመከላከል/ ይቸገራል። የካህናትንም ቃል መጠራጠር ይጀምራል። ይህ በእርግጥም የከፋ ነው ምክንያቱም ማንም ሰው ካህናት የሰውን በደል እንደሚሰውሩ እንጂ በአደባባይ ገልጠው ይናገራሉ ብሎ አይጠብቅምና።

ማንም ከካህናት አንደበት የበረከትን እንጂ የፍርድን ቃል አይጠብቅምና። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም ያቺን ኃጢአተኛ ሴት «እኔም አልፈርድብሽም ሂጂ፤ ዳግመኛ ግን አትበድይ» ብሏታልና። ዮሐ. ፰፥፲፩ እንዲሁም ደግሞ «እኔ ዓለምን ላድን እንጂ በዓለም ልፈርድ አልመጣሁምና» አለ። ዮሐ. ፲፪፥፵፯

ቅዱስ ጳዉሎስ ለደቀመዝሙሩ ለቅዱስ ጢሞቴዎስ «ሌሎቹ ደግሞ እንዲፈሩ ኃጢአት የሚሠሩትን በሁሉ ፊት ገሥጻቸው» ቢለውም ይህ ግን በተለየ የቤተ ክርስተያንን ሰላም ለማስጠበቅ፣ መናፍቃንን ለማውገዝ፣ ልደገኛና የቤተ ክርስቲያን ሥርዓትና ሕግ በመጣስ የሚሰማሩትን ለመለየት በአባቶች ካህናትና መምህራን

የሚፈጸም ነው። ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ለማስጠበቅ ሲል ቅዱስ ጴጥሮስ በሐናንያና ሰጲራ ላይ ፈርዷል። የሐዋ. ፭

፬. በመስማት መፍረድ

አባቶች «አንድ አድማጭ ለተናጋሪው የፈለገውን እንዲናገር ዕድል እስከሰጠ ድረስ የተናጋሪው ተባባሪ ነው» ይላሉ። ስለዚህ አባቶች መልካም ያልሆነውን እንዳንሰማ መክረውናል። ቅዱስ ጸሊምም ስለዚህ ነገር ሲናገር እንዲህ ይላል «ከሐሜተኛ ጋር አትሒድ፤ ስለማንም በከፉ የተነገረን ሐሜት አትመን።»

ሐሜተኛን የሚሰማ ከማሰናከያ ድንጋዮች እንድንጠበቅ የተሰጠውን ትዕዛዝ ያፈርሳል። ሐሜተኛን መስማት ወይም መፍረድ በእርግጥም የማሰናከያ ድንጋይ ወይም ፈተና በመሆኑ እንዲህ ካሉቐ ሪህን መጠበቅ ይገባል። እንዲህ ያሉትን የሚሰማ ሰው፣ ስሜቱ፣ ሕሊናውና ልቡናውን ያረክሳል። ሰው የሰማውን ሁሉ ሳይመረምር ካመነ ከሌሎቹ ጋር ያለው ግንኙነት ሊለወጥ ይችላል። መስማት በእርግጥም በሕሊና /ሐሳብ/ መፍረድን ያስከትላል። ቅዱስ ሙሴ ጸሊምም እንዲህ ይላል። በልብህ /ሐሳብ/ እንዳትፈርድበት ከወንድሞችህ ያንዱንም ውድቀት እንዳትሰማ ተጠንቀቅ። ይህ የሚሆነው የሰማኸውን ሁሉ ባመንክበት አጋጣሚ ሁሉ ነው፤ የማታምን ቢሆን እንኳን ቢያንስ እነዚያን የማይታመኑ ነገሮች በነገረህ ሰው ላይ ትፈርዳለህና በዚህ ፈተና ትወድቃለህ። አንዳንዴ ደግሞ የሰማኸውን አትቀበልም፣ አትፈርድምም፣ ነገር ግን የተነገሩህ ወሬዎችና ሐሳቦች በሕሊናህ ይቀመጣሉ፤ ቆይተውም ይገለጣሉ /ፈተና ይሆኑብሃል።/

...«ከወንድሞች አንዱ ቅዱስ ኢሳይያስ* እንዲህ ይላል፦ ...ላው ላይ ሲፈርድ የምትሰማ ከሆነ እግዚአብሔር አምላክህ ...ንዳ ይቆጣ በመፍራት ለመቃወም አትፈር። ይልቁንም በትሕ...ና «ወንድሜ ሆይ እኔን ከፉውን ሰው ይቅር በለኝ፣ እነዚህ የምትነግረኝ ሁሉ እኔም ከወደቅሁባቸው መሰናከሎች ጋር አንድ ናቸውና፤ ስለእነርሱ ከዚህ በላይ ልሰማህ አልችልም» በለው።

በእርግጥ እንዲህ ቃል በቃል እንድትናገር ላይጠበቅብህ ይችላል። በተስማሚ መንገድ ግን መስማትህን ማቆም አለብህ። የንግግሩን ሒደት ልትለውጠው ትችላለህ፤ ወይም ጉዳዩን የሚያስለውጥ ጥያቄ ማንሣት ወይም ደግሞ እግዚአብሔር ለእኛ ያለው ምሕረት ብዙ ነውና ለእርሱም እንጸልይለት በማለት ደምድም።

እንዲሁም ደግሞ «እነዚህ የሰማኋቸው ውድቀቶች በዲያብሎስ ሥራና ኃይል ምክንያት የሚመጡ ናቸው፤ የዲያብሎስ የተንኮል ጥበቦች እንዴት የሚገርሙ ናቸው?» ልትል ትችላለህ። በዚህ ጊዜ ጉዳዩን ወደ ዲያብሎስ የተንኮል ጥበብ ትለውጠዋለህ። ቅዱስ ኢሳይያስ አሁንም ደግሞ እንዲሁ ይለናል «የወንድምህን ኃጢአት መስማትን ወይም በእርሱ መፍረድን ለራስህ አትፍቀድለት»

ተመሳሳይ ምክርም በመዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ ፲፭ ተቀምጧል። መዝሙረኛው «አቤቱ በድንኳንህ ማን ያድራል?በተቀደሰው ተራራህ ማን ይኖራል? በቅንነት የሚሔድ ጽድቅንም የሚያደርግ በልቡም እውነትን የሚናገር በአንደበቱ የማይሸነግል

* [illegible]

በባልንጀራው ላይ ክፋትን የማያደርግ ዘመዶችንም የማይሰድብ» ይላል። መዝ. ፲፭፥፩-፫ እንዲህ ያለ ሰው ስለሰዎች ምንም ክፉ ቃልን አይቀበልም። መስማትንም ይቃወማል።

የሐሜትንና የፍርድን ቃል መናገር አይገባም። እነዚህን ነገሮች መስማትም ቢሆን። ቅዱስ ኤቫግሪዮስ እንዲህ ይላል፦ «ክፉውን ቃል የሚሰማ ክፉን ቃል ከሚናገረው ሰው ጋር ተባባሪ ነው። ሁለቱ የልብ ንጽሕናቸውን በማጥፋት ተባብረዋልና»

ቅዱስ ኤቫግሪዮስ የሰዎችን ቃል በመስማት የሚደሰት፣ ለተናጋሪም ደግሞ ደጋግሞ ዕድል የሚሰጥ ሰው ነው። ነገር ግን በአካል ቢገኝ እንኳን ለሚባለው ነገር እዝኑ ልቡናውን ባለመስጠት ሐሳብንም በሌሎች ነገሮች በማስያዝ ክፉውን መስማት ይቃወም ነበር። ቢሰማው እንኳ በተነገረው ነገር ላይ ደግሞ አያስብም፣ አያሰላስልም፣ በልቡናው እንዲቀመጥም አያደርገም።

ቅዱስ ኤቫግሪዮስ ምክሩን ቀጥሎ እንዲህ ይለናል። «እንደ እነርሱ እንዳትበድል ለክፉ ዓላማም እንዳትጠቀምበት በሌሎች ላይ ክፉ ለሚናገሩ ሰዎች ጆሮህን አትስጥ»

እንደ እነርሱ ትበድላለህ ማለቱም እውነት ነው። ምክንያቱም ለመስማት ከእነርሱ ጋር ትቀመጣለህ፣ ጊዜህን ታባክናለህ፣ በመስማትም የሕሊና /የልቡና/ ንጽሕና ታጣለህና፤ እንዲህ ካለው ክፉ ባልንጀራ ጋር ጸንተህ ተባብረህ ከቀጠልክም እንዲህ ያለውን ወሬ ትለምዳለህ፤ በውስጡም ትሳተፋለህ።

ቅዱስ ይስሐቅ በሌሎች የመፍረድን ነገር ከእሳት ጋር እያነፃፀረ እንዲህ ይለናል «እሳት ከአንተ ወጥቶ ሌሎችን የሚያቃጥል

ከሆነ እግዚአብሔር ስለተቃጠሉ ነፍሳት እንደሚጠይቅህ እወቅ!» ይህም ስለሌሎች ወንድሞቻቸው በምትናገረው ክፉ ቃል ለሌ...ሎች ሰዎች የዋህነትና ንጽሕና ማጣት ምክንያት በሆንክ ጊዜ... የሚፈጸም በደል ነው። በዚህ ጊዜ ለእነርሱ መሰናከል /ፈተና/ ...አምጥተህባቸዋልና እግዚአብሔር ስለ እነርሱ ነፍስ ይጠይቅሃል።

...ነገር ግን አንተ ሰሚ እንጂ ተናጋሪ ካልሆንክ ደግሞ ቅዱስ ይስሐቅ እንዲህ ይልሃል። «እሳትን ካንተ የማታወጣ ሆነህ ነገር ግን ሌላው እንዲያወጣ የተስማማህ፣ በሥራውም የተደሰትክ ብትሆን፣ በእርሱ በሚደርስበት ፍርድም ተባባሪ ትሆናለህ።»

ስለዚህ ተገቢውን አካሔድ ለማመልከት ሰሚዎችን በዓይነት መከፈል ይገባናል።

ሀ/ ክፉ ወሬን ሲሰሙ የሚበሳጩ፣ መስማትን መተው የሚሹ ነገር ግን በዓይን አፋርነታቸውና እጅግ ትሑት በመሆናቸው ምክንያት ያን ማድረግ የማይችሉ አዳማጮች /ሰሚዎች/፤

ለ/ የሰውን የፍርዱን ቃል የሚሰሙ ነገር ግን ከዚያ የሚሸሹ፤ ከዚያም ቦታ ፈጥነው የሚርቁ አዳማጮች፤

ሐ/ ነገሮቹን በጥንቃቄ የሚሰሙ፣ በሰሙት ነገር ላይም በብልሐት ውይይት የሚያደርጉና የሚመረምሩ፣ ተገቢውን የሚ...ቀበሉ የቀረውን ደግሞ በማንም ላይ ሳይፈርዱ ተራ ወሬ በመሆኑ የሚቃወሙ፤ ነገር ግን የተባለውን ነገር በጥንቃቄ ለመመርመር ጊዜ የሚጠብቁ ወይም ዕድል የሚሰጡ አዳማጮች፤

መ/ የፍርድን ቃል የሚሰሙ፤ የሰሙትን የሚያምኑ፤ በእርሱም ተጽዕኖ የሚያርፍባቸው፣ ሕሊናና ልቡናቸው የሚለወጥባቸው ሆነው ሳይናገሩ ግን ዝም የሚሉ አዳማጮች ናቸው።

፭. ሌሎች የመፍረድ ኃጢአት ዓይነቶች

በሌሎች መፍረድ አንዳንዴ ሰዎችን ወደዚያ ማእዘን በመግፋት፣ በማምጣት ወይም ለዚያ በማጋለጥም ሊፈጸም ይችላል።

አንድን ሰው ሞኝ /አላዋቂ/ ላትለው ትችላለህ። ነገር ግን ለዚያ ሰው ሊመልሰው የማይችል ወይም ካለው የዕውቀት የመረዳት አቅም በላይ የሆኑ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ያንን ልታስብለው ትችላለህ። በዚህ ጊዜ እስበህበት /ሆን ብለህ/ በዚህ መንገድ ይሔንን ሰው አጣብቂኝ ሁኔታ ውስጥ በማስገባት አላዋቂነቱ እንዲገለጥ፣ /እንደዚያ እንዲታሰብ/ ጥረት አድርገሃል። እንግዲህ በአንደበትህ ግልጽ የፍርድ ቃልን ሳትናገር ነገር ግን ለዚያ ዓላማ ጥያቄን በማንሣት፣ ድርጊቱን በመፈጸም በሌሎች ላይ በመፍረድ ኃጢአት ትወድቃለህ።

ምናልባትም ሰውየው እንዲያፍር እንዲፈረድበትም ለማድረግ በግል ጉዳዮቹ ላይ የሚያጠነጥኑ ጥያቄዎች ልታነሣበት ትችላለህ፤ ለምሳሌ «በዚያን ቀን የት ነበርክ? ከማን ተገናኘህ? ለእርሱስ ምን አልከው? ምንስ ሰጠህ?...» በማለት ልትጠይቀው ትችላለህ። እነዚህ ቃላት የፍርድ ቃልን ያልያዙ ይመስላሉ። በእርግጥ እነዚህ የፍርድ ቃልነታቸው በመልሶቻቸው ላይ ወይም በአዳማጮቹ ሕሊና ውስጥ በሚፈጠር ጥርጣሬ ላይ የተመሠረቱ

...ናቸው። እነዚያ ወገኖች ሌላው ቢቀር በሕሊናቸው በእርግጥም ...የተሠራ አንድ ስሕተት /በደል/ ሊናገሩ ይችላሉና።

በሌሎች መፍረድ በቅሬታ መልክም ሊቀርብ ይችላል። ቅሬታ ...ይህም አንድ ሌላ ሰውን በመበደል ምክንያት የሚመጣ ነው። ይህ ቅሬታ በሰፊው ...ማለት በደል ፈጻሚው ላይ ክስ ይቀርባል። ...እየተሰማ በሒደ ቀጥር ተከሳሹ እንደ አጠፋ፣ እንደጨቆነ ሌሎ...ቸንም እንደዘለፈ ሆኖ ስሙ ይጠፋል።

በሌሎች መፍረድ በንግግር ብቻ ሳይሆን በገጽታ /በምልክት/ ሊገለጽ ይችላል። ለምሳሌ አንድ ሰው ስለአንድ ሌላ ሰው ቢጠይቅህ ምንም የፍርድን ቃል ሳትናገር ከንፈሮችህን በንቀት ብታንቀሳቅስ ተመሳሳይ መልእክት ለማስተላለፍ እጆችህን ብታወዛውዝ፣ ራስህን ብትነቀንቅ ወይም ተመሳሳይ መልእክት በሚገልጽ መልኩ በማየት /ትዕይንት በመፍጠር/ ይገለጻል። እንቅስቃሴዎችህና ገጽህ ሳትል ለማለት መፈለግህን በግልጽ ያሳያሉና።

በሌሎች መፍረድ በማሳፈርና በመሳቅም ሊገለጽ ይችላል። ይህ በሌሎች ኃጢአት የሚፈረዱበት ሌላው መንገድ ነው። ከሌሎች በበለጠ በሰውየው ላይ ከሚፈጥረው ስሜት አንፃር አደገኛ ነው። ለሚፈርድበት ሰው ስሜት ምንም ጥንቃቄ ሳያደርጉ መዘለፍና ማቀለል ነውና።

አንድን ሰው ስለ ውድቀቱ የሚገኝ ሰው ኃጢአት በጀርባው በሐሜት ከሚፈስበት ሰው የባሰ ነው።

አንተ ከምትፈርድበት፣ በውድቀቱም በተወሰነ ድካሙም ከምትንቀው ሰው ጋር በፍጥረት አንድ መሆንህን እወቅ፣ አን ተም እንዲሁ ትወድቃለህና።

ቤቱስ በተመዘበረበት ሰው ልትፈርድ ትችላለህ? በአንተም እንዲሁ እንዳይሆን እየፈራህ ትራራለታለህ እንጂ። ኃጢአተ ኛም በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ያለ ነው።

ቅዱስ ኢሳይያስ ያለውን አስተውል፦

«ወንድሙን የሚወቅስ፣ የሚንቀውም ወይም ስለ እርሱ ክፉን የሚናገር በእውነት ከርሕራሔ የራቀ /ጨካኝ/ ነው።»

ምዕራፍ ሦስት

በሌሎች መፍረድ ድርብርብ በደል ስለመሆኑ

ቁጣ እንዴት ዘርፈ ብዙ ኃጢአት መሆኑን እንደተናገርን እንዳብራራን ሁሉ አሁን ደግሞ በተመሳሳይ በሌሎች ላይ ስለመፍረድ ኃጢአትም እንደዚያው እንላለን። ቀጥለን እንደ ምናየው በሌሎች የመፍረድ ኃጢአት እጅግ የከፋ የኃጢአት ሰንሰለት ነው።

በብዙዎች ላይ የሚፈፀምም ጥፋት ነው። መፍረድ በእግዚአብሔር ላይ፣ በሌሎች ላይ በሚፈርደው በራሱ፣ በሚፈረድበት ሰው ላይ፣ በአዳማሎቹና ጉዳዩ በሚነካቸው ወገኖች ላይ ሁሉ በቀጥታና በተዘዋዋሪ ይፈፀማል። ያ እንዴት ሊሆን ይችላል?

፩/ በእግዚአብሔር ላይ የሚፈጸም ጥፋት ነው

መፍረድ ለእግዚአብሔር የሚሰጥ ነው። የፍርድም ባለቤት እርሱ ነውና። ምክንያቱም እግዚአብሔር ፈራጅ ነው። /መዝ ፶፥፮/ የምድርም ሁሉ ፈራጅ ነውና። /ዘፍ ፩፥፳፭/ እርሱ ፍፁም ፍርድን መስጠት የሚችል ብቸኛ ዳኛ ነው። ምክንያቱም እርሱ ልብንና ሐሳቦችን ሁሉ ይመረምራል። ያሰብነውን፣ የሰወርነውን፣ የተገለጡትንም ነገሮች በእርግጠኝነት አካባቢውንና ሁኔታዎችን ሁሉ ያለጥርጥር ያውቃልና። ስለዚህ በሌሎች የሚፈርድ ሰው

የእግዚአብሔር የሆነውን ሥልጣን ሰራሁ የሰጠ ከአትሙም በላይ የሆነውን ሳድርግ የሚል ነው።

በዚህ መንገድ በሌላው የሚፈርድ ሰው እግዚአብሔር በዚህ ሰው በአሰፈረው የፍርድ ቀን ሳይፈርድበት አስቀድሞ ፈራጅ ልሁን የሚል ነው። ይህ ሰው ከጊዜው በፊት እየፈረደ ነው። እርሱ እግዚአብሔር ጊታው በሆነለት በዚያ ሰው ላይ ይፈርዳል።

ከዚህ በተለየ ግን እግዚአብሔር እንዲፈርዱ ሥልጣንን የሰጣቸው «በከንቱ ግን ሰይፍ አይታጠቅምና ክፉ ብታደርግ ፍራ፣ ቁጣውን ለማሳየት ክፉ አድራጊውን የሚበቀል እግዚአብሔር አገልጋይ ነውና» /ሮሜ. ፲፫፥፬/ በማለት የተናገራቸው ገዥዎችን እንዲሁም የባህርይ ወላጆችንና መንፈሳዊ አባቶችን ነው። ስለዚህ በሌሎች መፍረድ ኃጢአት የወደቀ ሰው «እንዳይፈረድባችሁ አትፍረዱ» /ማቴ ፯፥፩/ የሚለውን የእግዚአብሔር ትእዛዝ ይጥሳል። እንዲህ ያለ ሰው እግዚአብሔርን አያከብርም ይበድላል።

፪/ በሌሎች በሚፈርድ በእርሱ በራሱ ላይ የሚፈጸም ጥፋት ነው

በሌሎች ላይ የሚፈርድ ሰው የፈጣሪ ጸጋና ረድኤት ይለየዋል፡ ይወድቅማል። በውድቀቱም ውስጥ ይዋረዳል። በሌሎች መፍረዱንም ያቆማል። የፈረደበት ወንድሙ በወደቀበት ኃጢአትም ሳይወድት አይቀርም። ሌሎች በወደቁ ጊዜ እርሱ የነበረው ጽናት በራሱ ኃይል ሳይሆን በእግዚአብሔር ረድኤት ነበርና። ስለዚህ ይህ ነገር አንድን ሰው ከመታበይ በሌላውም ከመፍረድ ይከለከ ለዋል። የእግዚአብሔር ረድኤት እንዳይለየው፣ እንዳይወድቅም።

ይለይሃልና በያሩ ጽናት ትወድቃለህ።» አንድ ሰው በመፍረድና በማመዛዘር መካከል ምን ግንኙነት አለ በማለት ሊገረም ይችል ይሆናል። በእርግጥ ቀጥተኛ ግንኙነት የላቸውም። ነገር ግን በሌሎች የመፍረድ ኃጢአት ውጤቱ ረድኤተ እግዚአብሔር ማጣት ስለ ሚሆን በውጤቱ ይገናኛሉ።

ስለዚህ ለእርሱ ከማዘን በመነጨ ብቻ ሳይሆን ለራስህም ከመራራት የተነሣ በሌሎች አትፍረድ። በእርግጥም ለራስህ በመራራት በሌሎች በመፍረድ የሚመጣብህን መዘዝ አስቀር። እንዲህ የሚያደርግ ሰው የፈጣሪ ጸጋና ረድኤቱ ሊለየው ይችላል። በዕለተ ምጽዓትም ለፍርድ የተሰጠ ይሆናል። በወንድሙም ላይ በፈረደበት በዚያ ኃጢአት ወድቆ መሰቃየት እጣ ፋንታው ይሆናል። ይህም አንድን ወጣት በኃጢአት በመውደቁ በብርቱ የፈረደበት አረጋዊ በኋላ በጥርጥር ወድቆ በመጨረሻም ከገጻም እንደወጣው ያለ ነው። ይህም አረጋዊ በእርጅና ዘመኑ በወጣ ትነቱ እንኳን ላልሰመደው ኃጢአት ተሳልፎ ተሰጠ።

በተጨማሪም በሌሎች የሚፈርድ ሰው በዚሁ መንገድ በሌሎች ሰዎች ይታያል /ይፈረድበታል/። «ሰዎችን የሚመረምር እርሱ፣ በእነርሱ አጣብቂኝ ውስጥ ይገባል» የሚባል አባባል አለ። ዘወትር የሌሎችን ስሕተት የሚፈልግ ሰው በእርሱም ላይ ይህ ይሆናል። የሌሎችን ድክመት የሚገልጥ የራሱም ድክመቶች በእነርሱ ይገለጡበታል። ሁሉም በአንድ ድክመት ውስጥ አሉና ፈራጅ ማነው? የሚፈረድበት?

በሌሎች በመፍረድ ውስጥ ግን «እንዳይፈረድባችሁ አትፍረዱ፣ በምትፈርዱበትም ፍርድ ይፈረድባችኋልና፣ በምትሰፍሩበትም መስፈሪያ ይሰፈርባችኋል» ባለው የእግዚአብሔር የፍርድ ቃል ውስጥ ይወድቃል። /ማቴ ፯፥፲፩-፳፪/ ስለዚህ በሌሎች የሚፈ ርድ እርሱ በፍርድ ውስጥ ይወድቃል።

እርሱ ከዚያ በማያንስ ሳይሆን በመፈረበት ዓይነት በእርሱ ይመፈራል። ሐዋርያው ቅዱስ ማርቆስም «በምትመፍሩበት መሥ ፈሪያ፣ ይመፈርላችኋል። ለእናንተም ይጨመርላችኋል» ይላል። ማር. ፬፥፳፬

ለምሳሌ አንድ ሰው በሌላው ላይ በጭካኔ የፈረደ ከሆነ የእርሱን ለመሰለ ጭካኔ ተላልፎ ይሰጣል፣ ከዚያም በላይ። በእዚህ በምድር ፍርድን ተቀብሎም ከሆነ እንዲሁም ዳግሞ በሰማይም ይሆንበታል። ይህም ከታናሽ ባልንጀራው ጋር የተዋዋለውን ዕዳውንም እንዲከፍል ያሰጨነቀውን ያን ጨካኝ ባሪያ ይመስላል። ቅዱስ መጽሐፍም «ከዚያም ወዲያ ጌታው ጠርቶ አንተ ክፉ ባሪያ ስለለመንሽኝ ያንን ዕዳ ሁሉ ተዉሁልህ፣ እኔ እንደ ማርሁህ ባልንጀራህ የሆነውን ያንን ባሪያ ልትምረው ለአንተስ አይገባህምን? አለው። ጌታውም ተቆጣና ዕዳውን ሁሉ እስኪ ከፍለው ድረስ ለማሰቃየት አሳልፎ ሰጠው።» ማቴ. ፲፰፥፴፪-፴፬

በአንድ ወቅት አንድ ወንድም መንፈሳዊ አባቱን «አባቴ ለምንድነው ሰይጣን በማመዝር ኃጢአት በብርቱ የሚዋጋኝ? የምወድቀውስ?» በማለት ጠየቀው። ያም አባት እንዲህ አለው «በወንድምህ ላይ ስለምትፈርድ ነው። ስለዚህም ጸጋ እግዚአብሔር

ስለዚህ በሌሎች በምትፈርድበት ጊዜ የአንተው ድክመ ቶች እንዲገለጡ ራስህን ታቀርባለህ። ድክመቶችህ በምትፈር ድበት ሰው በራሱ፣ በሚወዱት ጓደኞቹ፣ መጠቃቱን በማይሹ ሁሉና እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በማንኛውም ምክንያት ሊገ ለጡ ይችላሉ። በመሆኑም አንተ ከወቀሳ የጸዳህ እንደሆንክ ቆጥ ረህ በወንድምህ ላይ ለመፍረድ ራስክን ዳኛ አድርገህ አታስቀ ምጥ። እንዲት ሴት ስታመነዝር አግኝተው ሊፈርዱባት ያቀረ ቧትን ሰዎች ጌታችን ምን እንዳላቸው አስተውል። «ከእናንተ ኃጢአት የሌለበት እርሱ አስቀድሞ ይውገራት» ዮሐ. ፰፥፯ ሐዋር ያው በሴቲቱ ላይ የፈረዱ ልበ ደንዳናዎችን ጌታ እንዴት እንዳስ ተናገዳቸው ሲገልጽ «ደግሞም ጐንበስ ብሎ በጣቱ በምድር ላይ ጻፈ» አለ። የእነዚህ ቃላት ትርጓሜ ጌታ የእነዚህን የእያንዳንዳ ቸውን ኃጢአት እንደጻፈባቸው ይናገራል። በዚህም ምክንያት ነው ከዚያው አስክትሉ «እነርሱም ይህን ሲሰሙ ህሊናቸው ወቀ ሳቸውና ከሽማግሌዎች ጀምሮ እስከ ኋለኞች አንድ በአንድ ወጡ። ዮሐ. ፰፥፰-፱ ይህም «ከእናንተ ኃጢአት የሌለበት አስ ቀድሞ በድንጋይ ይውገራት» የሚለውን የጌታን ቃል በሰሙ ጊዜ የእርሷን ኃጢአት በማየት ፋንታ የራሳቸሁን ተመልከቱ እንዳ ላቸው ሆነ።

ምንም እንኳ ሴቲቱ ስታመነዝር አግኝተው በማቅረ ባቸው ምክንያት በእርግጠኝነት የበደለች ቢሆንም፣ እነርሱም የጨቆኗት ባይሆንም ወይም በሐሰት የከሰሷት ባይሆንም

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ከሳሾቿ የሌሎችን በደል ሳይሆን የራሳቸውን ኃጢአት ብቻ እንዲመለከቱ ፈለገ።

ፈራጅ እግዚአብሔር ብቻ ነው፤ ምክንያቱም እርሱ ብቻውን ቅዱስ ነውና። ራእ. ፲፭፥፬ ሰዎች ሁሉ «በመስተዋት ቤት የሚኖሩ ሰዎች ድንጋይ አይወራወሩም» የሚለውን አባባል ተግባራዊ ማድረግ ይገባቸዋል። ስለዚህ ቤትህ እንዳይጠፋ /እንዳይሰበር/ ይህንን አባባል ታስታውሳለህ!? ርሕራሔን ለራስህ የምትፈልገውን ያህል ለሌሎችም ሩህሩህ ሁን፤ ኃጢአትህ እንዲሰወርልህ የምትፈልገውን ያህል የሌሎችንም በደል ሰውር /ሸፍን/። ኋላ አንተ ልትሠፈርበት በምትፈልገው መሥፈሪያ ሌላውን ሥፈር። አንተ በደሎችህ እንዲሸፈኑ ከሌሎችም ዕይታ እንዲሰወሩ ከፈለግህ አንተም እንዲሁ አድርግ፤ ሌሎችንም የሰውን በደል ሸፍኑ፤ ግለጡም አትበል።

፫/ በሚፈረድበት ሰው ላይ የሚፈጸም ጥፋት ነው

በሌላ ሰው መፍረድ ስም፣ ክብርና ዝናውን በሌሎች አንደበት ጭምር እንዲጠፋና በሁሉም ሰው እንዲታኝክ ማድረግ ነው። ምንም እንኳ እርስ በእርስ እንድንከባበር የሚፈለግብን ቢሆንም ይህ ግን ያንን ሰው ማዋረድ ነው። /ሮሜ. ፲፪፥፲/

በሌላው ላይ መፍረድ ለዚያ ሰው ራሱን የሚከላከልበት ዕድል ሳንሰጠው ስለእርሱ በደል ማውራት ነው። ያንን ድርጊት የፈጸመበትን ሁኔታና ምክንያት የሚያብራራበት ዕድል አንሰጠውምና። ምናልባት ሁሉም ነገር ተራ ወሬና አሉባልታ ብቻ ሊሆን ይችላል።

ይህ ሰው በእርግጥም በድሏል እንበል፤ ታዲያ ስለምን ኃጢአቱን አትሸፍንም? ቅዱስ መቃሪዮስ የሌሎችን ኃጢአት በመሸፈኑና አጋልጦም የማይሰጥ ነበርና መልአክ ዘበምድር ተብሏል። የሌሎችን ኃጢአትና አሳፋሪ ሥራ መሸፈን የማትችል ከሆነ ቢያንስ በወሬና በውይይት በስፋት ለትችትና ለውርደት ተጋላጭ ለመሆኑ ምክንያት አትሁን። የሌሎችን በደል አስፋፍቶ በማውራት የንስሓ መንገዳቸውን አትዝጋ።

ኃጢአቱ ለሌሎች ያልተገለጠበት ሰው በፈለገ ጊዜ ንስሓ ሊገባ ይችላል፤ ነገር ግን ክፉ ስሙና በደሉ በሔደበት ሁሉ የሚከተለው ጠባዩን ለመለወጥና አዲስ ሰው ለመሆን ይቸግረዋል። ስለ አንድ ሰው ኃጢአት ማውራትና ማስወራት ያንን ሰው ሰዎችን እንዳያምን ያደርገዋል። ይህ ደግሞ ያንን ሰው በኅብረተሰቡ ውስጥ ያለውን ክብር ለመመለስና ከተከበሩ ሰዎች ጋር ያለውን ግንኙነት መልካም ለማድረግ ያስቸግረዋል። ስለ እርሱ በተስፋፋው ሐሳብ ምክንያት ከእርሱ ጋር ያለው የትኛውም ግንኙነት በጥርጣሬ የተሞላ ይሆናል። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንዲህ አለ «በወንድምህ ላይ በጭካኔ የሚያወራ አፍህን መዝጋት ካልቻልክ ቢያንስ አንተ አታውራ።»

፬/ በሰማእያኑ ላይ የሚፈጸም ጥፋት ነው።

የተፈተኑት /ጥፋት የተፈጸመባቸው/ ሰማእያኑ በደላቸው ምንድነው? ሌሎችን ስለሚያሰናክሉ ሰዎች ጌታችን የተናገረውን ቃል በእርግጠኝነት ታውቃለህ። «መሰናከል ግድ ሳይመጣ አይቀርም፤ ነገር ግን መሰናከሉን ለሚያመጣው ወዮለት፤ ከእነዚህ በታናናሾች አንዱን ከማሰናከል ይልቅ የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ታስሮ ወደ ባህር ቢጣል ይጠቅመው ነበር።» ሉቃ. ፲፯፥፩-፪

ታዲያ በአንተ ምክንያት የዋህነቱንና በጎ ሐሳብን ያጣው ሰማኢ /ሰሚው/ በደሉ ምንድነው? በአንተ ምክንያት ስለሌሎች ያለው አመለካከት በሐሳቡ ይለወጣልና እንዲያም ሆኖ በውስጡ ይጸናልና። ሌሎች በማያውቁት ሁኔታ ከእርሱ ጋር ያላቸው ግንኙነት ይበላሻል። ይህ ሁሉ ጥፋት ግን ለምን?

ስለዚህ አባቶች «በሌላው ላይ በክፉ የሚያወራ ሁሉ የሰማእያኑን ነፍስ ያጠፋል» በማለት ተናገሩ።

፭/ አንተ በማታውቃቸው እነርሱም በማያውቁህ ሰዎች ላይ የሚፈጸም ጥፋት ነው

በአንተ የተነገረ የውግዘት ቃል በሰማእያኑ ብቻ የሚወሰን ላይሆን ይችላል፤ ነገር ግን ቃልህ በአንዱ ተወስዶ፤ ለሌላው ተነግሮ፤ ተባዝቶ፤ ሰፍቶ፤ ተንሠራፍቶ አንተ በማታውቃቸው ሰዎች ዘንድ ሁሉ ይደርሳል። እነዚህ ሁሉ ይሰናከላሉ፤ የዋህነታቸውን ያጣሉ። ከተፈረደበት ሰው ጋር ያላቸውም ግንኙነት ይሻከራል፤ ከዚህም በላይ ይሰፋል።

በአንተ የሚነገረው የውግዘት ቃል የደረቀ የጠወለገ አይደለም፤ ሌላ ፍሬን በየቦታው ያፈራል፤ ሌላ የድምዳሜ የሆኔት፣ የጭማሪ፣ ያለመረዳት ዘሮችን ያፈራል። የፍርድ ቃል ከዚህም በባሰ የተለያዩ ስሜቶችና ውዝግቦችን ሊያስከትል ይችላል። በአንተ የሚሰናከሉ ሰዎችን ቁጥርና በደልህ የት ድረስ እንደሚደርስ ለመረዳት ከፈለግህ እንደማትችል እወቅ። መድረሻው ሩቅ ነው፤ የተሰናከሉ ሰዎችም በስም የምታውቃቸው የማታውቃቸውም ናቸው።

በሌሎች በመፍረድህም ሌሎች በአንተ ላይ እንዲፈርዱ ምክንያት ትሆናለህ። አንተ እንዴት በሌሎች ላይ እንደፈረድክ እነርሱ ደግሞ ሊያብራሩ ይነሣሉ። በዚህና በዚያ ሰው ላይ ስለምን ፈረድክ? ለምንስ ተቸኸው? ከዚህ ሥራህ በስተጀርባ ያለህ ነገር ምንድነው? የተናገርኸውስ ሐሰት ነው ወይስ እውነት? በዚህ መንገድ ስለ እነርሱ መናገር ትቀጥላለህ? በዚህ አካሔድ ነገሩን ከአሰናካይ ወደ አሰናካይ ታሸጋግራለህ። ቃልህን የሰሙ ጥቂቶች ያምኑሀል፤ ሌሎች ደግሞ አይቀበሉም። ያመኑህ የፈረድክበትን ያንን ሰው ሲጠሉ ፤ያልተቀበሉህ ደግሞ አንተን በክፉ ያስቡሀል። በሁለቱም መንገድ ኪሳራው ያንተም የእነርሱም ይሆናል።

፮. በሌሎች መፍረድ የሚያስከትላቸው ሌሎች የኃጢአት ሥራዎች

የመፍረድ ሥልጣን ባላቸው ሰዎች ዘንድም ቢሆን በሌሎች መፍረድ ሁል ጊዜ ንጹሕና ትክክለኛ ላይሆን ይችላል። ሆኔት /ማሾከሾክ/ ማሰናከያ በሆነ ጊዜ በደል ይሆናል። ከሌሎችም የኃጢአት ሥራዎች ጋር ሊገናኝና ምክንያት ወይም መነሻም ሊሆን ይችላል። በሌሎች ወደ መፍረድ ኃጢአት ያስገቡን ምክንያቶች ምናልባትም ከመፍረድ በላይ የሆኑ የከፉ ኃጢአቶች ሊሆኑ ይችላሉ።

በሌሎች የመፍረድ ኃጢአት ከምንም የሚነሣ ሊሆን አይችልም፤ ምክንያቶች ወይም ለዚያ ድጋፍ/አነሣሽ/ የሆኑ ልናውቃቸው፣ልናስተውላቸው ልንቋቋማቸው የሚገቡ ወሳኝ ነገሮች ይኖራሉ። ስለዚህም እነዚያ ምን እንደሆኑ መለየት ይገባናል። አንዳንዶቹ በሌሎች ከመፍረድ ጋር ቀጥተኛ ዝምድና ላይኖራቸው ይችላል፤ ነገር ግን በአንድ አጋጣሚ ወይም ከአንድ ሰው ጋር ወይም በሌላ አጋጣሚ ወይም ከሌላ ሰው ጋር ግንኙነት ይኖራቸዋል እንጂ። እነዚህ ኃጢአቶች ምንድናቸው?

ፍቅርን ማጣት

በመጽሐፍ ቅዱስ «ፍቅር የኃጢአትን ብዛት ይሸፍናል» የሚል ተጽፏል። ፩ጴጥ.፬፥፰ ምናልባትም ይህ ቃል በቅዱስ ጴጥሮስ የተጠቀሰው «ፍቅር ግን ኃጢአትን ሁሉ ትከድናለች» ከሚለው የመጽሐፈ ምሳሌ ቃል ተወስዶ ነው። ምሳ.፲፥፲፪ ከዚህ ቃል ጋር የሚስማማ በስፋት የሚነገር አባባልም አለ። «ባልንጀራህ የወረወርከውን ጠጠር ይውጣል፤ ጠላትም ስሕተትን እንድትሠራ ይመኛል።» የሚል። አንድን ሰው ስትወደው አትፈርድበትም፤ እንደውም ትከላከልለታለህ /ትጠብቀዋለህ/ እንጂ። ጻድቅ በባልንጀራው ላይ ክፉን እንደማይፈጽም መዝሙረኛው ይናገራል። መዝ.፲፭፥፫ እንደውም ለሚወዳቸው፣ ለባልንጀሮቹ፣ ለዘመዶቹ የበለጠ መልካምን ያደርጋል እንጂ። ብዙ ጊዜ ሰው የሚፈርደው በማያውቀው ወይም ጥላቻም ሆነ ወዳጅነት በሌላው ወይም ለስምና ዝናው በየትኛውም መንገድ ጉዳይ በማይለው ሰው ላይ ነው። በእርግጥ ይህ ሁሉንም ከመውደድ የክርስትና

መርሕ ጋር የሚጋጭ ነው። ምክንያቱም እያንዳንዱ ሰው ሌላው ባልንጀራው ሰው እስከሆነ ድረስ ወይም ወንድሙ እስከሆነ ድረስ ለስሙና ዝናው ወዳጅነት ሊኖረው ይገባል። የማናውቃቸው ቢሆኑ እንኳን ለሁሉም ማሰብ ይገባናል።

በሌላም በኩል በሌሎች የመፍረድ ኃጢአት ከጥላቻና ከተንኮል ኃጢአት ጋር አብሮ ይሔዳል። ተንኮል ቁጣ ወይም ጥላቻ አንድ ሰው ከልቡ ሊያጠፋቸው የሚገቡ ብርቱ የኃጢአት ሥራዎች ናቸው። ተወዳጁ ሐዋርያ ቅዱስ ዮሐንስ «ወንድሙን የሚጠላ ግን በጨለማ አለ፤ በጨለማም ይመላለሳል የሚሔድበትንም አያውቅም፤ ጨለማው ዓይኖቹን አሳውሯልና።» በማለት ያረጋግጥልናል። ፩ዮሐ.፪፥፲፩

ጥላቻ በሌሎች የመፍረድ ኃጢአትን ትወልዳለች፤ በክፋቷም እየመገበች ታሳድጋታለች፤ ከእርሷም ጋር መንገዷን ሁሉ ትሔዳለች። በጥላቻ ምክንያት በሌሎች የመፍረድ ኃጢአት ድርብ ድርብርብ በደል ሆናለች። ወይም የሌሎችን ስሜት ያለመረዳት በሌሎች የመፍረድን ኃጢአት ከፍ ከፍ ያደርጋታል። ፍቅር ግን ከእነዚህ ሁሉ የራቀ ነው። ጥላቻ ወደ ቁጣና ተንኮል በተለወጠ ጊዜማ ምን ያህል የላቀ እንደሚሆን አስብ! በዚህ ጊዜ ነገሩ ውስብስብ ይሆናል። ጥላቻ ተንኮልና ቁጣን ወልዷልና። እነዚህም ደግሞ በሌሎች የመፍረድን ኃጢአት ያሳድጉታል። ጥላቻ ምስቱንም እየመገበች እያሳደገች ሳለ ከጥላቻ የሚመነጭ በሌሎች የመፍረድ በደል ከተመረዘና ከተረበሸ ልብ ይመነጫል። በሌሎች በመፍረድ ጊዜ የሚወጣው ድምፅና ቃል በውስጥ ያለ ተንኮልን ያንጸባርቃል።

የልብ መደንደን

በሌሎች መፍረድ ስለሌሎች በሚፈጸም ሆኔት ወይም ተራ ወሬ ወይም ስላቅ እና አሽሙር ሆኖ እነሱ እንደሚያስቡት ለመዝናናት በሚደረግ ጊዜ ከልብ መደንደን ጋር ላይያያዝ ይችላል። በአንዳንድ ሁኔታዎች ውስጥ ግን በጠንካራ ፍርድና በጠንካራ ቃላት የሚፈጸሙ ናቸው። ለዚህም ምሳሌ የሚሆነን ኃጢአት የሠራችውን ሴት በሰዎች ሁሉ ፊት ያቀረቡት ጸሐፍትና ፈሪሳውያን ናቸው። እርሷን ለማዋረድ ምክንያት ያደረጉት ነገር አጥጋቢ ባይሆንም እንደ ሕጉ በድንጋይ ሊወግሯት ሽተው ነበር። ዮሐ.፰፥፭

ሌላው ምሳሌ ደግሞ ክርስቶስን ለሞት ያበቁት ሰዎች የልብ ድንዳኔ ነው። እነዚያ አጥብቀው እንዲሞት የፈለጉት «ስቀለው» በማለት ጮኸዋል። ማቴ.፳፯፥፳፫፣ማር.፲፭፥፲፫ ይህ መፍረድ ደግሞ ከደንዳና ልብ በሚመነጩ ሌሎች የጭካኔ ሥራዎች ማለትም በመትፋት፣ በግርፋት፣ በመምታት. . . ይታጀቡ ነበር። የልብ ድንዳኔ/ጭካኔ/ በሚያቆስሉም ቃላት በመጠቀም ሊገለጽ ይችላል፤ ምናልባትም ለሚፈረድበት ሰው መጥፎ ስም በመስጠት ሊሆን ይችላል። ወይም ክብሩን፣ ባህርይና አስተሳሰቡን የሚነኩ የከስ ቃላትን መናገር ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ «አንተ ደንቆሮ/ሞኝ/» የሚለው ኅጂ ቃል ጌታ እንዳለው በሲዖል እሳት የሚያስቀጣ ነው። ማቴ.፭፥፳፪። ከዚህ «አንተ ደንቆሮ/ሞኝ/» ከሚለው ቃል ጋር አቻ ትርጉም ያላቸውና የምንጠቀምባቸው ቃላት ምን ያህል ይሆኑ!

ስለዚህ ደንዳናነትን አንዳንድ ሰዎች በጭካኔና በኃይል በሌሎች ላይ ለመፍረድ ሊጠቀሙበት ይችላሉ። እንዲህ ያለ ሰው በሌሎች ላይ በሚፈርድ ጊዜ በከባድ ቁጣ፣ በግልጽ እልህና ንዴት ሊሆንና ቅሬታ ሊያሳይ፣ የዚያን የወንድሙን ግብር በኃይለኛ ቃላት ሊገልጽና የልቡን ድንዳኔ ሊያንጸባርቅ ይችላል።

የልብ ድንዳኔ ለተፈረደበት ለዚያ ሰው ይቅርታን ባለማድረግም ሊገለጽ ይችላል። የዚያን ሰው ስሜታዊና ማኅበራዊ ዝንባሌ፣ አካባቢያዊ ሁኔታ እና ለዚያ ተግባር ያበቁትን ምክንያቶች ከግምት ባለማስገባትም ሊናገር ይችላል። እነዚህን ሁሉ ከግምት ለማስገባት «ምንም ምክንያት ቢሆን» በማለት ፍርዱን ይደመድማል። ድንዳኔ ለፍርድ ተላልፎ በተሰጠው ሰው ላይ ከባድ ቅጣት ተፈጻሚ እንዲሆን በማድረግም ሊገለጽ ይችላል። ቅጣቱም በዚሁ ፍርዱን በሰጠው ሰው ሥልጣን የሚፈጸም ከሆነ፤ ሥልጣን ባይኖረውም እርሱ መመሪያ በሚሰጠው ሰው ከሆነ፤ ሥልጣን ባይኖረውም እርሱ መመሪያ በሚሰጠው ሰው ተፈጻሚ ሊሆን ይችላል። በጭካኔም «ይህ ሰው ይህና ያ ቅጣት ይገባዋል፤ እኔ ፈራጁ ሰው ብሆን ይህንና ያንን አደርግበት ነበር» ይላል።

ጭቆና /ሜና/

ሁሉም ፍርዶች ትክክለኛ ናቸው ማለት አይቻልም። ልክ አንድ ሰው ስለሌላው ሰምቶ ወይም ሀሜትን መነሻ አድርጎ በሚፈርድበት ጊዜ እንደሚሆነው በጭቆና/በሜና/ የሚፈጸም ፍርድ ሊሆን ይችላል። የሚሰማው ነገር ሐሰት፣ ሀሜቱም በአድልዎ የተፈጸመ ወይም የሌላውን ክብርና ዝና ለማጉደፍ በአንድ

ተንኮለኛ ሰው የተነዛ ሊሆን ይችላልና:: የተባለው ነገር በሀሜት የተባዛ ተራ ፌጠራ ሊሆን ይችላል:: የተባዛ ወሬ ሁሉ እውነት፣ ለፍርድም መነሻ ሊሆን አይችልም::

ጭቆናው /ሜናው/ እርግጠኛ ያለመሆንና ያለማረጋገጥ ውጤት ነው:: የተከሰሰ ሰው ወንጀለኛ መሆኑ ተጣርቶ እስኪ ደመደም ድረስ ንጹሕ እንደሆነ ይታሰባልና:: ነገር ሳይጣራ፣ ተከሳሹ ራሱን የመከላከል ዕድል ሳይሰጠው በማንም የተሰጠ ምስክርነትን ሁሉ እንመነው አይባልም::

ጻድቁ ዮሴፍ ባልሠራው ጥፋት በጌታው ሚስት በሐሰት ተከሶ ተፈርዶበት ነበር:: ክሱ እውነት ይሁን ሐሰት ሳይጣራ ለእስራትና ለጌታው ቁጣ ተዳርጎ ነበር:: በክፉዋ በጲጥፋራ ሚስት ምክንያት የዮሴፍ ዝና በሀገሩ ሁሉ በክፉ ይጠራ ነበር:: በዚህም በሐሰት ላይ በተመሠረተ ፍርድ ዮሴፍ በክፉ ስምና በእስራት እነዚያን ዓመታት አሳልፏል:: ጭቆናው/ሜናው/ ምናልባትም እንደ ጲጥፋራ ሁኔታ ብናየው ተጨባጩን /እውነታውን/ ባለ ማወቅ ሲሆን እንደ ጲጥፋራ ሚስት ከሆነ ግን ሆነ ተብሎ /በማወቅ/ በንጹሑ ዮሴፍ ላይ በመፈጸሙ ምክንያት የመጣ ነው:: ጭቆናው /ሜናው/ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ተፈጽሞ ንጹሕ ሰው ላይ የሚፈረድ ከሆነ በሌሎች ላይ ወደ መፍረድ ኃጢአት ያደርሰናል::

ውሸት

ውሸት ፍፁም ውሸት ወይም ግነት ሊሆን ይችላል:: ፍፁም ውሸት ማለት በአንድ ሰው ላይ ሆን ብሎ /በማወቅ/

ስሙን ለማጥፋት በማሰብ አንድ ተራ የውሸት ወሬ መፍጠር ነው:: በእርግጥ ነገሩ በውስጥ ካለ ጥላቻ ወይም ከበቀል ወይም ከቅናት ሊመ ጭ ይችላል:: በዚህ ጊዜ በሌሎች ላይ መፍረድ ድርብ ድርብርብ ኃጢአት ይሆናል::

በሌሎች ላያ መፍረድ በማጋነን መልክ ከከፊል ውሸት ጋር በማሳከት መንገድ ሊሆን ይችላል:: አንድ ሰው ባለመረዳት ምክንያት በሃይማኖት ጉድለት ውስጥ ሊወድቅ ይችላል፤ በዚህ ጊዜ ሌላው ሰው ይህንን ጉድለት ኑፋቄ፣ አሳፋሪ ሥራ፣ ውርደት፣ ጉድለቱንም በማስፋት መንፈስ ቅዱስን እንደመሳደብ አድርጎ ሊያቀርበው ይችላል:: ይህ እንግዲህ ሰውየውን ለመጉዳት ወይም አጋኖ በማውራት ልማድ ምክንያት የፈጸመው ሊሆን ይችላል::

ስለዚህ ውሸት በሌሎች የሚፈርደው ወይም ከሌላው ተቀብሎ የሚያወራው ሰው የፈጠረው ሊሆን ይችላል:: በእነዚህ በሁለቱም መንገዶች የሚፈረድበት ሰው ንጹሕ ቢሆንም ለጭቆና /ተቀ /ሜና/ ተጋልጧል:: ስለዚህ አንድ ውሸትን የሚያስተላልፍ /ተቀ ብሎ የሚያሠራጭ/ ሰው ከመቀበልና ለሌላው ከማስተላለፉ በፊት ነገሩን መመርመር ይገባዋል:: ምናልባትም ለሌላው የማስተ ላለፍ መብት እንኳ ላይኖረው ይችላል::

ትሕትና ማጣት

በሌሎች የሚፈርድ ሰው ብዙ ጊዜ የራሱን ኃጢአት የሚረሳ ነው:: አንድ ሰው የራሱን ኃጢአት የሚያስታውስ ከሆነ

የወንድሙን በደል አያስብም:: ጸሐፍትና ፈሪሳውያን አመንዝራ ዋን ሴት በያዟት ጊዜ የራሳቸውን ኃጢአት አላሰቡም ነበር። ስለዚህም ጌታ ኃጢአታቸውን አስታወሳቸው:: በእርሷም ላይ መፍረድን አቆሙ፤ ከዚያም ሥፍራ ራቁ:: /ዮሐ.፰+፱-፲፩/ ትሕ ትና ማጣት አንድን ሰው ራሱን ከሌሎች የተሻለ አድርጎ እንዲ ያስብ፣ እንዲፈርድባቸውም ያደርጋል:: ያ ትዕቢተኛ ፈሪሳዊ የራሱን ጽድቅ፣ጾምና አሥራት ማውጣት በማሰብ ራሱን ከሌሎች ቀራጮች አስገድደው ግብርን ከሚያስከፍሉ በሐሰት ከሚፈርዱ፣ ከአመንዝሮች ወይም ከዚያ ከቀራጩ ሰው የማይ መሳሰል /ልዩ/ እንደሆነ ባሰበ ጊዜ በቤተመቅደስ ቆሞ በቀራጩ ላይ ፈርዷል:: ሉቃ.፲፰+፲፩ በእግዚአብሔር ፊት በራሱ ላይ ይፈርድ የነበረው ያ ቀራጭ ግን በሌላ በማንም ላይ አልፈረደም::

አንድ ሰው ራሱን ከሱ በደረጃ ዝቅ ካለ ሰው ጋር በማያ ነፃጽር ጊዜ በትዕቢት መንገድ በሌሎች የመፍረዱ ነገር ይጨ ምራል:: ያ ትዕቢተኛ ፈሪሳዊ በቀራጩ ላይ እንዳደረገው ከእርሱ በደረጃ በሚያንሰው ላይ ሁሉ ይፈርዳል:: ራሱን ዝቅ አድርጎ የሚያይ ትሑት ግን በማንም አይፈርድም:: ትዕቢተኛ የፈረ ደበት ያ ሰው በወደቀበት ኃጢአት በተመሳሳይ እርሱም ሊወድቅ እንደሚችል ሊያስብ አይችልም:: ከየትኛውም ኃጢአት የራቀ እንዳይደለ የሚያስብ ትሑት ሰው ግን «ወገታ የጣለቻቸው ብዙ ናቸውና፣ እርሷም የገደለቻቸው እጅግ ብዙ ናቸውና» ያቺን ኃጢአት ያስታውሳል:: ምሳ.፯+፳፮ ይህም በሌሎች እንዳ ይፈ ርድ ያደርገዋል::

ትዕቢት ግን አንድን ሰው ከእርሱ በላይ በሆኑት ላይ እንኳን እንዲፈርድ ያደርገዋል:: ማርያምና ወንድሟ አሮን ታላቁ ነቢይ ሙሴ ኢትዮጵያዊቷ በማግባቱ ምክንያት በመፍረድ ኃጢ አት ውስጥ ወድቀው ነበር:: ትሑት ሰብእናቸውን ይመልስ ዘንድ የፈረዱበትን የሙሴንም ታላቅነት ይገነዘቡ ዘንድ እግዚ አብሔርም ገሠጻቸው፤ ከሙሴም ምን ያህል ያነሡ እንደሆነ ገለ ጻላቸው:: እግዚአብሔርም ማርያምን በለምጽ መታት፤ ትሕት ናንም እንድትማር ከእርሱ በላይ በሆነ በማንም ላይ እንዳ ትፈርድ እንዳልነጹ ሰዎች ከቅጽሯ ርቃ ለሰባት ቀን ተዘግቶባት ቆየች:: ዘኁ.፲፪+፲፭

ከማርያምና ከአሮን ውድቀት ጀርባ የትሕትና ማጣት /ትዕቢት/ ነበር:: «በውኑ እግዚአብሔር በሙሴ ብቻ ተናግሯ ልን፣ በእኛስ ደግሞ የተናገረ አይደለምን?» በማለት ተናግረው ነበርና:: ስለዚህ እግዚአብሔር በፊቱ ያላቸውን ዋጋቸውን እንዲ ያውቁ ትሑትም እንዲሆኑ ገሠጻቸው::

ሌሎችን ማስናከል

ይህ በሕሊና ሳይሆን በአንደበት /በንግግር/ የመፍረድ ውጤት ነው:: በንግግር ሲፈረድ ሰሚው ይሰናከላል፤ ከተናገረው ጋርም በአንድ ዓይነት ኃጢአት ውስጥ ይወድቃል:: በዚህ አጋ ጣሚ በሌላው በመፍረድ የሚናገር ሰው ወንድሙ እንዲወድቅ ምክንያት ይሆናል:: በዚሁ ጥፋትም በእግዚአብሔር እንዲጠየቅ ምክንያት ይሆናል:: ብዙ ሰዎችም ይሰናከላሉ፤ የተናጋሪውም በደል የከፋ ይሆናል::

ስድብና ንቀት

በሌሎች በመፍረድ ሒደት ውስጥ የሚፈረድበት ያለጥር ጥር ይዋረዳል:: በአንድ ሰው በመፍረድ ሒደት ውስጥ ደካማ ጎኖቹ፣ ኃጢአቱ፣ ጉድለቶቹ ይገለጣሉ:: ፍርድም የጸና ሊሆን ስድብና ንቀት ይከተትበታል:: ፈራጁ ሰው የሚፈርድበትን ሰው ዋጋ ቢስነት እንዲሰማው በማድረግ፣ በንቀትም በመዝለፍ ሌሎችም እንዲንቁትና ክብር እንዲያሳጡት ያደርጋል:: ነገሩ ከዚህም አልፎ የሚፈረድበትን ሰው ምስጢሩን በመግለጥ፣ የግል ጉዳዮቹን በሰዎች ሁሉ ፊት በማሳየት ወደ መጉዳት ያድጋል::

ያ ሰው አክሎም በሚፈርድበት ሰው ላይ ሌሎች ክብሩን የሚነኩ ነገሮች ይናገራል፤ ያ ሰው የማይጠቅም፣ ሊታረምም የማይችልና የጠፋ እንደሆነ አድርጎ በመፍረድ የሚሰሙት ሁሉ እንዲያምኑ ሊያደርግም ይችላል::

ሥነ ሥርዓት ማጣት

በሌላው ላይ የሚፈርድ ሰው በጠላቶች ፊት ድክመ ቱንና ጉድለቱን በመጥቀስ በእርሱ ላይ እንዲፈነድቁበት እንዲ ሳንዱበት ያደርጋል:: ጠላቶቹ ዕድሉን ይጠቀሙበታል እንዲ ሁም አዲስ የውጊያ መሣሪያ በመያዝ ይህን ሰው ያጠቁታል:: ይህም በሰውየው ላይ ብዙ ችግር ያስከትልበታል::

ያ ሰው ምናልባትም በሥራ ረዳቶቹ፣ በልጆቹ ወይም በደረጃ ከእርሱ ባነሡና ታናሽ በሆኑ ሰዎች ፊት ሊሆን ይችላል:: ይህም ያ ሰው ክብሩን እንዲያጣ ወይም ሥልጣኑን እንዲነጠቅ

በንቀት የሚፈጸም ሊሆን ይችላል:: እነዚህና እነዚህን የሚመስ ሉት ሁሉ ሥርዓት ማጣትና በሌሎች ላይ የመፍረድ ኃጢአትን ከባድና በእጅጉ የሚያስጠይቅ የሚያደርግ ነው:: ይህ ሁሉ ጥበብ ከማጣትና የሌሎችን ስሜት ከጣም ካለማስገባት ጋር ይደባለቃል::

በሌሎች ምኞት/ሐሳብ/ ላይ መፍረድ

አንድ ሰው ሌላው ቀርቶ በሰዎች ፍላጎት/ዕቅድና/ ዓላማ ላይ ይፈርዳል፤ እንዲህና እንዲያ ዓይነት ክፉ ፈቃድና መሻት አላቸው ይላል:: ፍላጎትና ዓላማ ግን የሚመለከተው እግዚአብሔ ርን ብቻ ነው:: በሌሎች ላይ መፍረድን አዘውትሮ የሚፈጽም ሰው በሐሳብና መሻት ላይ በመፍረድ ኃጢአት ውስጥ ለመው ደቅ ያበቃዋል:: ይህም በዚያ ዘንድ ከነበረው ልምድና ድምዳሜ የተነሣ ነው ሊባል ይችላል:: በእርግጥ እነዚህ ሁለቱም ትክክል አይደሉም:: ብዙ ጊዜ ግን ድምዳሜዎች ሁሉ የተሳሳቱና ዕውቀትን መሠረት ያላደረጉ አንድ ሰው ሊያስበው ከሚገባው በላይ ማሰብ ከመሆን በተጨማሪ ሜናዎች ናቸው:: ሮሜ.፲፪+፫

በሐሳብ ባለ ፍላጎት ላይ መፍረድ እውነት ቢሆን እንኳን መንፈሳዊ ስሕተት ነው:: ሐሳብና ስሜቶች በጥርጣሬ ብቻ የሚ ታወቁና ሁልጊዜ ጥርጣሬዎችም እውነት ሊሆኑ የማይችሉ በመሆ ናቸው በውስጥ ስሜትና በሰዎች ሐሳብ ላይ መፍረድ የበለጠ /የባሰ/ ስሕተት ነው:: አንድ ሰው በአንድ ሰው አጠቃላይ ሕይ ወት ወይም ባህርይ፣ ሌላው ቀርቶ በወደፊት ዕጣ ፈንታው ላይ እንኳ ሊፈርድ ይችላልና::

በገነተ አበው መጽሐፍ አንድ አረጋዊ አባት እንዲህ ብሏል «የሰው መንፈስ የሰውን ነገር ብቻ ያውቃል፤ /፩ቆሮ.፪+፲፩/ ብዙዎች ያለ እኛ እርዳታ ኃጢአታቸውን አውቀው ንስሓ ይገባሉ:: እግዚአብሔር በጌታ ቀኝ እንደተሰቀለው ወንበዴ ሊቀ በለው ይችላልና ሰው በሕይወቱ የመጨረሻ ቅጽበት ንስሓ ሊገባ ይችላልና በማንም ላይ መፍረድ አይገባንም:: ፈራጅ እግዚ አብሔር ብቻ ነው:: በእግዚአብሔር መብት /ሥልጣን/ እጃችንን ማስገባት እንዴት ደፈርን!

«ሁላችንም ኃጥአን፣ ተላላፊዎች ሆነናል ኃጥኡን አትጥላው፤ ግድ ካለህ ለእርሱ አልቅስለት፤ ለነፍሱም ጸልይለት::»

ይህን እያሰቡ አበው ለፈራጅነት ሳይሆን ለመሀሪነት በታ ይሰጣሉ፤ ኃጥአንም ስምና ዝናውን ከማጥፋት ይልቅ እንጸል ይላት ዘንድ ያዝዛሉ:: ይህ ለእኛም ጥቅም እንጂ ለኃጥእ ብቻ አይደለም:: በኃጥእ ላይ በመፍረዳችን እንዳይፈረድብን፣ ለርሱ ባላየነው ምህረት የተነሣ ከእግዚአብሔር ምህረት እንዲቸረን ነው:: የአበው አባባሉችም ከዚህ ጋር ይስማማሉ::

ግብዝነት

በሌሎች ሰዎች ጥፋት የሚፈርድን እርሱ ግን ያንኑ ጥፋት የሚፈጽም ምናልባትም ከዚያ ሰው በከፋ የሚያደርገን ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግብዝ እንደሆነ ይነግረናል:: ጌታችን እንዲህ ዓይነቱን ሰው እንዲህ ይለዋል «በወንድምህ ዓይን ያለውን ጉድፍ ስለምን ታያለህ? በዓይንህ ግን ያለውን

ምሰሶ ስለምን አትመለከትም?... አንተ ግብዝ አስቀድመህ ከዓይንህ ምሶሰውን አውጣ፣ ከዚያም በኋላ ከወንድምህ ዓይን ጉድፉን ታወጣ ዘንድ አጥርተህ ታያለህ::» ማቴ. ፯+፫-፭

እኛ በስውር በወደቅንበት ኃጢአት ሌሎች ሲፈጽሙት ዓይቶ በእነርሱ መፍረድ ግብዝነት ነው:: ምናልባትም ከዚያም በላይ በሆነ የኃጢአት ሥራ ውስጥ እንወድቃለንና::

ምዕራፍ አራት

በሌሎች ላይ ስለመፍረድ የአባቶች ትምህርት

ቅዱስ ዶሮቲዮስ /Dorotheus/ እንዲህ አለ።

«በእግዚአብሔር ፍጥረት ላይ መፍረድ የሚገባው ከእኛ ይልቅ ራሱ እግዚአብሔር ነው።»

«እርሱ እግዚአብሔር ብቻ የማንኛችንም ግልጽና ሥውር ነገሮች ያውቃልና እሱ ብቻውን በማንኛቸውም ነገሮችና በማንኛችንም ላይ የመፍረድ ሥልጣን አለው።»

«እግዚአብሔር ብቻ እውነትን የሚመሰክርና የመፍረድ መብት አለው፤ እርሱ የማንኛችንንም ባህርይና አቅም ያውቃልና።»

እግዚአብሔር የማንኛውንም ሰው ዝንባሌ፣ ችሎታ፣ አካባቢ ሁኔታ፣ ከሁሉት ያውቃል። ስለዚህ በሚፈርድ ጊዜ በእውነት ይፈርዳል። ለዚህም ነው ቅዱስ ጳውሎስ «አንተ በሌላው ሎሌ የምትፈርድ ማን ነህ? እርሱ ቢቆም ወይም ቢወድቅ ለገዛ ጌታው ነው፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ሊያቆመው ይችላልና ይቆማል።» በማለት ይህንን የእግዚአብሔርን ሥልጣን እንድንረዳ ያሳሰበው። ሮሜ. ፲፬፥፬

ቅዱስ ዶሮቲዮስ አሁንም ደግሞ እንዲህ ይላል

«በሌሎች የመፍረድ መርዝ አንዳንዴ ከአንዱ ፊስ ወደ ሌሎች ይቀዳል» እዚህ ላይ ይህ አባት በሌሎች የሚፈርዱ

ሰዎችን መርዙን እንደሚተፉ እባብ ያስባቸዋል። በሌሎች መፍረድንም የደረሰበትን ሁሉ እንደሚገድል መርዝ አድርጐ ገለጸው።

ቅዱስ ኢቫግሪዮስ ደግሞ እንዲህ ይላል፡-

«በሕደቀትና ውድቀት ባጋጠማቸው መካከል ልዩነትን አታድርግ። የኩራት ሐሳብም አንተ ፈራጅ እንደሆንክ እያሳምንም።»

ይህ ቅዱስ በቃሉ ኩራትንና በሌሎች መፍረድን አገናኟቸዋል። ቅዱስ ኢሳይያስ ደግሞ እንዲህ አለ።

«አንድ ሰው ኃጢአትን ሲሠራ ብታገኘው አትሳለቅበት፤ አትናቀውም፤ አንተም በጠላቶችህ እጅ እንዳትወድቅ።»

ቅዱስ እንጦንስ እንዲህ አለ

«ምንም ምክንያት ቢኖርህ ማንንም አትሳደብ፤ ወንድምህንም አትማ፤ በሕጉ ያለውን ያልፈጸመ ቢሆን እንኳን።»

ቅዱስ ዕንባቆም እንዲህ አለ

«ማንንም አትናቅ፣ በእርሱም አትፍረድ፣ በኃጢአት ውስጥ ወድቆ ያየኸው ቢሆን እንኳን።»

ስታመነዝር በተያዘችው ሴት ታሪክ ውስጥ ያለው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ይህንን ሕግ /ትዕዛዝ/ ያረጋግጥልናል።ይህች ሴት እንዲፈረድባትና በድንጋይም ተወግራ እንድትሞት በያዟት ሰዎች በጌታ ፊት ቀርባ ነበር። በእርግጥ እርሷን የከሰሷት በሐሰት አልነበረም፤ ያልሠራችውንም የገለጹበት አጋጣሚ አልነበረም፤ ምክንያቱም በእርግጥም ኃጢአት ውስጥ ነበረችና። ይሁን እንጂ ጌታ በእርሷ ላይ ከመፍረድ ከለከላቸው፤ «ከእናንተ ኃጢአት

የሌለበት አስቀድሞ በድንጋይ ይውገራት» ባላቸውም ጊዜ ሐሳባቸው ወደ ራሳቸው ኃጢአት ተመለሰ። ዮሐ.፰፥፯

በዚህም ጌታ በኃጢአት ውስጥ ወድቆ ብናየው እንኳን በማንም እንዳንፈርድ ትምህርት ሰጠን። እኛም ደግሞ በብዙ ኃጢአት ውስጥ እየወደቅን ነው። እናም ታማሚ ሰው ስለበሽታው ሌላውን ታማሚ አይሰድብም፤ ምክንያቱም ሁለቱም ለተመሳሳይ ስቃይ የተጋለጡ ናቸውና። ስለዚህ የሌላውን ጉድለቶች ከማገለጥ ይልቅ መሸፈን የተሻለ ነው። ምክንያቱም እኛም የራሳችን ጉድለት አለብንና።

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንዲህ አለ

«ወንድምህን የማትሸፍነው /በደሉን የማትሸፍን/ ከሆነ ቢያንስ አትፍረድበት።»

«በወድምህ ላይ ክፉ የሚናገር እንደበትን/አፍን/ ማቆም የማትችል ከሆንክ፡ ቢያንስ ራስህ በእርሱ ላይ ክፉን ለመናገር አፍህን አትክፈት» ስለዚህ እጅግ ጠቃሚው ነገር በወንድምህ ላይ በሰዎች የሚደርስበትን ጎጂ የሆነ ስም ማጥፋትን መከላከል ነው። ካልቻልክ ቢያንስ በእርሱ ላይ በመፍረድ አትሳተፍ /አትተባበር/ ይልቁንም የፍርድን ቃል ቀድሞ መናገር አትጀምር።

ቅዱስ ጳውሎስ ዘሲና እንዲህ አለ

«ባልንጀራህ በበደለ ጊዜ ለአንተ እንደምታልቅስ እዘንለት፣ ምክንያቱም ሁላችንም ለውድቀት የተጋለጥን ነንና።»

በዚህ መንገድ እርሱን በጭካኔ ፍርድ ሳይሆን በርሕራሔ ፍቅር ቅረበው። በውድቀት ውስጥ ቢገኝም እንኳ ባልንጀራህና ወንድምህ ነውና። ኃጢአቱን ውሰድ፣/ያ/ ለራስህ እንደሆን አድርገህ ግለጽ፤ ስለ እርሱም ሙት። ታዲያ አንተ ወንድምህን ምን ያህል ልታቀርበው ይገባህ ይሆን?!

ሰማያዊው አባት የጠፋ ልጁ በተመለሰ ጊዜ «ይህ ልጄ ሞቶ ነበርና ደግሞም ሕያው ሆኗል» ብሏልና። ሉቃ.፲፭፥፳፬ የጠፋና የሞተ ሆኖ ቢኖርም አባቱ እርሱን ልጄ ብሎ ጠራው።

አሁንም በዚህ ታሪክ ውስጥ አንድ ታላቅ ነገር እንማራለን። ሰማያዊ አባት ልጁን ይቅር እንዳለ ወንድሙ ግን ያንን እንዳላደረገ ነው። ሌላው ቀርቶ ወንድሙ በወንድሙ መመለስ ወደ ደስታው ለመምጣት በደስታውም ለመሳተፍ መቃወሙን እናያለን። እናም በወንድሙም በአባቱም «ይህ ልጅህ... ገንዘብህን ከጋለሞቶች ጋር በልቶ...» በማለት ፈርዷል። ሉቃ. ፲፭፥፴

እግዚአብሔር በፍቅሩና በርሕራሔው ድንቅ ነው። ሁሉም መብት ያለው /ሁሉን ሊያደርግበት/ የሚችል ቢሆንም እንኳ እርሱ ይቅር ይላል። በማንም ለመፍረድ መብቱ የሌለን እኛ ታዲያ ስለምን ይቅርታን አናደርግም?

ቅዱስ አትናቴዎስ እንዲህ ይላል።

«ይቅር እንድትባል በወንድምህ ላይ ፈራጅ አትሁን። ምክንያቱም ጌታ "እንዳይፈረድብህ አትፍረድ"» ይላልና። በሌሎች ላይ የምናደርገው ይቅርታና ምሕረት በፍርድ ቀን ወደ እኛ

ይመለሳል። በሌሎች ላይ መፍረድን ከእኛ ማራቅ እምነት እና ንስሓ እንዲኖረን በማዘጋጀት ይቅርታን ለማግኘት ይረዳናል።

ማር ይስሐቅ ደግሞ እንዲህ አለ

በወንድምህ ላይ ክፉ ሐሳብ ካለህ ተጠንቀቅ፤ ፍጹምነት ላይ የደረስክ ቢሆን እንኳን የትሩፋት /የመልካም ሥራዎችህን አቋም/ ከልብህ ውስጥ ይገዳል።

ማር ይስሐቅ ይህንን ሲያረጋግጥ «በክፉ ሐሳቦች ውስጥ ዘወትር መኖር ከልብ ማደንደን የሚመጣ ነው» ይላል።

ማር ይስሐቅ ጨምሮም እንዲህ ይላል «በጌታ እግዚአብሔር ምሕረት ትወለድ ዘንድ የወንድምህን በደል ሸፍን፤ ከተስፋ መቀረጥ ስሜት ነጻ እንዲወጣ አጠንክረው።»

ይህም ማለት ኃጥአንን የምንቀርብበት ምሕረት የእግዚአብሔርን ምሕረት ለመቀበል የተገባን ያደርገናል፤ ጌታ «ምን እንድ ትሰሙ ተጠበቁ፤ በምትሠፍሩበት መሥፈሪያ ይሠፈርላችኋል፤ ለእናንተም ይጨመርላችኋል።» እንዳለ። ማር. ፬፥፳፬

ማር ይስሐቅ አሁንም ደግሞ እንዲህ ይላል

«የተናቀውን፣ ምስኪኑን፣ የተጨነቀውን በቃል እርዳ፤ ሁሉን በሚችል በእርሱ የቀኝ ክንድ ትረዳለህ፤ በመከራ ውስጥ ያሉትን በዘወትር ጸሎትህና በልብ ሐዘንህ ተካፈል፤ ለጥያቄዎችህ /ለተማጽኖህ/ ሁሉ ከምሕረት ምንጭ መልስ ታገኛለህ።»

ቅዱስ እንጦንስ እንዲህ ብሏል፡- በተጸራሪዎችህ እጅ ከመውደቅ ትድን ዘንድ በሌሎች ላይ አትፍረድ። በሌሎች ላይ ስትፈርድ ወደተውሃቸው ኃጢአቶች ትመለሳለህ።

በሌሎች ላይ በመፍረድ ልብህን አከብደህ ቢያገኝህ፣ እነርሱ ከአጋንንት ጋር ያለባቸውን ጽኑ ጦርነት አንተም ትቀምሰው ዘንድ ሊያደርግ እግዚአብሔር ይቻለዋል። በወደቅህ ጊዜ በሌሎች ላይ መፍረድን ትተህ ለነርሱ ርሕራሔ ይኖርሃል።

ቅዱስ እንጦንስ እንዲህም ብሏል፡-

«እግዚአብሔር ጸሎትህን እንዳይጸየፍብህ ሌሎችን አትጸየፍ።»

በሌላው ላይ በመፍረድ የተነሣ የሚመጡ እነዚህ ሁለት ኪሳራዎች /በቅዱስ እንጦንስ ትምህርት መሠረት/ እጅግ ብርቱ ናቸው።

ሀ/ ወደቀደመ ኃጢአት እመለስ ዘንድ በተጸራሪዎች እጆች ተላልፌ መሰጠት፣

ለ/ የጸሎቴ በእግዚአብሔር ዘንድ መናቅ፣

ከአፍቃሪ ልብ የመነጨ አይደለምና እግዚአብሔር እንዲህ ያለውን ጸሎት ይጸየፋል።

ባህታዊው ቅዱስ ኢሳይያስም ተመሳሳይ ትምህርት ያስተምራል።

ቅዱስ ዶሮቲዮስ እንዲህ ብሏል፡-

«በልቡ በሌላው ላይ የሚፈርድና አፉንም በርሱ ላይ የከፈተ፣ በወንድሙ ላይ በፈረደበት ኃጢአት እርሱም ይወድቅበታል፤ መለኮታዊ ጥበቃ እርሱንም ስለፈራጅነቱ ይለየዋልና።»

ታላቁ ቅዱስ መቃርዮስ እንዲህ ብሏል፡- ምላስህን ጠብቅ፤ በወንድሞችህም ላይ ክፉን አትናገር፤ በወንድሙ ላይ ክፉን የሚናገር በርሱ የሚያድረውን እግዚአብሔርን ያስቆጣልና።

በወንድም ላይ የተሠራ ግፍ ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ እንደተፈ ጸመ ይቆጠራል።

ከገነተ አበው የተገኘ ታሪክ፡- በአንድ ወቅት፣ አባ ይስሐቅ የተባለ ካህን ከወንድሞች በአንዱ ላይ ፈረደ። አባ ይስሐቅ ወደ በኣቱ ሲመለስ መልአከ እግዚአብሔር ከበኣቱ በር ላይ ቆሞ ጠበ ቀውና «የዚያን ወንድም ነፍስ ወዴት ትጣል ዘንድ እንደምት... እንድጠይቅህ እግዚአብሔር ወዳንተ ላከኝ» አለው። አባ ይስሐ ቅም የወንድሙ ነፍስ እንድትጠፋ ከመሻት ባይናገርም ኃጢ አት እንደሠራ ተረዳና በመልአኩ ፊት ተጸጸተ። ለመልአኩም «በድያለሁና ጸሎትህ ይምረኝ ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሁን» አለው። መልአኩም «እግዚአብሔር ይቅር አለህ፤ አንተም ከእግዚአብሔር ቀድመህ በሌላው ላይ እንዳትፈርድ ራስህን ጠብቅ» አለው።

ቅዱስ ጴሜን እንዲህ አለ፡-

«በጽሙና ያለ የሚመስል፣ በህሊናው ግን በሌሎች ላይ በመፍረድ የተጠመደ ሰው ይኖራል። ይህ ሰውና እርሱን የሚመስል ሁሉ ዘወትር እየለፈለፈ እንደሆነ ይረዳ።»

በሌሎች ላይ መፍረድ በአፍ አውጥቶ ብቻ ሳይሆን በህሊናም ሊፈጸም እንደሚችል ይህ አባት ያስተምረናል። አንደበት በሌሎች ላይ ከመፍረድ ተገታ ማለት ህሊናም እንዲሁ ከመፍረድ ተገትቷል ማለት ላይሆን ይችላል።

ይሁንና፣ አፍ አውጥቶ በሌላው ላይ የፈረደ በህሊናው ብቻ ከፈረደ የበረታ ፍርድ ይቀበላል። በህሊና ብቻ የመጣ ውድቀት

አደባባይ ስላልወጣ ሌላውን /የተፈረደበትን ሰው/ አላበሳጨም። የሌላውንም ስም አላጠፋም። የህሊና ውድቀት ገና በራስ ብቻ የተወሰነ ነውና በአንደበት የተገለጠ የአደባባይ ውጤት የለውም።

ከአበው አንዱ እንዲህ አለ፡-

አንድን ሰው ዛሬ ኃጢአት ሲሠራ ብታየው ነገ አትፍረደበት፣ ኃጢአቱን በሠራበት ቀን ማታውኑ ንስሐ ገብቶ እግዚአብሔር ይቅር ብሎት እንደሆን ምን ታውቃለህ?

ታላቁ ቅዱስ መቃርዮስ እንዲህ ብሏል፡-

«ማንንም ክፉ ነው ብለህ በህሊናህ አታስብ ወይም አትቀበል፤ ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ «ማንንም ርኩስ ነው እንዳልል እግዚአብሔር ይህን አሳየኝ ብሏልና።» /ግብ.ሐዋ. ፲፥፳፰/

ቅዱስ ኤፍሬም ደግሞ እንዲህ አለ፡-

«በሌሎች ስሕተት መደሰታችን ውስጣችን በክፋት እንደተሞላ ያሳየናል።

በወንድሙ ውድቀት የሚፈነጥዝ ሰው እንደዚያ ሰው እርሱም ይወድቃል።

ነገ ምን እንደሚሆን አታውቅምና ወንድምህን አታማጥል፤ ምናልባት አንተ ትወድቅ ይሆናል፤ እርሱ ደግሞ ንስሐ ይገባ ይሆናል።

ጓደኛውን የሚሰድብ ሰው ሀሜተኛና ክፉ ነው፤ ምህረትና ሐዘኔታም አያውቅም።

ራስህን በሌሎች ላይ ፈራጅ አድርገህ አትሹም፣ እያንዳንዱ ስለራሱ ሥራ ይፈረድበታልና አንተም ሌሎች ስለሠሩት አይፈረድብህምና።»

ቅዱስ ስምዖን ዘአምዲ እንዲህ አለ፦

«ከወንድሞች አንዱ በትንሹ ከመንገድ ቢወጣ በርሱ ተስፋ አትቁረጥ፣ መጽሐፍ 'አንዱ ሌላውን ያበርታ' ይላልና። /፩ተሰ. ፱÷፲፭/ እየወደቀ ያለውን ልታነሣው ይገባሃል እንጂ ታጠፋው ዘንድ አይገባህም። በወንድምህ ላይ ስትፈርድ፣ ስለራስህስ ምን ትላለህ?»

ቅዱስ ጴሜን እንዲህ አለ፦

«በራሳችን ላይ ብንፈርድ፣ በሌሎች ላይ አላግባብ ለመፍረድ የሚሆን ጊዜ አይተርፈንም።»

ማርይስሐቅ እንዲህ ይላል፦

«አንተም እንደነርሱ እንዳትወድቅ በሌሎች ላይ አትፍረድ። በሌሎች ላይ የሚፈርድ እነርሱ በወደቁበት መንፈሳዊ ጦርነት ውስጥ ባይሆንም ራሱን ግን ለፈተና እያጋለጠ ነው።

ከአፈር እንደተገኘህ አትርሳ፣ ደካማ ሥጋና የርሱ ተፈጥሯዊ ጫና እንደሌሎቹ ሁሉ በአንተም ላይ አለብህ።

የእግዚአብሔርን አስታዋሽነት ቸል ያለ ሰው ብቻ በወንድሙ ላይ ክፉን ይናገራል።»

ይህም ማለት ከጸሎት ጋር፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን እያነበበ እግዚአብሔርን ሁልጊዜ ለሚያስታውስ ሰው የሌላውን ኃጢአት ለመቁጠርና ለመፍረድ ጊዜ አይተርፈውም። በአምልኮቱ ቸለ የሚል ሰው ግን በስንፍና /ያለሥራ/ የሚያጠፋው ጊዜ በሌሎች ላይ የመፍረድ እድል ይሰጠዋል።

ዮሐንስ ሐጺር እንዲህ አለ፦

«ለጠፉት አዛኝ፣ ለወደቁት መሐሪ ሁን።»

ይህም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለዕብራውያን የተናገረውን ይመስላል። «ከነርሱ ጋር እንደታሰረ ሆናችሁ እስሮችን አስቡ፣ የተጨነቁትንም ራሳችሁ ደግሞ በሥጋ እንዳለ ሆናችሁ አስቡ» ይላል። ዕብ. ፲፫÷፲፫

በርግጥም፣ የወደቁትን ልናነሣቸው እንጂ ልንፈርድባቸው አይገባም።

ነቢዩ «የደከሙ እጆችን አበርቱ፣ አቅም ያጡ ጉልበቶችንም አጠንክሩ» ይላል። ኢሳ. ፴፭÷፫ ሐዋርያው ደግሞ «ሰነፍ የሆኑትን ገሥጹአቸው፣ ድፍረት የሌላቸውን አጽኑአቸው፣ ለደካሞች ትጉላቸው፣ ሰውን ሁሉ ታገሡ» ብሏል። ፩ተሰ. ፭÷፲፬

ማር ይስሐቅም እንዲህ ብሏል፦

«በገዛ ዐይኑ ያለውን ምሰሶ የሚመለከት፣ በወንድሙ ዐይን ውስጥ ያለውን ጉድፍ የሚመለከትበት ጊዜ የለውም። በሌሎች ላይ የሚያየውን ድካመት የሚያስተካክል ሰው ለራሱም መንፈሳዊ መስታወትን አግኝቷል።

ሌሎች ስሕተት እየሠሩ መሆናቸውን ስናስተውል፣ እኛም ያንን ስሕተት እየሠራን እንዳይሆን ራሳችንን መመርመር

አለብን። ሌሎች የተወገዙበት ተግባር በኛ ዘንድ ካለ ራሳችንን እናስተካክላለን።

ቅዱስ ኢቫግሪየስም በተመሳሳይ እንዲህ ብሏል፦

የሌሎችን ስሕተት የሚመረምር ሰው የራሱን ተግባራት ገና በቅጡ አልመረመረም፣ ራሱን ቢመረምርስ ኖሮ በሌሎች ያለውን ድካመት በራሱም ውስጥ ያገኘው ነበር።

ቅዱስ ሜለስም /St. Melus/ ተመሳሳይ ነገር ተናግሯል፦

«የራሳችንን ጉዳዮች ብንመረምር በሌሎች ላይ ባልፈረድን ነበር፣ ሌሎችን የምንወቅስበትን ድካመት በራሳችን ላይ እናገኘዋለንና።»

ከአበው አንዱ እንዲህ አለ፦

እግዚአብሔር ዳኛ ነውና ሁሉንም ፍርድ ለልጁ ሰጥቷል። ዮሐ. ፭÷፳፪ ፍርዱ ግን በመጨረሻዋ ቀን እርሱ በሕያዋንና በሙታን ላይ ለመፍረድ ሲመጣ ይሰጣል። ስለዚህ አንተ ዛሬ ያለ ጊዜውና የፈራጅነት ሥልጣን ሳይኖርህ በሌላው ላይ ትፈርድ ዘንድ ከቶ ማን ነህ?»

ታላቁ ቅዱስ መቃርዮስ እንዲህ ብሏል፦

«ልበ ንጹሕ ትሆን ዘንድ ሌላውን ከማጠልሸትና ከማማት ራስህን ከልክል፣ የማጠልሸትን ነገር የሚሰማ ጆሮ ከቶውንም ልብን ሳይቆሽሽ በንጽህና መጠበቅ አይቻለውም።»

ጆሮ ከልብ ጋር የተሳሰረ ነውና ልብህ ንጹህ ይሆን ዘንድ ጆሮህን በንጽህና ጠብቅ።

ሀሜትንና ማጠልሸትን የሚሰማት በአደጋ ውስጥ አለ፣ ይህን ክፉ ይልቁንም የሚናገራት በበለጠ አደጋ ውስጥ አለ፣ ይህን ክፉ ንግግር የሚያመላልሰውም እንዲሁ አደጋው የከፋ ነው።

በሚያመላልሰው ክፉ ወሬ ምክንያት የሰዎችን ግንኙነት ስለሚያሻክረው ሰው ምን እንላለን? ያለ ጥርጥር ይህ ሰው ከእግዚአብሔር ርቋል። መጽሐፍ «አስታራቂዎች ብፁዓን ናቸው፣ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና» ይላል። ማቴ. ፭÷፱ ስለሆነም በሰዎች ፊንታ ጠብን የሚዘራ ሰው የእግዚአብሔር ልጅ አይደለም።

ቅዱስ ዮሐንስ ዘአሲዩት በአንድ ወቅት ይህን ተጠየቀ፦

«በክፉ ላይ የሚፈርድ ሰው ክፉትን ይጠላልን?» ለዚህ ጥያቄ የቅዱሱ መልስ «አይጠላም፣ ሁሉም ሰው ክፉን እጸየፋለሁ ይላል፣ ክፉትን እንደምትጸየፉ ሊመሰክርላችሁ የሚችለው ግን ሥራ ችሁ ብቻ ነው።»

ቅዱስ አውግስጢኖስ እንዲህ ይላል።

«አራዊትን መግራት ግልመድ ችሎ የነበረ ሰው አንደበቱን መግራት አልቻለም /ያዕ ፫÷፰/ የጌታን ቃል የማይፈራ እርሱ፣ ወንድሙንም «አንተ ሞኝ» የሚል ማንም የሲዖል እሳት አደጋ ውስጥ ነው።» /ማቴ. ፭÷፳፪/

በእውነቱ ከሆነ ፍርዳችን በንቁዎቹ ብቻ የተወሰነ አይደለም። ነገር ግን ከሞታቸው አስቀድሞ ለንስሐ ሕይወት ሊበቁ ወደሚችሉ፣ እግዚአብሔርም ኃጢአታቸውን ከሚያስተሠርይላቸው፣ «በደላቸውን እምራቸዋለሁና፣ ኃጢአታቸውንም ከእንግዲህ ወዲህ

አላስብምና።» /ኤር. ፴፩÷፴፬/ በማለት በተናገረው ቃል ኪዳኑ መሠረት ጻግም ወደማያስብባቸው ሙታንም ይደርሳል እንጂ።

እግዚአብሔር የሰዎችን ኃጢአት አያስብም/አያስታውስም/፣ እኛ ግን አሁንም ድረስ እናስብባቸዋለን። እንዴት የሚገርም ነገር ነው! አንድ ሰው አእምሮው የሚያመላልሰው ነገር አንዳንዴ ራሱንና ሌሎችንም ያስቸግራል። የአንድ ሰው ምላሱም /ነገሩም/ ደግሞ አንዳንዴ እሱንና ሌሎችንም ይረብሻል። ሰው የሁሉን ሥራ በትችት ዓይን፣ ማቆሚያ በሌለው ሐሳብ፣ ሊያቆስልም በሚችል ንግግር /ምላስ/ ለመታዘብ ራሱን ያስቀምጣል። ነገር ግን በምንም ምክንያት ቢሆን በሌሎች እንዳንፈርድ ቅዱሳን ከልክለዋል /አዘዋል/።

በእርግጥ በሌሎች ላይ የመፍረድህ ዓላማ ምንድነው? ያንን ሰው ሰዎች እንዲጠሉት ትሻለህን? ወይስ እግዚአብሔር እንዲያጠፋውና እንደ ክፉ ሥራው እንዲቀጣው ትፈልጋለህ? እስቲ ስለዚህ ነገር ዕውቀትን የሚሰጥህን አንድ ታሪክ ተመልከት።

አንድ በምግባር በሃይማኖቱ የተናቀና ሰነፍ የሆነ መነኮስ ነበር። ሊሞት በደረሰ ጊዜ አበው መነኮሳት ሞትን እንዴት ይቀበላት እንደሆነ ያዩ ዘንድ በዙሪያው ተሰባሰቡ። ነገር ግን ደስተኛ ሆኖ አገኙት። አንድ አረጋዊ መነኮስም «ወንድሜ ሆይ በርታ በክርስቶስ ስም እንጠይቅህ፣ እንዲህ እጅግ ደስተኛ የሆንከው ለምንድነው?» በማለት ጠየቀው። ያም ታማሚ መነኩስ እንዲህ ሲል መለሰ «ሰዎች ነፍሴን ይወስዷት ዘንድ ሲመጡ አየሁ። የሠራሁትንም የኃጢአት ሥራ መዝገብ አየሁት። እንዲህም አሉኝ «እነሆ የኃጢአት ሥራዎችህ» እኔም አልኩ «አውቃለሁ

አልክድም። ነገር ግን መነኮስኩ፣ በማንም ላይም አልፈረድኩም «እንዳይፈረድብህ አትፍረድ» የሚለው ቃሉም በእኔ እንዲፈ ጸም እሻለሁ። በማንም ላይ አልፈረድኩምና እንዴት ይፈረድ ብኛል? ይህንንም ቃል እንደተናገርሁ የኃጢአት መዝገቤ ተቀዶ ነበር።»

በእርግጥ ይህ መነኩሴ የኃጢአትን ሕይወት አልመራም። እርሱ ሩህሩህ ነገር ግን አምልኮትን በግዴለሽነት ያዘ እንጂ። እርሱ በማንም ላይ ክፉን አልተናገረም። ትሑትም ነበር። ገንዘብ ባደረጋት ትሕትናው በሌሎች ባለመፍረዱ ይህ መነኮስ ዳነ። የፈጣሪ ትእዛዝ ለመንገዱ ብርሃን ነበርና ከፍርድ ማምለጥ ችሏል። እንዲያ ባይሆን ግን በቸልተኛነቱና በስንፍናው ምክንያት በተፈ ረደበት ነበር።

ቅዱስ ኤሪየስ እንዲህ አለ

አንድ ሰው በሀሜት የወንድሙን ሥጋ ከመብላት የወ[...] ድሙን ደም ከመጠጣት ይልቅ ሥጋ ቢበላ ወይንንም ቢጠ[...] ይሻላል።

ቅዱስ ኤሪየስ ደግሞ እንዲህ አለ

እባብ በወሬው ለሔዋን ከገነት መጥፋት /መሰደ[...] ምክንያት እንደሆነ ወንድሙንም የሚያማ እንዲሁ ነው። እን[...] ያለው ሰው ለሰሚዎቹ ነፍስ መጥፋት ምክንያት ይሆና[...] እባብ ከእርግማኑ እንዳላመለጠ የዚህም ሰው የራሱ ነፍስ ከጥፋ[...] አያመልጥም።

ስለዚህ እንዲህ ያለው ሰው ራሱንና ሌሎችንም ያጠፋል።

ቅዱስ ምስራ እንዲህ አለ

ከመብል መጠጥ ከመታቀብ በላይ የሆነች ራስን መግዛት የወንድምን ሥጋ እና ደም ወዳለመብላት ወዳለመጠጣት የምታ ደርስ ናት።

እነዚህ ቃላት ከቅዱስ ኤሪየስ ቃላት ጋር የሚመሳሰሉ ናቸው። ይህንንም የመሰለ ቃል በነነዌው ኤጲስ ቆጶስ ቅዱስ ይስሃቅ ተነግሯል።

ማር ይስሃቅ እንዲህ ይላል

ከመብል ከመጠጥ ታቅቦ የሚጾም አንድ ሰው በሀሜት የሰዎችን ሥጋ መብላትን ከቀጠለ ይህ ጾም የግብዝነት ነው።

ማር ይስሃቅ በሌሎች የሚፈርድን ሰው መንፈሳዊ ሳይሆን ስሜታዊ እንደሆነ ያስተምራል። በሁሉም ሰዎች ይፈር ዳልና። ምክንያቱም ልቡ የሰዎች ሥራ መልካም ወይም ክፉ ስለመሆኑ የሚመረመሩበት መልካሙንና ክፉውን የምታሳው ቀውን ዛፍ ይሟልና።

ማርይስሃቅ እንዲህ አለ

ስሜታዊ ሰው የፃድቁም የኃጥኡም ፈራጅ ነው። የንቁ ውም የሙቱም ፈራጅ ነው። በልቡ ውስጥ የዘር ግንዳቸን አዳም እንዳይበላት የተከለከለችው መልካሙንና ክፉውን የምታሳውቀው

ዛፍ አለች። ስሜታዊ ሰው እውቀቱን ዘወትር ከዚያቹ ያገኛል። ስሜታዊ ሰው የፍርድ ምንጭ ነው። ያገኘውን ሁሉ ሕያዋንንም ሙታንንም በመልካምና በክፉ እውቀት መሥፈርት ላይ ያስቀ ምጣል።

ምዕራፍ አምስት

መፍትሔዎች

፩. ሰዎችን ማክበር ልመድ

በሌሎች ላይ ለመፍረድ የሚያበቃውን ምክንያት ብናውቅ ኖሮ በሌሎች ላይ በመፍረድ የምናሳየው ጠባይ መፍትሔ ይሆን ነበር። የመጀመሪያው በሰዎች ላይ እንድንፈርድ የሚያደርገን ምክንያት ሰዎችን ለመጉዳትና ስማቸውን ለማጥፋት ለራሳችን የሰጠነው ነፃነት ነው።

ስለዚህ ሰዎችን ባሉበት ቦታ እንደምትወዳቸው እና እንደ ምታከብራቸው ሁሉ በሌሉበት ቦታ ሁሉ ለመውደድና እነርሱን ለማክበር እራስህን ግራ። በተመሳሳይ መልኩ ሌላውን ሰው ሲታና ገረውም ሆነ ስለ እርሱ ከሌላ ጋር ስታወራ እንዳታስቀይመው ተጠንቀቅ።

በሰዎች ላይ መልካም አስተያየት ካለህ ተናገረው፤ ከሌለህ ግን ዝም በል። ሌላውን እንዳትጎዳ ወይም መጥፎ ቃልን እን ዳትናገረው ራስህን አለማምድ። ማንንም ቢሆን አትተች ወይም አትመርምር፤ ይህንን ካደረግህ በማንም አትፈረድምና።

ሌሎችን የሚያከብር ሰው በማንም አይፈረድም። እንዲህ ያለው ሰው ሥነ ሥርዓት ያለው በመባል በሌሎች ይወደሳል። እርሱም ሌሎችን በአግባቡ በማክበርና በማቀላመጥ ይናገራል እንጂ መጥፎ ቃላትን አይናገርም። ምላሱንም ሌሎችን ለመጉዳት

ወይም መጥፎ ነገር በሌሎች ለማውራት አያውለውም። በመሆኑም በሌሎች አይፈረድም።

ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ በዚህ አንጻር ስለ ምላስና ስለ ስሕተቶቹ የሚለውን ተመልከት።

«በምላሳችን እግዚአብሔርን አባታችንና አምላካችንን እንባርክበታለን፤ በዚያው ምላሳችን በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠሩ ሰዎችን እንረግምበታለን» ያዕ. ፫፥፱

ስለዚህ በሰዎች ላይ የመፍረድ ኃጢአት በእግዚአብሔር አምሳል ለተፈጠሩ ሰዎች እርግማን ይሆንባቸዋል ዘፍ. ፩፥፳፮-፳፯ ሐዋርያው በድጋሚ «ከአንዱ አፋችን መርገምና ምርቃት ይወጣል፤ ወንድሞች እነዚህ ነገሮች ሊሆኑ አይገባቸውም» ይላል። ያዕ. ፫፥፲

እግዚአብሔር ግን «የሚረግሙአችሁን መርቁ» ማቴ. ፭፥፵፬ በማለት ያስተምረናል። ታዲያ ወንድሞቻችንን መርገም አግባብ ነው? ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም መርቁ እንጂ አትርገሙ ይለናል። ሮሜ. ፲፪፥፲፬ ስለዚህ አፋችን የታረመ ምላሳችንም ንጹህ እና በጎ ሊሆን ይገባዋል። ከእርሱም የምርቃት ቃል ብቻ እንጂ የፍርድ፣ የስድብ እና የእርግማን ቃላት ወጥተው ሌሎችን መጉዳት የለበትም።

ስለዚህ የሰዎችን መልካም ምግባር ብቻ ለመናገር እራስህን አለማምድ። በዚህም ተግባር በሰዎች ጠንካራ ጎን ላይ ብቻ አተኩር እንጂ ደካማ ጎናቸውን ንቀህ ተው። በአእምሮህ ውስጥ መጥፎ እና ጭጋጋማ ገጽታ ያላቸውን ሰዎች ቅዱስ ጳውሎ/

ለብር እንጣሪው እስክንድር እንደነበረው ዓይነት አመለካከት አድርገው እንጂ ዕኑ ሆኖ በሕይወትህ ሙሉ አይዝለቅ። ፪ጢሞ. ፱፥፲፱ እንደእነዚህ ዓይነት ሰዎችንም ስማቸውን እንኳ አትጥራ። እግዚአብሔር የሚያስተካክላቸው ወደ በጎም የሚመልሳቸው ከሆነ ታገስና ተመልከት። ይህ ከሆነ ደግሞ ለነርሱ የነበረህ እይታ ይስተካከላል።

ይህ ሁሉ ግን ለቤተ ክርስቲያን ጠላቶች እና ለፀረ ሃይማኖቶች አይሠራም። ቤተ ክርስቲያን እራስዋን ከእንደነዚህ ዓይነቶቹ መጠበቅ አለባት። ስሕተታቸውን እና ኑፋቄያቸውንም በግልጽ ማስተማር አለበት። ያ ከሆነ ማንም እነርሱ በጀመሩት ክህደት ውስጥ ገብቶ እንዳይወድቅ ይረዳዋል።

ጌታችን መድኃኒታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስም በመቅእለ ስብከቱ እንደእነዚህ ካሉት ሰዎች እንድንጠበቅ አስጠንቅቆናል። እርሱም በማቴ. ፯፥፲፭ ላይ «ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠበቁ» ሲለን በማቴ. ፲፥፲፮ ላይ ደግሞ «እነሆ እኔ እንደበጎች በተኩላዎች መካከል እልካችኋለሁ፤ ስለዚህ እንደ እባብ ልባሞች እንደ ርግብም የዋሆች ሁኑ፤ ነገር ግን ወደ ሸንጎ አሳልፈው ይሰጡአችኋል እና በምኩራቦቻቸውም ይገርፉአችኋልና ከሰዎች ተጠበቁ» ብሎናል።

፪. የጊዜ ማሳለፊያ የሚሆን መልካም ስምሪት ፈልግ

ሰዎች የሚሠሩት እና የሚያወሩት ሲያጡ ሌሎችን ወደ ማማት፣ ስሕተታቸውን እና ወራዳ ሥራቸውንም ወደ መግለጽ እንዲሁም ውድቀታቸውን ወደ ማውራት ይመጣሉ።

በመሆኑም ስለ ሰዎች ድርጊትና ጠባይ ማውራት በየቤቶች ውስጥ፣ በየክለቦች፣ ካፍቴሪያዎች እና ሰዎች በሚሰበሰቡበት ቦታ ሁሉ ዋና ጊዜ ማሳለፊያ ተደርጎ የሚወሰድበት ወቅት አለ። በሰዎች ላይ መፍረድ በመፈለጋቸው ምክንያት አይደለም፤ ከዚያ ውጪ ሊያወሩት የሚችሉት ነገር ባለመኖሩ ነው እንጂ። አንዳንዶች ደግሞ በጋዜጦች የሚያነቡትን ነገር እውነት ወይም ሐሰት መሆኑን ሳያጣሩ ፕሬዚዳንቶችን በመውቀስና በእነርሱም ላይ በመፍረድ ሰዓታቸውን ያሳልፋሉ። ወይም ደግሞ ስለ አንድ ታዋቂ፣ በጋዜጦች ስሙ የተጠቀሰና ለጊዜው በሕግ ቁጥጥር ሥር ስለዋለ ሰው በማውራትና ስሙን በማጥፋት ብዙ ወራት ድረስ ሊቆዩ ይችላሉ። በመጨረሻም በተከሰሰበት ጉዳይ ፍርድ ቤት በነጻ ሊያሰናብተው ይችላል። ነገር ግን አሁንም ስለ መታሰሩ እንጂ ስለመለቀቁ ያላነበቡ ሰዎች ሁሉ በእነዚያ ወራት ሲፈርዱበት ሊቆዩ ይችላሉ።

እኔ ሰዎች ትርፍ ጊዜያቸውን በሚጠቅሙና ቁም ነገር ባላቸው ወይይቶች ቢያጠፉ መልካም ነው እላለሁ። ይህንን ካደረጉ ደግሞ ስለ ሌሎች ሰዎች ጠባይ የሚያወሩበት ጊዜ አይኖራቸውም። ለምሳሌ ያህል በየኮሌጆች እና በዩኒቨርሲቲዎች ያሉትን ተማሪዎች እንመልከት። እነርሱ ፈተና በሚሰጥባቸው ጊዜያት ጊዜያቸውን ሁሉ ለፈተና በመዘጋጀትና በማጥናት ያሳልፋሉ። ስለዚህም ተረት የሚያወሩበት በአስተማሪዎቻቸው በመቀለድ ሌሎችን በብልሹ ሥራቸው በመንቀፍ የሚያሳልፉበት

ምንም ጊዜ የላቸውም። በእነርሱም ላይ በመፍረድ እርስ በእርሳቸው ሲጣሉ እና ሀሜቱ ሲሰፉ አይታይም።

ብዙ ሥራ ያላት ሴትም ቁጭ ብላ ከጎረቤቶችዋ ጋር ስለ ሌሎች በመፍረድና በማማት ጊዜዋን አታባክንም። የሚነጋገሩበት ሰዓት ከተገኘ ግን ሌሎችን በክፉ ሥራቸው ወደ ማማት በእነርሱም ወደ መፍረድ መግባቱ አይቀርም። ሁሉም ይህ ዓይነት ፍላጎት ኣላቸው ማለት ሳይሆን እንዴት ጊዜያቸውን ማሳለፍ እንደሚገባቸው በማያውቁት ዘንድ የሚታይ ነው።

በትርፍ ጊዜ ማለታችን የነገሩ እውነትነት ከፊል /ግማሽ/ ገጽታ ነው። ይህን ትርፍ ጊዜ የምናሳልፍበት መንገድ ደግሞ ሌላው ከፊል ገጽታ ነው። መፍትሔው ችግሩን ለመፍታት በቂው ጊዜ ማግኘት ሳይሆን ጊዜውን እንዴት ማሳለፍ እንደሚገባን ማወቅ ነው። ስለዚህ ጊዜን በአግባቡ ማሳለፍ ያወቁ ሰዎች ባገኙት ትርፍ ሰዓት በንባብ እራሳቸውን እና ሌሎችን እንደሚጠቅሙ አድርገው ያሳልፉታል ሌሎችም የእጅ ሥራ ሙያን ወይም ትምህርት ይማሩበታል። ከዚህ በተለየ መልኩ ሌሎች ደግሞ የታመሙትን በመጠየቅ ያዘኑትን በማጽናናት እንዲሁም የተቸገሩትን በመርዳት መልካም የሆነ መንፈሳዊ ሥራን ይሠሩበታል።

ከሌሎች ሰዎች ጋር በተሰበሰብክ ሰዓት ጠቃሚ የመወያያ አርእስት ማግኘት ይገባሀል። ብዙ ሰዎች በተሰበሰቡበት ቦታ አንድ ቁም ነገረኛ እርሱ በደንብ የሚያውቀውንና ማናቸውንም ጥያቄ የሚመልስበትን ሌሎችንም የሚስብ የመወያያ አርእስት

በማቅረብ ሌሎች ሰዎችን ከመፍረድ እና ከሀሜት መታደግ ይችላል።

ይህ ጉዳይ በቤተሰባችን ውስጥ ጭምር ሊከሰት የሚችል ነውና ልንሠራው ይገባል። በቤታችን ከቤተሰቦቻችን ጋር ባለንበት ሰዓት ሳይንሳዊ ወይም መንፈሳዊ የሆነን አንድ አርእስት በማንሣት ውይይቱን አቅጣጫ ማስያዝ እንችላለን። በዚህም ውስጥ አዲስ ዜናን ወይም ግኝትን ካልሆነም ያነበብነውን መጽሐፍ በአጭሩ በማቅረብ ወይም ታሪክና ባህልን በጉዳዩ ላይ በማንሣት ሁሉንም ማሳተፍ እንችላለን። ይህም ሲደመደም ቁም ነገር አዘል ቀልዶችን፣ እንቆቅልሾችን፣ የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀታችንን የሚፈትሹ ጥያቄዎችን ወይም ገድለ ቅዱሳንን ሁሉንም በሚያሳትፉና በማይሰለች መልኩ በማቅረብ ጥሩ ሰዓት ልናሳልፍ እንችላለን።

ከየቤተሰቦቻችን ጋር ዓላማ ያለውን ውይይት ለማድረግም ከሌሎች ባልንጀሮቻችን ጋር እንደምናደርገው ያለ ዝግጅት ይፈልጋል። መሰባሰብ ያለ ዓላማ ከሆነ ግን ወደ ሐሜት የሚወስድ አደገኛ መንገድ ነው። እንዲህ ያሉ ግንኙነቶች የምናወራበት ጠቃሚ ጉዳይ ከሌለን ወይም ውይይቱን በብልሀት የሚመራው እስከሌለ ድረስ የማይረቡ ወሬዎች የሚወሩበት ሌሎችን የማማት ነገር የሚከሰትበት ይሆናል። ከዚያም አልፎ ወደ ጭቅጭቅ፣ መሰዳቸትና ጠብ ሊያስገባን ይችላል። ስለዚህ መሰባሰባችን ለዓላማ እና ለውጤት ሊሆን ይገባዋል። የአእምሮ ስንፍና እንጂ ትርፍ ጊዜ በራሱ ጎጂ አይደለም።

ይህንን ስንል በየቤታችን፣ በክለቦች እና በካፍቴሪያዎች ሀሜት ብቻ ለምን ይወራል? የሚል ጥያቄ ሊነሣ ይችላል። መልሱ ግን አጭርና ግልጽ ነው። እነዚህ ሰዎች ስነፍ አእምሮ ስላላቸው የሚያወሩት እና የሚወያዩበት መልካም የሆነ አርስት የላቸውም የሚል ይሆናል።

፫. መፍረድን ከመስማት ተለይ

በተቻለህ መጠን በሰዎች ላይ የሚወራውን ሀሜትና ፍርድ ላለመስማት ሞክር እንደዚህ ዓይነት ፊተና ሊያመጡብህ ከሚችሉ የሰዎች ስብስብ ተለይ። መለየት የማይቻልህ እንኳ ቢሆን አእምሮህን ሌላ ነገር እያሳሰብክ የሚሉትን ላለመስማት ሞክር።

በተጨማሪም ስለ ሌላው የሚወራውን ምን ጊዜም ቢሆን በጥሬው አትመን ሀሜቱን የሚነግርህ ሰው ምን አልባትም ሌላ ሰው ካወራለት አግኝቶ የሚያወራ ስለሆነ እውነታው የተዛባ ሊሆን ይችላል። በተጨማሪም በሌላው የሚፈረደውም ሰው ይህንን የሚልበት የራሱ ምክንያት ሊያቀርብ እንደሚችል ገምት። ከአንድ ወገን ሆኖ የተነገረን እውነታ ማወቅ እና መፍረድ አይቻልም። ስለዚህ ለራስህ እንዲህ በል «የሚባለው እውነት ቢሆንም ያ ለኔ ምኔ ነው?»

እነዚህን ቃላት ምን ጊዜም ደጋግማቸው፤ በተጨማሪም «እኔን ምንም አያገባኝም፤ የራሴን ጉዳይ ብቻ ማየት ይገባኛል» በል። የሰዎች ጉዳይ እኔን አይመለከተኝም። በእግዚአብሔርም ፊት እንዲህ እንዲደረግ ሓላፊነት እና ሥልጣን አልተሰጠኝም

ስለዚህ ስለ ሰማሁት ጉዳይ ትኩረት አልሰጠውም በማለት እራስህን አሳምን።

እንደዚህ ያለ አስተሳሰብ በሰዎቹ ላይ ከመፍረድ ይጠብቅሃል። ስለዚህ የሰማኸውን ፍርድ እና ሀሜት ችላ በለው። ይህን በማድረግም በአንተ ውስጥ ቦታ ከማግኘትና ከማደጉ ትክለ ክለዋለህ።

ሰዎች ለሚፈርዱበት ሰውም እግዚአብሔር ኃጢአቱን ይሸፍንለት ዘንድ ጸልይለት። እግዚአብሔር ያስተካክለውም ዘንድ ጸልይለት እንጂ እርሱን ከመናቅ እና ከማማት ተቆጠብ።

ሙሴ ጸሊም ስለዚህ ነገር ሲናገር እንዲህ አለ «ማንም ቢሆን የወንድሙን የውድቀት ወሬ አይስማ፣ ምክንያቱም በውስጡ በእርሱ ላይ ከመፍረድ ይድናልና» ሰዎችን ማረም የሚል ሰበብ አታምጣ።

ሰዎች ይስተካከሉ የሚል ሰበብ መፍጠርና ሰዎችን ማማትም ሆነ በእነርሱ መፍረድ ልክ አይደለም። በመንፈሳዊ ቅናት ተነሣሥቼ ነው ይህንን የማደርገው የሚል ሐሳብ ቢኖርህ እንኳ የሚከተለውን ማለት ይኖርብሃል።

«ሌሎችን አድናለሁ ብዬ እራሴን ማጣት የለብኝም» በተጨማሪም ሌሎችን የማስተካከለው በፈቃዴ ነው ወይስ ለዚህ ከእግዚአብሔር ፈቃድ አግኝቻለሁ። ይህንንስ ካላደረግሁ ሀሊናዬ ይወቅሰኛልን? ሌሎችንስ ለማስተካከል ብቃቱ አለኝ? በማለት እራስህን መጠየቅ አለብህ። ሌሎችን ለማስተካከል የሚፈልግ ማንም ቢኖር በጥበብ እና በመልካም ምግባር ሊያስተካክላቸው

ይገባል። ይህ የሚሆነውም በፍቅር በትሕትና ቢታረሙ እና በረጉ ቃላት ነው። ማንም ሳይጎዳ ወይም የሚታረመው ሰው ደካማ ጎኖቹ ከሌሎች ሰዎች ተሰውሮ ሊነገረው ይገባል።

ከዚህ በተለየ ማንንም ቢሆን በወቀሳና በስም ማጥፋት ማስተካከል አይቻልም። ጌታችን እንዴት ባለ መልካም ቃላት ይህንን እንደሚገልጸው ተመልከት። ማቴ. ፲፰፥፲፭ «ስህተቱን በአንተ እና በእርሱ መካከል እንዳለ ምከረው» ዮሐንስ አፈወርቅ ይህንን ሲያስረዳ «ጌታ እንኳን በአንተና በእርሱ መካከል ይሁን ያለውን አስተውሉ» ብሏል። ስለዚህ የሰውን ስሕተት የከተማው ሕዝብ ሁሉ ባለበት ለማረም ከመነሣት በአንተና በእርሱ መካከል በምስጢር ብታደርገው ሰውየው ይማርበታል።

እግዚአብሔርም ለአንተ በዚህ ዓይነት መንገድ ይቅር ብሎሃል.. እግዚአብሔር ለአንድ ለሠራኸው ኃጢአት ሊቀጣህ ሲፈልግ ወደ ንስሐ ይመራሃል። ከቤተ ክርስቲያን ምስጢራትም አንዱ በሆነው በንስሐ ውስጥ ባንተና በካህኑ መካከል በምስጢር ኑዛዜህን ትናገራለህ። ኃጢአትህንም እግዚአብሔር እንዲሸፍን ተገንዘብ።

እውነትን ለመመስከርና ሌሎችንም ለማረም ስትነሣ ቅዱስ ጳውሎስ በገላትያ ፮፥፩ ያለውን ማሰብ ይኖርብሃል። በዚያ ወንድሞች ሆይ ሰው በማናቸውም በደል እንኳ ቢገኝ መንፈሳውያን የሆናችሁ እናንተ እንደዚህ ያለውን ሰው በየውሃት መንፈስ አቅኑት አንተ ደግሞ እንዳትፈተን ራስህን ጠብቅ» ብሎአል። ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብም በመልእክቱ ፭ይ «ከእናንተ ጥበበኛ

እና አስተዋይ ማን ነው? በመልካም አኗኗሩ ሥራውን በጥበብ የዋህነት ያሳይ፤ ነገር ግን መራራ ቅንዓትና አድመኛነት በልባችሁ ቢኖርባችሁ አትመኩ፤ በእውነትም ላይ አትዋሹ። ይህ ጥበብ ከላይ የሚወርድ አይደለም።» ያዕ ፫፥፲፫-፲፭

ያለሌላ ምንም መነሻ በመንፈሳዊ ቅናት ብቻ ልትነሣሣ ትችላለህ? ለዚያስ ሰው ፍቅር በማጣት፣በውስጣዊ ተንኮል፣ ፍንደቃ ወይም ከሌሎች የበለጠ የተማረ ፣መምህር ወይም መሪ መስሎ መቅረብስ እውነተኛ ምክንያት ሊሆን ይችላል? ራስህን በአግባቡ መርምር።

በቅናትህ ውስጥ ሆነህ የእግዚአብሔርን ሥልጣን ከሕዝቡ አገኘሁ የምትል ከሆነም ራስህን ጠይቅ።

ሌሎችን ከማረምህ በፊት ራስህን ማረም ጀመርከን? ሳትጎዳው የወንድምህን ጉድፍ ከወንድምህ ዓይን ለማስወገድ አጥርተህ ታያለህ። ማቴ. ፯፥፭ ሌሎችን ስለማረምም በፊታችን ማስቀመጥ የሚገባን ነገር አለ።

፬. የእንክርዳድና የስንዴው ምሳሌ

ሠራተኞቹ ወደ ጌታቸው መጥተው እንክርዳዱ ከአዝመራው እንዲሰበሰብ ይፈልግ እንደሆነ ጠየቁት። ጌታም እንዲህ በማለት መለሰ «እንክርዳዱን ስትለቅሙ ስንዴውን ከእርሱ ጋር እንዳትነቅሉት አይሆንም። ተውአቸው እስከ መከር ጊዜ አብረው ይደጉ።» ማቴ. ፲፫፥፳፰-፴

እግዚአብሔር ጉልበታችንን ሁሉ እንክርዳድ በመሰብሰብ እንድናባክን አይፈልግም፤ እንደ ስንዴ እንድናድግ እንጂ።

መከር በመጣ ጊዜ ቅንጣቶች ሠላሳ፣ስድሣ፣ መቶም የሞላ ፍሬ ሆነው ይገኙ ዘንድ፣ ጎተራችንም በስንዴ ይሞላ ዘንድ እርሱ እንደ ስንዴ እንድናድግ ይፈልጋል።

ዛሬ በመንፈሳዊ ቅናት ስም፣በማረም ስም እንክርዳዱን በመልቀም የተጠመዱ ብዙ ናቸው፤ ነገር ግን በንዴት፣ በቁጣ፣ በጩኸት፣ መፍረድንም በማስፋፋት፣ በወቀሳ በስድብ ሌላውን በመገሠጽ አባዜ የተሞሉ ናቸው። ክብርን በማይሰጡና መልካምነት በሌላቸው ጠንካራ ቃላት የቤተክርስቲያንን፣ የማኅበራትን፣ የአገልጋዮችን የካህናትን ጉድለት መናገር ለምደዋል። ነገር ግን ሰዎች በእነዚህ የተሐድሶ አራማጆች በራሳቸው ቁጣና ጎጂ ጠባዮች ውስጥ የእንክርዳድነትን ሥዕል /ገጽታ/ በትክክል ያያሉ።

እኔ ግን እንክርዳድን በምትነቅልበት ጊዜ ውስጥ አንተ ራስህ እንክርዳድ እንዳትሆን እፈራለሁ።

ትሕትናና የዋህነትን ልታጣ ትችላለህ። እናም ተሳዳቢ፣ ጎጂ፣ ስም አጥፊ እና አብራተኛ ትሆናለህ። ፍርዶችህ ጭካኔ ይሆናሉ፤ ለሌሎች የጥላቻና የጸብ ስሜት ያድርብሃል፤ ቁጡም ትሆናለህ! እንዴት የሚደንቅ ነው! በእነዚህ ኃጢአቶች ውስጥ ሁሉ የወደቅኸው ግን ለጌታ ስትሬ ነው?!

ከሌሎች ውስጥ እንክርዳድን ስትነቅል በአንተ ውስጥ ያለውን ስንዴ እንዳትነቅል ተጠንቀቅ። ርጋታህ፣ የልብህ ሰላም እና መልካምነትህ ከእነርሱም ጋር በአንተ ውስጥ ያሉ የመንፈስ ፍሬዎች ማለትም «ፍቅር ደስታ ሰላም ትዕግስት ቸርነት በጎነት እምነት የውሃት ራስን መግዛት» እንዳይነቀሉ ተጠንቀቅ። ገላ ፭፥፳፪

ምንም እንኳን ይህን ሁሉ ብታጣ ማንንም አለማስተካከልህን ታገኛለህ /ታውቃለህ/። ምንም እንዳላገኘህ ትረዳለህ፤ ሰማይንም ሆነ ምድርን፤ ሰዎችን ወደ መንግሥተ እግዚአብሔር መምራትንም፤ ያንተን እርጋታና ከሰዎች ጋር ያለ መልካም ግንኙነትን። ሰዎችንም ራስህንም አላገኘህም፤ ምክንያቱም ሰዎችን በመፍረድና ስም በማ ጥፋት እንዲስተካከሉ ማድረግ አይቻልምና።

ቅዱስ አውግስጢኖስ እንዲህ ይላል

«በክፉው የምንናደድ ከሆነ ሰዎች ብቻ መሆናችን ነው የሐዋርያውን ቃል መስማት አለብን። «እንደቆመ የሚመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ» ፩ቆሮ.፲፥፲፪

እነሆ ስንዴ እንሁን፤ እንክርዳድንም በመንቀል ጊዜያችንን እናጥፋ። እኛኑ ራሳችንን እንክርዳድ እንዳናደርግ በውስጣችን ያለውን ኃጢአት እንንቀል፤ እናስወግድም። ሌሎችን ለማረም በመሞከር ራሳችንን ማረም እንርሳ።

ማንኛውም ሌላውን ጠያቂ /ከሳሽ/ ሆኖ ሲቀመጥ እንዴት ይደነቃል፤ አንድ ሰው የሌሎችን ሲያስብ፤ ሥራቸውንም በእነርሱም ላይ በፍርድ ቃል ሲናገር የመጨረሻውን ግን ለራሱ ሲያደርግ እንዴት ይደነቃል?

እመኑኝ ይህ ትኩረታችንን ከእኛ ስበ የሌሎችን ኃጢአት እንድናስብ፤ ከንስሓ ሕይወት ይልቅ የሌሎችን ሥራ እንድንቆጥር ፈልጎ ሰይጣን ያቀረበው ፆር ነው።

በመጨረሻው ቀን ግን እግዚአብሔር የሚጠይቅህ የራስህን ኃጢአት እንጂ የሌሎችን በደል አይደለም።

፭. ትሕትናና ራስን መገሠጽ

በሌሎች ላይ የመፍረድ ኃጢአት በራስ ላይ በመፍረድ ሊፈወስ ይችላል። ይህም አንዳንድ ቅዱሳን እንደነገሩን እርስ በእርስ በመናዘዝ ነው። ቅዱስ ኢቫግሪዮስ «እንደ በደለኛ አድርገን በራሳችን የምንፈርድ ከሆነ ሌሎችን ንጹህና መላእክት ሆነው እናያቸዋለን። ነገር ግን በሌሎች ላይ እንደ በደለኛ የምንፈርድ ከሆነ ራሳችንን እንደ መላእክትና ቅዱሳን እናያለን።»

በአንድ ወቅት ጥቂት ወንድሞች በቅዱስ ጴሜን ፊት አንዱን ሰው «ክፉውን ይጠላል» በማለት ያመሰግኑታል። ይህም ቅዱስ «ክፉውን መጥላት» ሲል ምን ማለታቸው እንደሆነ ይጠይቃቸዋል። እነርሱ በዚህ ነገር ግራ በተጋቡ ጊዜ ቅዱሱ እንዲህ በማለት ገለጸላቸው «ክፉውን መጥላት ማለት የምናደርገውን ክፉ ነገር እንጂ ሌሎች የሚያደርጉትን ማለት አይደለም» አላቸው።

ቅዱስ እንባቆምም እንዲህ አለ

«በሌሎች ላይ መፍረድ የአንድ ሰው የእብሪት ውጤት ነው። ትሑት ሰው ግን ሁሉንም ሰው ከእርሱ እንደሚሻል ያስባል።» «ራስህን ጻድቅ አድርገህ እንድታስብ ከሚመራህ ማንኛውም ሐሳብ፤ ወንድምህንም ከመናቅ ራስህን ጠብቅ፤ ምክንያቱም ሌሎችን የሚያከብር ራሱንም የሚንቅ እጅግ ብፁዕ ነውና።»

ስለዚህ በሌላው የመፍረድ ፆር በገጠመህ ጊዜ ኃጢአትህን አስታውስ፤ እንዲሁም በል «ያ ሰው ከእኔ ይልቅ ፃድቅ ነው፤

ምክንያቱም እኔ እንዲህ እና እንዲያ ነገሮችን አድርጌአለሁ፤ እርሱ እኔ በወደቅሁበት ዓይነት ነገር ሊወድቅ አይችልም።»

በዚህ ረገድ ማር ይስሐቅ እንዲህ አለ። ያንተን ደካማ ነጥቦች የማታስብ ከሆነ በሌሎች ድካመት ውስጥ ትወድቃለህ። በራስህ ኃጢአቶች ላይ የማታተኩር ከሆነ፤ እነርሱንም በማሰብ የማትጠበቅ ከሆነ በሌሎች ሰዎች ኃጢአት ውስጥ ትወድቃለህ።

አንድ ጊዜ አንድ ወንድም አንድ አረጋዊ መነኩሴን «ለምንድን ነው ዘወትር በወንድሞች ላይ የምፈርደው?» በማለት ጠየቀው። ያም አባት እንዲህ በማለት መለሰለት «ለራስህ የምታስብ ከሆነ ስለሌላው የምታስብበት ጊዜ የለህም፤ በዓይኑ ግንድ እንዳለ ያወቀ፣ ያንንም ለማውጣት /ለማስወገድ/ የሚሞክር በወንድሙ ዓይን ያለውን ጉድፍ ለማስወገድ ጊዜ አይኖረውም።»

እንግዲህ በሌላው ላይ የመፍረድ ሐሳብ በመጣብህ ጊዜ ለራስህ እንዲህ በለው «እኔም ደግሞ ኃጢአተኛ ነኝ» «ራሴን በአግባቡ ልመርምር፤ ራሴን ያለ ኃጢአት የማገኘው ከሆነ፣ በእርሱ በወንድሜ ላይ ጠጠር እወረውራለሁ»

በአንድ ወቅት መነኮሳት አንዱን ወንድም ከገዳሙ አስናበቱት፤ ቅዱስ ሴራፒዮን የዚህን ምክንያት በጠየቃቸው ጊዜ በወደቀበት ኃጢአት ምክንያት መሆኑን ነገሩት። ይህንንም በሰማ ጊዜ ቅዱስ ሴራፒዮን «እኔ ራሴ ደግሞ ኃጢአተኛ ነኝ» በማለት ከማኅበረ መነኮሳቱ ተለየ።

እንዲሁም በበደለ አንድ ወንድም ላይ እንዲፈርድ የተጠራበት የቅዱስ ሙሴ ጸሊም የታወቀ ታሪክ አለ። ያም ቅዱስ

በአሸዋ የተሞላና ቀዳዳ ያለው ከረጢት ተሸክሞ/አዝሎ/ መጣ። ለምን እንዲህ እንዳደረገም በተጠየቀ ጊዜ «እነዚህ ከኋላዬ የሚከተሉኝ ብዙ ኃጢአቶቼ ናቸው ነገር ግን በወንድሜ በደል ለመፍረድ በዚህ አለሁ»

በአንድ ወቅት አንድ ወንድም ቅዱስ ጴሜን «ሌሎችን ላለማማት ራሴን የምገዛው እንዴት ነው?» በማለት ጠየቀው። ቅዱሱም እንዲህ በማለት መለሰ «አንድ ሰው ራሱን በሚወቅስ ጊዜ ወንድሙ በፊቱ ከእርሱ በላቀ የከበረ ይሆናል። በዓይኑም ፊት ከእርሱ ይልቅ ታላቅ ይሆናል። ነገር ግን አንድ ሰው ራሱን የሚያደንቅ ከሆነ ወንድሙ በፊቱ የተሳሳተና የተወገዘ ይሆናል።»

ማር ይስሃቅ እንዲህ ይላል «በራሱ የሚፈርድ ወንድሙንም የሚያከብር እርሱ ብፁዕ ነው። በሰዎች ድካመት ውስጥ የራሱን ውድቀት የሚያይ እርሱ ብፁዕ ነው።»

ይህም ማለት አንድ ሰው በሌሎች ጉድለትን ባገኘባቸው ጊዜ ሁሉ በእነርሱ በመፍረድ ፈንታ ራሱን መመርመር፤ በራሱም ያለውን ጉድለት መፈለግ አለበት። እናም አንድ ሰው ሌሎች አንድ ሌላን ሰው በአንድ ጥፋቱ ሲገሥጹ /ሲወቅሱ/ የሚያዩ ከሆነ ለራሱ «ወንድሜ ይህ ምት በቀጥታ ወደ አንተ የሚያመራ ነው» ሊል ይገባል።

፮. በሌሎች ላይ መፍረድን ለማስወገድ የሚረዱ የመፍትሔ ልምምዶች

፮.፩ ከንግግር ኃጢአት ራስህን ለመፈወስ ራስህን አሠልጥን። በተዘዋዋሪ በዚህ መንገድ በሌሎች ላይ የ ፍረድን ኃጢአት ታስወግዳለህ። አንተን በማይመለከቱህ ጉዳዮች ጣልቃ ባለመግባትና በጸጥታ አንዳንድ ልምምዶችን ለማድረግ ሞክር። በዚህ ጊዜ በሌሎች የመፍረድ ኃጢአት ቀድመው ከሚወገዱት የንግግር ኃጢአቶች አንዱ እንደሚሆን ጥርጥር የለውም። እንዲህ ያለው ልምምድ በንግግር መፍረድን እንድትቋቋም ይረዳሃል፤ በሕሊናም ከመፍረድ እንድትቆጠብ የሚያስችል እርምጃ ይሆናል።

፮.፪ «እንግዲህ ከወዴት እንደወደቅህ አስብ፤ ንስሐም ግባ» /ራእ. ፪፥፭/ የሚለውን የጌታን ቃል አስታውስ። ይህ ደግሞ ለራስ ቁጭ ብሎ በማሰብ የሚመጣ ነው። እንዲሁም በእርሱ ዘወትር መሞከር፣ በሌሎች የሚፈረድባቸውን ሰዎች ማንነት ለመለየት፤ በሌሎች ላይ ወደ መፍረድ የሚመሩህ ጉዳዮች ምንድናቸው? የትኞቹ ግንኙነቶች ወይም ጠባዮች ለአንተ የማሰናከያ ድንጋይ ናቸው? ከዚያም ለእነዚህ በሌሎች ለመፍረድ መነሻ ለሚሆኑ ነገሮች መከላከያ /ጠባቂ/ ይሁኑልህ።

፮.፫ በሌሎች ላይ መፍረድን በፍቅር አሸንፍ

ለአንዳንድ ሰዎች ፍቅር የምታጣ ከሆነ ወይም ለእነሱ ያለህን ፍቅር በከፊል ካጣህ ያቻልከውን ያኸል ያጣኸውን ፍቅር ለመመለስ ጣር፤ ምክንያቱም ቅዱስ መጽሐፍ ስለፍቅር እንዲህ ይላል፤ «የማይገባውን አያደርግም፤ ክፉ ነገርን አያስብም፤. . .

ስለ ሀመፃ ደስ አይለውም» ፩ቆሮ. ፲፫+፭-፮ ስለዚህ ፍቅር በጎደለው ልብህ ላይ ተመሥርተህ አትፍረድ።

በሌሎች ላይ መፍረድ ግንኙነትን መጥፎ እንደሚያደርግ እርግጠኛ ሁን። የቀደመ ፍቅርህን በመመለስ ፈንታም በአንተና በምትፈርድበት ሰው መካከል ያለው ክፍተት የበረታ ይሆናል፤ በተለይ ወሬውን የሚያስተላልፉ፣ የሚያባዙና በዚያ ላይ የሚጨምሩ አንዳንድ ሰዎች የሚኖሩ ከሆነ። እንዲህ ያሉት ሰዎች ባይኖሩም ያንተ ሕሊናና ልብ ሰላም ሊሆን አይችልም።

፮.፬ በሌሎች መፍረድ በአንተም ላይ ደግሞ ጉዳት እንደሚያስከትል አስብ።

ቅዱሳን እንዲህ ይላሉ፤ አንድ ሰው በሌሎች የሚፈርድ ከሆ፣ ከጸጋ እግዚአብሔርና ከረድኤቱ የተነፈገ ይሆናል፤ ለውድቀትም ይጋለጣል። ጌታም እንዲህ ብሏል «በምትሠፍሩበት መሥፈሪያ ይሠፈርላችኋል፤ ለእናንተም ይጨመርላችኋል።» ማር. ፬+፳፬ በተጨማሪም በሌሎች ላይ መፍረድን በሚመስሉ በሌሎች ኃጢአቶች ውስጥ ትወድቃለህ።

ቅዱስ ቤፍኖሺየስ /Bephnolius/ እንዲህ ይላል

በወንድምህ ላይ አንዳችም ክፉ ቃል አትናገር፤ አባታችውን ሙሴን ከዚያ ዕድል ፈንታ ነፍጎ ኢያሱና ካሌብን ወደ ቃል ኪዳኗ ምድር እንዲገቡ ባደረገ ጊዜ በእስራኤል ሕዝብ ላይ እንዳደረገው እግዚአብሔር ከቃል ኪዳኗ ምድር፣ በእርሷም ካለ ፍሬ እንዳትበላ እንዳያደርግህ።

አንድ አረጋዊ መነኩሴ በአንድ ወቅት እንዲህ አለ። የሀሜት ኃጢአት በውስጡ የወደቀ ማንንም እግዚአብሔር ባለበት እንዲቆም አይፈቅድለትም፤ ምክንያቱም «ባልንጀራውን በቀስታ/በሹክሹክታ/ የሚያማን እርሱን አሳደድሁ።»የሚል ተጽፏልና። መዝ. ፻፩+፭

ውድቀትንና ቅጣትን በመፍራት በሌሎች ላይ ከመፍረድ ተጠበቅ። ከመጽሐፍ ቅዱስ በሌሎች ላይ ስለመፍረድ የሚናገሩ ጥቂት ጥቅሶችን በሀሊናህ ማስቀመጥ ትችላለህ።እነርሱንም በልብህ ውስጥ ተማራቸው፤ ደጋግማቸውም፤ አሁንም በኋላም እነሱን አሰላስል።

፮.፭ የሰዎችን ክፉ ሥራ አለማሰብን ወይም በችኮላ አለመፍረድን ለራስህ አስለምድ። የሰዎችን ክፉ ሥራ በማሰብ ውስጥ ጨዳኝ /በደይ/ ልትሆን ትችላለህ፤ በሌሎች ላይ በችኮላ ስትፈርድም እንደዚያው። ፈጥነህ ጉዳዮችን/ነገሮችን/ ሳትመረምር በማንም ላይ አትፍረድ። መብቱ ኖረህም አልኖረህም ቢያንስ በእርጋታና አስበህ መፍረድን ለራስህ አስለምድ። ጥቁር መነጽር አድርገህ ሰዎችን የምታይ እንደሆን ተጠንቀቅ።

፮.፮ በሰዎች ላይ በርህራኄ መፍረድን ለራስህ አስለምድ

ከምሕረት ጎራ/ወገን/ ሁን እንጂ በጭካኔ ውስጥ አትሁን። ፍርዱን ቀላል ሊያደርግልህ የሚችል ይቅርታን በውስጥህ አስብ። በርህራኄህ ውስጥ ለበዳይ ጸልይ፤ ጸሎት የርህራኄን ስሜት ያመጣል/ያነሣሣል/፤ ርህራኄም ለጸሎት ያነሣሣል።

፮.፯ በሚታዩ ነገሮች ሁሉ አትፍረድ

በቤተክርስቲያን ፊት ለፊት የቆመ አንድ ሰው ገንዘብን በመጠየቅ እየለመነ ልታገኘው ትችላለህ፤ ምክንያቱ ለልጁ የሚያበላው ማጣቱ ነው። ነገር ግን ማንም አይሰጠውም። በዚህ ጊዜ በልብህ «ለዚህ ለተራበ ሰው ርህራኄ የሌላቸው እነዚያ ሰዎች እንዴት ጨካኞች ናቸው» ልትል ትችላለህ። ነገር ግን ብትጠይቅ ብዙ እንደተቀበለ /እንዳለው/ ታውቃለህ፤ ምናልባትም ከሚፈልገው በላይ እጅግ ብዙ። ነገር ግን በቃኝ ያላለ ይሆናል። ስለዚህ የሚለምነው ከሚገባው በላይ እጅግ ብዙ ለማግኘት የሰዎችን ልብ ለመሟሟን /ለማሳመን/ እንዲረዳው ነው።

፮.፰ የሚፈትኑህን /የሚያስቆጡህን/ መታገስን ራስህን አስለምድ። አንዳንዴ ትዕግሥትን እንድታጣ፣ ብስጭት እንዲሰማህ ሌሎችንም እንድትከስ ያደርግሃል። በሰው ሁሉ ፊት በደላቸውን እንድታወራ፤ በቁጣህ መሠረትም እንድትፈርድባቸው ያደርግሃል።

ያለነው ፍፁም በሆነ ዓለም ውስጥ አለመሆኑን እወቅ፤ ስሕተት ይኖራል። በስሕተት ሁሉ ላይ የምንነጣ ከሆነ ቁጣችንንም በምላሳችን በመፍረድና የሰዎችን ስሕተት ሁሉ በማውራት በመጉዳትና በመቅጣትም ቁጣችንን የምንገልጽ ከሆነ እኛን ደስ እንደሚለን አይጠረጠርም። ነገር ግን ማንም በደስታ ውስጥ አይሆንም። የሰዎች ብዙ ስሕተቶችን እንድንተዋቸው በትዕግሥትና በመቻል እንድናያቸው እንዳልሆነም አድርገን እንድናስብ በፈጸሟቸውም ላይ እንዳንፈርድ ይፈልጋሉ።

፮.፱ ሰውን እጁ በሌለበት ሁኔታ አትፍረድበት

አንድን ሰው በቅርጹ፣በሐሳቡ ወይም እጅግ በጣም አጭር ስለ ሆነ ወይም እጅግ በጣም ወፍራም ወይም የመሳሰሉትን በመሆኑ ምክንያት እንዲህ ያለውን ሰው ለፌዝ እና ለንቀት አትስጠው /አታጋልጠው/። አንድ ሰው ከቁጥጥሩ ውጪ በሆነበት ነገር ብትፈርድበት ቅን ፍርድ አይደለምና።

፮.፲ በወቀሳ መልክ ስትፈርድም ጥንቁቅ ሁን

ምንም እንኳን እግዚአብሔር ወቀሳን ቢፈቅድም ሁሉም ግን ወቃሽ ሊሆን አይገባም። ማቴ. ፲፰+፲፭ ብዙ ጊዜ ወቀሳ መጥፎ ውጤቶች ያመጣል። ስለዚህም መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል «ፌዘኛን የሚገሥጽ ለራሱ ስድብን ይቀበላል፤ ኃጥእንም የሚዘልፍ ነውርን ያገኛል። ፌዘኛን አትገሥጽ እንዳይጠላህ፤ ጠቢብን ገሥጽ ይወድሃል።» ምሳ. ፱+፯-፰

ለማጠቃለል ያህል በሌሎች መፍረድ በውስጥህ ያለ ጠባይ እንዲሆን አትፍቀድ።

ፍርድን በማሳለፍና መፍረድ ጠባይ ሆኖ በመገለጡ መካከል ልዩነት አለ። ጠባይ በሚሆንበት ጊዜ በሔደበት ሁሉ ምክንያት ኖረም አልኖረም ይፈርዳል፤ ያወግዛል፤ ይተቻል፤ የሰዎችንም ሥራ ይተነትናል።